

"ጠ/ሚኒስትሩ የቂም በቀል ሰንሰለት ካንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሰበረው ይመስለኛል"

ስዩም ተሾመ

የአንዳርጋቸው የአራት ዓመት የእስር ቤት ቆይታ ምን ይመስላል

ከንፈሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶ)

“ሀገሪቱ እየተመራች ያለችው በአዋጅ እንጂ በሕግ አይደለም”

ብ/ ጄነራል ተፈራ ማሞ




መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

ልዩ ዕትም

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 8 ግንቦት 2010 ዓ.ም ዋጋ 14.99




- የሰነዓ ኤርፖርት አፈና
- “ከግብፅና ከኤርትራ ጋር ስላለን ግንኙነት በስፋት ጠይቀውኛል”
- “ጠ/ሚ ዐብይ እንደ ነጂ ሳይሆን እንደ መሪ ነው የሚናገሩት”
- “የያዙኝ፣ ያሰሩኝ፣ ይጠብቁኝ የነበሩት ሕወሓቶች ብቻ ናቸው”
- “ለአንድ ዓመት ያህል የት እንዳለሁ አላውቅም ነበር”

# አነጋጋሪውና ያልተሠማው፤ በአንዳርጋቸው አንደበት

በተለይ ለግዮን

ግዮን
ቅጽ 1 ቅዳሜ ግንቦት 25 2010 ዓ.ም



# አነጋጋሪውና ያልተሠማው፤ በአንዳርጋቸው አንደበት (በተለይ ለግዮን)

5

**ቀጣይ ዕትም ቅዳሜ ሰኔ 02 ይጠብቁን!**




**ቁጥር 7 ዕትም**

16 "የተሻለ ሕይወት መኖር እየቻለ በረሃ መግባቱን ሳስብ ይጨንቀኛል"
**እማዋይሽ አለሙ**

2 ‹ሽብርተኝነት›፣ በነጻነት አዋቂው አንዳርጋቸው ተበጣጠሰ! ቦሌ፣ ኦሎምፒያ በደስታ ተናጠች!)
**ኤልያስ ገብሩ (ጋዜጠኛ)**

11 "ሀገሪቱ እየተመራች ያለችው በአዋጅ እንጂ በሕግ አይደለም"
**ብ/ጄነራል ተፈራ ማሞ**

12 "ጠ/ሚኒስትሩ የቂም በቀል ሰንሰለት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሰበረው ይመስለኛል"
**ስዩም ተሾመ**

14 የአንዳርጋቸው የአራት ዓመት የእስር ቤት ቆይታ ምን ይመስላል
**ክንፈሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶ)**

17 የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ አገታ

18 "አንዳርጋቸው የሚያደርገውን በትክክል ያውቅ"
**አቶ ፅጌ ሃብተማሪያም (የአንዳርጋቸው አባት)**

19 "እስኪፈታ ድረስ እንዳየው፤ እንድጠይቀው አልተፈቀለኝም"
**ወ/ሮ አይኔ ፅጌ / የአንዳርጋቸው እህት/**

20 "አንዳርጋቸው ቡድን መገንባትና መምራት የሚችል ፖለቲከኛ ነው"
**ብርሃኑ ተክለያሬድ**

21 "የአንዳርጋቸው ጥያቄዎችና ፍላጎቶች የኔ ጥያቄዎች፣ ፍላጎቶች ናቸው"
**ሸዋቀና አባትነህ**

22 "እግሩ ስር ወድቄ ረጅም ሠዐት መነሳት ተስኖኝ ነበር"
**እየሩሳሌም ተስፋው**

23 አንዳርጋቸው ጽጌ…."ለወገኑ ነጻነት፣ ነጻነቱን ተነፍጎ የኖረ ነጻ አውጪ"
**ታምራት መርጊያ**

24 አንዳርጋቸው ፅጌ - የገብርኤሉ መንገድ ካህን
**ግርማ ሠይፉ ማሩ**





ኤልያስ ገብሩ
(ጋዜጠኛ)

# ‹ሽብርተኝነት›፣ በነጻነት አዋቂው አንዳርጋቸው ተበጣጠሰ!
## (ቦሌ፣ ኦሎምፒያ በደስታ ተናጠቹ!)



ስለታጋዩና ፖለቲከኛው አንዳርጋቸው ጽጌ ለማጻፍ ‹‹ከየት ልጀምር?፣ ከየቱስ ጀምሬ የቱ ጋር ልቋጭ? …›› በሚለው ሀሳብ ውስጤ መናጡ አልቀረም:: ስለአንዳርጋቸው የትግል እንቅስቃሴ በዝርዝር የሚያጽፉ አንኳር ርዕሦ ጉዳዮች እጅግ ብዙ መሆናቸውን አምናለሁ:: የአንዳጋቸው የፖለቲካ ጉዞ ብዙ መጽሃፎችንም ያጽፋል:: እኔም በዚህቺ የፍጥነት ጽሑፍ ከአንዳርጋቸው ፍቺ ጋር በተያያዘ ከባለፈው ቅዳሜ (ግንቦት 18 ቀን 2010 ዓ.ም) ጀምሮ እስከ ማክሰኞ (ግንቦት 21 ቀን 2010 ዓ.ም) ድረስ በግል ባየሁትና ባስወዋልኳቸው ነገሮች ላይ ማተኮርን መረጥኩ::

### ዕለተ-ቅዳሜ

አርብ (ግንቦት 17 ቀን 2010 ዓ.ም) አመሻሽ ላይ አንዳርጋቸው ጽጌን ጨምሮ ሌሎች እስረኞች እንደሚፈቱ መወሰኑ በአገዛዙ ሚዲያዎች ተሰማ:: ሁላችንም ደስታ ተሰማን፤ ጻፍንም:: ቅዳሜ ጠዋት ረፋድ ላይ ‹‹አንዳርጋቸው ጽጌና ሌሎች ከ500 በላይ የሚሆኑ እስረኞች ተፈቱ›› የሚል ይዘት ያለው ዜና በፋና ብሮድካስቲንግ ፖርፖሬሽን ድረ-ገጽ ላይ ተነበበ:: ዜናውን ወዲያው ብዙ ሰው ከሀገር ውስጥ እስከውጪ ድረስ ተቀባበሉት:: ፋና ብዙም ሳይቆይ የዜናውን ርዕሥ ‹‹…እንዲፈቱ ተወሰነ›› በሚል አስተካከለው:: በቀድሞ የአንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ንቁ ተሳታፊ በነበረውና አሁንም በማኅበራዊ ሚዲያ በድፍረት ሀሳቡን በሚያራምደው ስንታየሁ ቸኮል የተመራው ግብረ ሀይል ወደቃሊቲ ገሰገሰ:: ስንታየሁ ቃሊቲ አከባቢ ስላሉ መረጃዎች በፍጥነት ያደርስን ነበር:: ▶

እኔና እሱም በስልክ መረጃዎችን ስንለዋወጥ ነበር:: ከሰዓት በኂላ፣ የአንዳርጋቸው ጽጌ ወላጅ አባት አቶ ጽጌ ሀ/ማርያም ወደቃሊቲ እስር ቤት አምርተው ወደውስጥ በመግባት ስለልጃቸው ፍቺ ጠየቁ:: የቃሊቲ እስር ቤት ሃላፊዎችም ‹‹እኛው ራሳችን ቤት ድረስ እናመጣዋለን፤ እርስዎ ወደቤት ተመለሱ›› እንዳሏቸው ሰማን::

## የአቀባበል ዝግጅት

በእነአንዳርጋቸው ቤተሰብ መኖሪያ ቤት የአሁኑ ሰማያዊ እና የቀድሞ ሰማያዊ ፓርቲ፣ የቀድሞ የአንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ንቁ አባላትና አመራር እንዲሁም በቅርቡ ከእስር የተፈቱት ብርሃኑ ተ/ያሬድ፣ እየሩሳሌም ተስፋውና መምህርትና ጸሃፊ መስከረም አበራ በፈቃደኝነት ያዋቀሩት አንዳርጋቸውን በክብር የሚቀበል ቡድን የደመቀ ዝግጅቱን ማጠናቀቁንና አንዳርጋቸውን በማንኛውም ሰዓት ለመቀበል መዘጋጀቱን የአንዳርጋቸው ምስል ያለበትንና ጀግንነቱን የሚገልጽ ካናቴራ በመልበስ ከወላጅ አባቱና ከአክስቱ ጋር ሆነው ፎቶግራፍ ተነስተው በማኅበራዊ ሚዲያ አሰራጩ:: አንዳርጋቸው በዚያን ዕለት ባይፈታም ይኼ አንዳርጋቸውን የሚቀበል ወጣት እዚያው ቦሌ ኦሎምፒያ አከባቢ በሚገኘው መኖሪያ ቤት ማደራቸውን ገለጹ:: መረጃዎችን ቶሎ ቶሎ ያደርሱ ነበር::

## ሰንበት

በዕለተ እሁድም አንዳርጋቸው ሊፈታ ይችላል በሚል ከጠዋት እስከማታ ድረስ ብዙ ሰው በተስፋ ሲጠብቅ ዋለ፣ አመሸ:: እነስንታየሁም ቃሊቲ በር ጋር በዚህ ቀን መሄዳቸው አለቀረም:: የተለወጠ ነገር ባይኖርም:: አንዳርጋቸው በሁለት ቀናት ውስጥ ከእስር ተፈትቶ ከእንግሊዝ ከቤተሰቡ ጋር እንደሚቀላቀል የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለአንዳርጋቸው ባለቤት በስልክ ደውሎ መናገሩን ከስካይ ኒውስ መረጃ ለመረዳት ተቻለ:: የአጭር ደቂቃ የቪዲዮ ቃለ ምልልስ ከአንዳርጋቸው ባለቤትና ከልጆቹ ጋር የተደረገው በተለያዩ ሚዲያዎች ተሰራጨ:: ከዚህ መረጃ በኂላ ‹‹አንዳርጋቸው የእንግሊዝ ዜግነት ስላለው በቀጥታ ወደእንግሊዝ ነው የሚላከው›› የሚለው ሀሳብ ሚዛኑን ደፋ::

## ሰኞ፣ ግንቦት 20

ሰኞ በጠዋት በረከት ዓለሙ ከሚባል ጓደኛዬ ጋር ተቀጣጥረን ወደቃሊቲ አመራን:: ስንታየሁ ቸኮል አንዳርጋቸው ይፈታል ከተባለበት ቀን ጀምሮ ከጠዋት እስከማታ ድረስ ቃሊቲ በር ጋር ከሌሎች ጓዶቹ ጋር በመሆን በንቃት ሲጠባበቅ ነበር:: በዚህ ቀንም ስንታየሁና ሌሎች የትግል ጓዶቹ ቀድመው ተገኝተው ነበር:: በዛ ያሉ ቪ-8 መኪኖች ወደቃሊቲ እስር ቤት ሲገቡ በማትየና ፎቶግራፎች ጭምር በማንሳትም በማኅበራዊ ሚዲያ መረጃዎችን ሲያጋረን ነበር:: ከስንታየሁ ጋር በስልክ እየተነጋገረን እኛም ቃሊቲ ደረስን:: ቃሊቲ እስር ቤት በር ፊት ለፊት በዛ ያሉ ሰዎች ተሰብስበው ነበር:: ከአንዳርጋቸው እህት ኑኑ ጽጌ ጋርም ከዓመታት በኂላ በአካል ተገናኘን:: አባትየው ከዚህ ቀደም ‹‹መንግስት ለመገልበጥ አሲረዋል›› በሚል ክስ በእነብርጋድየር ጄኔራል ተፈራ ማሞ የክስ መዝገብ ታስረውና ተከስሰው የዕድሜ ልክ ፍርደኛ የነበሩ ሲሆኑ ከኑኑ ጋር ፍርድ ቤት እንጋኝ ነበር:: አባትየውም ከጥቂት ዓመታት እስር በኂላ ከእስር ተፈትተዋል::

በቃሊቲ ሰው ቀስ በቀስ እየጨመረ መጣ:: እኛም ቆመን ሁነቱን እየተከታተልን በመጠበቅ በሀገራዊ ጉዳይ ላይ መወያትና መከራከር ቀጠልን:: ጸሃይዋም ከርራለች:: ጸሃይ ላይ መቆሙም ድካም ሲያመጣ ቡና ለመጠጣትና ለማረፍ ብለን ክራውን ሆቴል ገባንና ጨዋታችንን ቀጠልን:: በግምት ከ45 ደቂቃ በኂላ፣ ቃሊቲ የገቡት መኪኖች ወጡ ተባለ:: እኔና በረከት በበረከት ቪትስ መኪናም መኪኖቹን ለመከተል ጥረት አደረግን:: በመኪኖቹ ውስጥ አንዳርጋቸው ይኑርበት አይኑርበት ግን የምናውቀው ነገር አልነበረም:: መኪኖቹም መጠነኛ ርቀት ስለነበራቸው ከተወሰነ ርቀት በኂላ ተሰወሩብን:: ‹‹እቤት ሊወስዱት ይችላሉና ወደቤት መሄዱ ይሻለናል›› በማለት ከበረከት ጋር በቦሌ መስመር ነጎድን:: በቦሌ ሚሊኒየም አደባባይ አከባቢ ወጣቶች በሞተር ብስክሌትና በመኪና ከኂላ መጥተው በጥሩንባ አከባቢውን አነቃነቁት:: ደስ የሚል ትዕይንት ነበር:: እስከኦሎምፒያ አደባባይ ድረስ መኪኖችና ሞተር ብስክሌቶች በጥሩንባ፣ ወጣቶች በድፍረት ዝማሬና የአንዳርጋቸውን ስም በጀግንነት በማንሳት እየጨፈሩ በአይኔ አየሁ:: በረከትም የመኪናውን ጥሩንባ እያሰማ ወደቤት አከባቢ ደረስን:: አከባቢው እጅግ በበዛ ሰው ተከብቧል:: ሰው የአንዳርጋቸውን መፈታት በደስታ፣ በተስፋና በትዕግስት እየተጠባበቀ ነበር:: አንዳርጋቸው ግን አሁንም አልመጣም:: ‹‹የት ወሰዱት?››፣ ‹‹ኤምባሲ ወስደውት ነው:: ከዚያ እዚህ ያመጡታል››፣ ‹‹ቤተመንግስት ነው››፣ ‹‹እንግሊዞች የጤና ምርመራ እንዲደረግለት ሆስፒታል ወስደውታል››፣ ‹‹ከቃሊቲ አልወጣም››፣ ‹‹ወደእንግሊዝ ማታ እንዲበር የጉዞ ፕሮሰስ እያደረጉለት ይገኛል››፣ ‹‹እዚህ ሳያመጡት ቀጥታ ማታ ወደእንግሊዝ ይልኩታል››፣ ‹‹ከዐብይ አህመድ (ዶ/ር ጋር ተገናኝቷል›› ….ወዘተ የሚሉ መላምቶች በተለያዩ ሰዎች አንደበት ሲገለጽ ዋለ:: ‹‹አሁን ሊመጣ ነው ተዘጋጁ›› የሚልም መልዕክት ወደአመሻሽ አከባቢ መጣና በርካታ ሰዎች በተለያዩ አነቀቂ ሃገራዊ እና የአንዳርጋቸው ጽጌ የግንቦት ሰባት የትግል መዝሙር [‹‹ላንቺ ነው ሀገሬ›› የሚለው]) በመኖሪያ ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በደስታ ይጨፍሩ ጀመር:: ግቢው በደስታ ቀለጠ:: ዘናቡ መዝነብ ቢጀምርም በዝናብ ውስጥ ወጣቶች በደስታ ከመጨፈር አላገዳቸውም:: ዝናቡ ሲበዛ ብዙ ሰው መጠለያ ወደመፈለግ መጣ:: ሆኖም ሳይጠለሉ ዝናቡ እስኪያባ ድረስ በመዝፈንና በመጨፈር የቀጠሉ ብርቱ ወጣት ወንዶችና ሴቶች ነበሩ::

> ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላም በድጋሚ ጃኖ ለብሶ ንግግር ሊያደርግ አንዳርጋቸው ከቤት ወጣ:: በስንት ትግል ሰውን አልፎ ፎቅ ላይ መጥቶ ቆመ:: እዛም ላይ ሆኖ አድናቂዎቹን ወደታች ሰላም ይል ጀመር፤ በዚህ ጊዜ ፊቱ በደስታ ተሞቷል:: ….<<ላንቺ ነው ሃገሬ>> የሚትለዋ መዝሙርን እንዴት ሊደርሳት እንደቻለ እንባ እየጠናነቀው ትርክቱን ገለጸ:: ከንግግሩም በኋላ ለአራት ዓመታት ተመላልሰው በጠየቁት በወ/ሮ ታደለች ታዬ በኩል 18 ግራም የወርቅ ሃብል ተበረከተለት:: ጭፈራው፣ ፌሽታው ደራ

በዚህ ዶፍ ዝናብ ውስጥ እየተደበደቡ ባንዲራ ይዘው አንድ አርበኛ ወደግቢው ዘለቁ:: የሚጨፍሩ ወጣቶች አይተዋቸው ደስ በሚል ሁኔታ ወደእኚህ አዛውንት ሄዱና አቀፏቸው:: አብረዋቸውም ጨፈሩ:: እኚህ ሰው፣ ቁጭ ሲሉ አጠገባቸው ሄጄ አነጋገርኳቸው:: ቀኝ አዝማች አለባቸው ሃይሌ ይባላሉ:: በጎጃም ክ/ሀገር በጎንቻ እነሴ ወረዳ ልዩ ስሙ እነገት በሚባል ቦታ ተወልደው በአርበኝነት ብዙ ሀገራዊ ተግባራትን ለሀገራቸው ያበረከቱ መሆናቸውን ነገሩኝ:: በእጃቸው የያዙትንም ዶክመንቶች እያወጡ አሳዩኝ:: አዛውንቱ የአንዳርጋቸው ጽጌን ፍቺ ዜና ሰምተው የመጡ ናቸው:: የአያትታቸው፣ የአባታቸውንና የራሳቸውን የአርበኝነት ሜዳሊያ አድርገዋል:: አንዱን ሜዳሊያ በእጄ ይገዬ ሳየው ‹‹ድል የትግል ውጤት ነው›› ይላል:: እውነት ነው፣ ድል የትግል ውጤት ነው:: የአንዳርጋቸው ፍቺም የሁላችንም የሀገር ልጆች የትግል ውጤት ነው፤ የህዝብ ትግል! በግሌ፣ አንዳርጋቸው ከየመን ተይዞ (ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ.ም የዛሬው የአገዛዝ ሥርዓት ተላልፎ መሰጠቱ በግልጽ በታመነ ቀን፣ በአንዳርጋቸው መታሰር እጅግ ማዘኔን በማኅበራዊ ሚዲያ ጽፌ ነበር:: በተለያዩ ጊዜያትም ‹‹አንዳርጋቸው ጽጌ የነጻነት ታጋይ እንጂ አሸባሪ አይደለም!›› በማለት በግልጽና በድፍረት ጽፌያለሁ:: በሀገር ውስጥ ያሉና የደፈሩ ሌሎች በርካቶችም ስለአንዳርጋቸው ጽጌ የሚምኑበትን ሀሳብ በድፍረት ጽፈዋል:: እንዲፈታም በጽኑ ወትውተዋል::

እኚህ አርበኛ እንዴት ሊመጡ እንደቻሉ ጠየኳቸው:: ‹‹ጠንካራ ወገኔ ይፈታል ሲባል ደስ ብሎኝ መጣሁ!›› ብለውኛል:: … በእነአንዳርጋቸው መኖሪያ ቤት እስከምሽት ድረስ ጭፈራው ደርቶ ነበር:: ይሄም በአባይ ሚዲያ በቀጥታ ሲተላለፍ የነበረ ሁነት ነው:: እኔም የጭፈራ ጽዋ ደርሶኝ ትንሽ ጨፍሬያለሁ:: ‹‹ጭምት ናቸው፣ አይጨፍሩም›› ብዬ ያሰብኳቸው ሰዎች ጭምር ጭፈራቸውን በደስታ ሲያደሩ ተመልክቼም ከልቤ እየሳኩ በግርምት ተመልክቻለሁ:: እንዲህ ነው እንግዲህ ….አንዱ የአንዳርጋቸው አቀባበል! በዚህ በግንቦት ሃያ ቀን ግንቦት 7 አሸነፈ የምትለዋ አገላላጽም አይረሴ ናት::

## ማክሰኞ - የፈቺ ቀን

ሰኞም ከእስር ተፈትቶ መውጣት ያልቻለው አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ እሱን ጨምሮ ሌሎች ከ500 በላይ እስረኞች እንደሚፈቱ በገዥው ሃይል በኩል በጠዋቱ መረጃ ወጥቶ በትዊተር ላይ መገለጹን ከጋዜጠኛ መስፍን ነጋሽ የፌስ ቡክ ገጽ ላይ አነበብኩ:: ተስፋ ያልቆረጠው ሕዝብም በዚህ ቀን የአንዳርጋቸውን መፈታት በመጠባበቅ ከጠዋት እስከማታ ድረስ በመኖሪያ በቤቱ ከተመ:: እህቱ ወ/ሮ ኑኑም ‹‹አንዳርጋቸው ዛሬ ተፈትቶ እቤቱ ይመጣል፤ እርግጠኛ ነኝ›› የሚል ምላሽ ሰጥታን ነበር:: በቤቱ ውስጥ ድንኳን ተደኩኖ ሰዎች በሥነ-ሥርዓት ተቀምጠው ምሳም በሉ:: ቀትር አልፎ የከሰዓቱ ጊዜ መንጎድ ሲጀምርም ብዙ ሰው ግራ የመጋባት ስሜት ተፈጥሮበት ነበር፤ እኔን ጭምር:: ግቢሱ ይጨፍራል:: ገሚሱ ግቢውን በቂጠማ ያሳምራል፣ ገሚሱ አበባ መንገድ ላይ ይበትናል:: ገሚሱ ይቀመጣል፣ ገሚሱ ይንቆራጠጣል:: ገሚሱ ከሞባይል ስልኩ ጋር ተፋጥጦ ስልኩን ይነካካል:: ገሚሱ ቡና ለመጠጣት ላይ ታች ይላል:: በተስፋ ውስጥ ያለ ድካምና መጠነኛ መሰለቸትም ትንሽ በማይባሉ ሰዎች ዘንድ በጉልህ ይታይ ነበር:: ይኼም



◀ገኘሁውን ሃይል ካለማመን የመነጨ ነው:: ከቀኑ 10፡15 ሰዓት በኋላ እህቱ ከቤት በመውጣት መንታ መንገድ ላይ ቆማለች:: በንቁ አስተያየት የአንዳርጋቸውን መምጣት እየተጠባበቀች መሆኑ ፊቷ ላይ ይነበብባታል:: ሌሎች ሰዎችም ወደመንገዱ መጥተው መቆማቸው ቀጠለ:: ብርሃኑ ተ/ያሬድም መንገድ ላይ ለተሰበሰቡ ሰዎች ‹‹አንዳርጋቸው ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላ ይመጣል›› ብሎ ተናገረ:: ትንሽም ጭፈራ መንገዱ ላይ ተደረገ:: እኔም ሰዓቴን ሳየው 10፡45 ሆኗል:: ‹‹ማምጣት ካለባቸው እንዴት እስከአሁን ይቆያል?›› በማለት አጠገቤ ለነበሩት የዞን 9 ጦማሪያን አቤል ዋባላ እና አጥናፍ ብርሃኔ ነገርኳቸው::

## ፈጁቸው!

ወዲውም አንዲት አንቡላንስ በፍጥነት ወደተሰበሰበው ሰው ድረስ መጥታ አለፈች:: መኪናዋን የጠረጠሩ ሰዎች ግን አንቡላንሷን ጠጋ ብለው ተመለከቱ:: አንዳርጋቸውን አዩት መሰለኝ፣ ‹‹አንዲ …አንዲ …ጀግናው መጣ … ጀግናው መጣ …›› በማለት በሩጫ ተከተለት:: በተለይ አንቡላንሷ ወደእነአንዳርጋቸው ቤተሰብ መኖሪያ ቤት ስትጣጠፍ፣ ህዝቡ እየጮኸ መሮጡን ቀጠለ:: እኔም በአቅራቢው ነበርኩና ሮጥኩ:: እውነት ነበር፣ አንቡላንሷ በር ላይ ቆማለች:: መኪናው በህዝቡ ተወረረ:: ተኩስ የሚመስል ድምጽ ይሰማም ጀመር:: ርችት መሆኑ ገባኝ:: ርችቱ እንደጉድ ተንጣጣ::[ራሄል ረጋሣ የምትባል አንድ ጓደኛዬም ወደስፍራው እየመጣች ነበርና ከርቀት የርችቱ ድምጽ የተኩስ ድምጽ መስሏት ‹በቃ ፈጁቸው!› ብላ በድንጋጤ መብረክረኳን ምሽት ላይ በስልክ ነግራኝ በሳቅ ሞቻለሁ::] አከባቢው በጩኸትና በጭፈራ፣ በትርምስምስ ተደበላላቀ:: ማንም ሰው ማንንም አይሰማም:: ሁሉም ስሜቱን ነበር የሚከተለው:: መኪናዋ ሙሉ በሙሉ በሚጨፍሩ፣ አንዳርጋቸውን በሚያወድሱ፣ በሚጮሁና በበደስታ በሚያለቅሱ ሰዎች እንደታይታኒክ መርከብ ሰጠመች::

ወደግቢው ገብቼ በአንዱ ነጻ ቦታ ላይ ቆሜ ትዕይንቱን በቅድሚያ በፎቶግራፍ፣ ቀጥሎ ደግሞ በፌስቡክ የቀጥታ ስርጭት በመቅረጽ ማስተላለፉን ተያያዝኩት:: ዶፍ ስናብም ይዘንብ ጀመር:: ዝናቡ የአንዳርጋቸውን አድናቂዎች አልበገረም:: የሚጨፍረውም ይጨፍራል:: በሰው መተረማመስ የወደቁና የተጎዱ ሰዎች ነበሩ:: ጭፈራው ደርቷል፣ ዝናቡም ይወርዳል:: አንቡላንሷ ወደግቢው ልትገባ ጥረት አደረገች:: ግን እንዴት ተችሎ? በስንት ትግል ግን አንዳርጋቸውን ከመኪናው አውርደው፣ አቅፈውና ተሸክመው በድንኳኑ ውስጥ ወጣቶች ይዘውት መጡ:: እኔም ለመጀመሪያ ጊዜ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን አየሁት:: አቀባበሉን በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ በስልኬ ቀጥታ እያስተላላፍኩ ቢሆንም አንዳርጋቸውን ለመመልከት ጥረት አደረኩ:: አንዲ፣ ወጣቶች ላይ ተኝቷል:: ግራ ተጋብቷል፤ ፊቱ ላይ ግን የደስታ ስሜቱ በጉልህ ይታያል:: ጉልበተኛ ወጣቶች በስንት ትግል የሰውን ግርግር አልፎ ወደቤት አስገቡት:: ጥቂት ሰዎችም ከእርሱ ጋር ገብተው በሩ ተዘጋ:: ዝናቡ ይዘንባል:: መቆም አልቻለም:: ብዙ ሰው የሚጠለልበት አልነበረውም:: እኔም እንደምንም አንዲት ጠባብ ክፍል በር ላይ መቆም ቻልኩ:: እዛም ላይ ሆኜ ሁነቱን ለመቅረጽ በትንሹ ረድቶኛል:: ግቢው ትምምስምር ብሏል::

## የአንዳርጋቸው ንግግር

ከቆይታ በኋላ፣ ‹‹አንዳርጋቸው ሶስት ደቂቃ ያህል መናገር ስለሚፈልግ ሥነ-ሥርዓት እንያዝ›› የሚል መልዕክት ከአስተባባሪዎች ተሰማ:: በቦታው ግን ሥነ-ስርዓትን ለማስፈን እጅግ ፈታኝ ነበር:: ከደቂቃዎች ትግልና መገፋፋት በኋላ አንዳርጋቸው ለሚጠበቀው ብዙ ሰው ሊናገር ወጣ:: አሁንም ትርምሱ ቀጠለ:: አንዲት እናት ጎን እንደምንም አስቀመጡት:: እዚህ ጋር አንዳርጋቸው በሁነቱ እጅግ ተገርሞ እጁን በአፉ ያዘ:: አንድ ወንበር ላይ እንዲቆም ተደርጎም ጥቂት ንግግሮችን አደረገ - ደስታም እንባም መገረምም ተደበላልቆበት:: ትንሽ ከተናገረ በኋላ፣ እድምተኛው ያጨበጭባል፣ አድናቆቱንም ይገልጻል:: ‹‹አንዴ ዝም በሉ!›› ይባልና በድጋሚ ይናገራል፣ ተመሳሳይ ነገር ይከሰታል:: አንዳርጋቸው፣ በንግግሩ እንዲህ አይነት አቀባበል እንዳልጠበቀ፣ በዚህ በጣም መገረሙንና በጣምም ሁሉንም ማመስገኑን ገለጸ፡ ፡…ከንግግሩ በኋላም በድጋሚ ወደቤቱ ገባ:: ተመሳሳይ ትርምስ ተከተለ:: ‹‹ላንቺ ነው ሃገሬ›› የሚለው እሱ የደረሰው የትግሉ መዝሙርም ተከፈተ:: ድጋሚ ተቋረጠ:: ….የፕሮግራም መናበብ ችግር በጉልህ ታይቷል፤ ያው ደስታ የፈጠረው እና የዝናቡ ክብደት መሆኑ ባይዘነጋም::

## አንዳርጋቸው በጃኖ!

ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላም በድጋሚ ጃኖ ለብሶ ንግግር ሊያደርግ አንዳርጋቸው ከቤት ወጣ:: በስንት ትግል ሰውን አልፎ ፎቅ ላይ መጥቶ ቆመ:: እዛም ላይ ሆኖ አድናቂዎቹን ወደታች ሰላም ይል ጀመር፤ በዚህ ጊዜ ፊቱ በደስታ ተሞቷል:: ….‹‹ላንቺ ነው ሃገሬ›› የሚትለዋ መዝሙርን እንዴት ሊደርሳት እንደቻለ እንባ እየጠናነቀው ትርክቱን ገለጸ:: ከንግግሩም በኋላ ለአራት ዓመታት ተመላልሰው በጠየቁት በወ/ሮ ታደለች ታዬ በኩል 18 ግራም የወርቅ ሃብል ተበረከተለት:: ጭፈራው፣ ፌሽታው ደራ:: በመጨረሻም አንዳርጋቸው ‹‹እኔም ቤተሰብን ላግኝ፣ አባቴንም አላገኘሁትም:: እናንተም ደክሟችኋል እረፉ:: ለተወሰኑ ቀናት እዚህ ስላለሁ ተረጋግተን እንገናኛለን::›› የሚል ይዘት ያለው መልዕክት አስተላለፈና ህዝቡን በደስታ ተሰናበተ:: አንዳርጋቸውን ለመቀበል የመጣው ሰው ቁጥሩ ጨመረ እንጂ አልቀነሰም::

ከፎቁም ወርዶ ሰዎችን እየጨበጠ በደስታ ሰላምታ መስጠቱን ቀጠለ:: ከቢቢሲ ጋርም ጥቂት ቃለ-ምልልስ አደረገና ድጋሚ ወደቤት ገባ:: በቤት ውስጥም ከአባቱ ጎን ተቀምጦ ከተለያዩ ሰዎች ጋር የማስታወሻ ፎቶግራፍ ደስ ብሎት ይነሳ ጀመር:: አንዳርጋቸውን ሰው ጋብ ካለም በኋላ ሰውን ሰላም በማለት፣ የማስታወሻ ፎቶግራፍ በመነሳትና ስልክ በማነጋገር ሲስቅ እና ሲጫወት እስከምሽቱ አራት ሰዓት ድረስ አይቸዋለሁ:: እኔም በኩል ኢሳት ውስጥ ከሚሰሩ ጋዜጠኞች ጋርም በስልክ አገናኝቼው መኝታ ክፍል ውስጥ ገብቶ እየሳቀ ጭምር ሲያነጋር ነበር:: ….የፍቺው ቀን ሁነት ምሽቱ ይሄንን ይመስል ነበር::

ከአንዳርጋቸው ፍቺ የተረዳሁት ነገር፣ ሰፊው ህዝብ እውነተኛ ነጻነትን፣ ዴሞክራሲን ፣ ፍትህን፣ እኩልነትን፣ …እጅጉን በተግባር መሻቱን ነው:: ለዚህ እውን መሆኑ አንዱ አሸባሪ ተብለው ተፈረጁ ድርጅቶች (ግንቦት 7፣ ኦነግና ኦብነግ) ከአሸባሪነት ዝርዝር ውስጥ ስማቸው በተግባር መነሳት አለበት:: ብዙ ኢትዮጵያዊ ዜጎችንና ሀገሪቷን ዋጋ ያስከፈለውና እያስከፈለ የሚገኘው የጸረ-ሽብርተኝነት አዋጁም ይሻር:: ወይም ብዙሃንኑ ዜጋ በሚያጠቃ ሳይሆን በሚጠቅም፤ የአገዛዙን ዕድሜ በሚያራዝማ ሳይሆን ለሁሉም ዜጎች ጥበቃ ሊሆነድ በሚችል መልኩ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በሚስማሙበት ደረጃ መሻሻል ይኖርበታል:: ጠላት-ተኮር የፍረጃ ፖለቲካ ያክትም:: በጸረ-ሽብርተኝት አዋጁ ዋጋ መክፈል ይብቃን! ህዝብ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ብቻ የዴሞክራሲያዊ የሥልጣን ባለቤት ይሁን!

## ኢትዮጵያ!


## ግዮን መጽሔት

**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**
**በየ 15 ቀኑ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

ማኔጂንግ ዳይሬክተር
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

ዋና አዘጋጅ
ፍቅር ሠይድ
አድራሻ፡- አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 7
የቤት ቁጥር 314

አዘጋጆች
ሮቤል ምትኩ
ብሩክ መኮንን

አምደኞች
አበባው አያሌው
ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ
ተረፈ ወርቁ
መስፍን ጌታቸው
ሁሴን ከድር
በሀይሉ ገ/እግዚአብሔር
ሠሎሞን ለማ

ክርኤቲቭ ዲዛይን
ሀብታሙ መኮንን

የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09
የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 5ተኛ
ፎቅ ቢሮ ቁ. 501
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 951693
ኢ-ሜይል፡
Gihon2010meg@gmail.com
Facebook
Gihon-meg Fekadu

አታሚ
ሰለሞን፣ ከበደና ጓደኞቹ ኅትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማ
አድራሻ
ክ/ከተማ ን/ስ/ላ፣ ወረዳ12
የቤት ቁጥር 1876
ስልክ ቁጥር 0911 77 15 56
0909 54 83 30





# አነጋጋሪውና ያልተሠማው፤ በአንዳርጋቸው አንደበት

## (በተለይ ለግዮን)

በ1985 ዓ.ም ላይ "አካሄዳችሁ ልክ አይደለም" በሚል በስብሰባ ላይ የጊዜውን የኢህአዴግ ባለሥልጣናት በአደባባይ ነግሯቸው ወደ መጣበት ሀገረ እንግሊዝ የተመለሰው የቀድሞው የኢህዴን አባል፤ በ1997 ዓ.ም የቅንጅት አባል ሆኖ ተመልሶ ወደ ሀገሩ በመምጣት የድርጅቱን ንቅናቄ መርቷል:: በጊዜውም አዲስ አበባና ዝዋይ ላይ ታስሮ ከፍተኛ በደል ተፈፅሞበታል:: አንዳርጋቸው በዛው አመት ከሕዝብ ዘንድ ያደረሰው "ነፃነትን የማያውቅ ነፃ አውጭ" የተሰኘ መጽሐፍ ከፍተኛ ተወዳጅነትን ማግኘቱ ይታወሳል::

ኢህአዴግ መራሹ መንግስት በዜጎች ላይ የሚያደርሰውን ግፍና በደል ለአመታት በፅኑ ሲቃወም የነበረው አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ድርጅቱ ግንቦት ሰባት ጨቋኙ ሥርዐት የሚወድቀው የትጥቅ ትግልን ጨምሮ በሁለገብ የትግል ስልት ነው ብሎ በማመኑ እሱም በዕድሜ ማምሻው ላይ ኤርትራ በርሀ ወርዷል::

"ትግሉ ፈታኝ ቢሆንም ከሀገርና ከህዝብ የሚበልጥ የለም" የሚለው አንዳርጋቸው ፅጌ ለሌሎች የነፃነት ታጋዮች ራሱን አርአያ ለማድረግ ከግንቦት ሰባት የመጀመሪያዎቹ አስራ ዘጠኝ አባላት አንዱ በመሆን እልህ አስጨራሽና ፈታኝ እንደሆነ የሚነገርለትን የኤርትራ በርሀ የሚኖርባትን አውሮፓዊቷን እንግሊዝ ትቶ ተቀላቅሏል:: በበረሀ ቆይታው ለሁሉም ቀድሞ ታድሎ የነበረው ከሸራ የተሰራ መኝታ ታድሎ ነበር:: ትግሉን የሚቀላቀል አንድ ሰው ሲመጣ በቅድሚያ ለአዲሱ ሰው መተኛውን በመልቀቅ የሳር ፍራሽ ላይ ወርዶ የተኛውና ድርጊቱን ሌሎች በአርአያነት እንዲመለከቱት ያደረገው ይህ የምናወራለት አንዳርጋቸው ነው::

ስቃይና መከራ በበዛበት የኤርትራ በርሀ የግንቦት ሰባት የትግል ቆይታ በድርጅቱ ደንብ መሠረት እያንዳንዱ የሠራዊቱ አባል በአንድ ዙር ሁለት ጀሪካን ውሀ መቅዳት ያለበት ቢሆንም አንዳርጋቸው ፅጌ ግን በራሱ ተነሳሽነት ሁሌም በአስር ዙር 20 ጀሪካን ውሀ በመቅዳት ለወጣቶች ትልቅ ተምሳሌት ሆኖ ነበር::

ዕድሜው፣በድርጅቱ ውስጥ ያለው ሥልጣንና በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ያለው ከፍተኛ ተቀባይነት ሳይበግረው ተገቢውን ሥልጠና ከመላ የሠራዊቱ አባላት ጋር የወሰደው አንዳርጋቸው ፅጌ እሱም ሆነ ሌሎች የደርጅቱ መስራቾች በጋራ እንጨት የመፍለጥ፤ ወንዝ ተሻግሮ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ማምጣት፣ እንጀራ መጋገርና ሌሎች መሰል ተግባርን ደስተኛ ሆኖው አከናውነዋል::

ከአራት ዓመታት የእስር ቆይታ በኋላ የተፈታው ታላቁ የነፃነት ታጋይ አንዳርጋቸው ፅጌ በእስር ቆይታው ከሁለት ሰዎች ውጭ ማንም እንዳይጠይቀው የተደረገበትን ምክንያት፣ የመን ላይ የተያዘበት ሁኔታ፣ ለአንድ ዓመት ያህል ለቤተሰብም የት እንዳለ በማይታወቅ መልኩ ተሰውሮ የነበረበት ምስጢርና ሌሎችም ተዛማጅ ጉዳዮች ይፋ እንዲሆኑ ብሎም የፖለቲካው ዓለም ሰዎቻችንስ በእርሱ መፈታት ምን አይነት ስሜት አላቸው? ከሚል አኳያ የመጽሔታችንን ሙሉ ይዘት በአንዳርጋቸው ጽጌ ላይ አድርገን ይህንን "ልዩ ዕትም" አሰናድተናል::

ኦሎምፒያ ሸዋ ዳቦ አካባቢ ከሚገኘው የወላጅ አባቱ መኖሪያ ቤት የተገኘው የግዮን መጽሔት **ጋዜጠኛ ፍቃዱ ማ/ወርቅ** አንዳርጋቸው ፅጌን በሰፊው አነጋግሮታል:: ሌሎች የግዮን ጋዜጠኞችም በእርሱ ዙሪያ የተዘጋጀውን ልዩ ዕትም የተሳካ ለማድረግ በቂ መረጃዎችን አሰባስበዋል:: በሕይወት መኖሩ አጠራጣሪ በሆነበት ወቅት ወላጅ አባቱ፣ እህቱና ሌሎች የቅርብ ሰዎቹ ምን አይነት ስሜት እንደነበራቸው በዝርዝር አቅርበናል::

ከአንዳርጋቸው ፅጌ ጋር መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ ተንቀሳቅሳችኋል ተብለው ከተያዙትና 10ዓመት ከታሰሩት ብርጋዲየር ጀነራል ተፈራ ማሞና ወ/ሮ እማዋይሽ ዓለሙ ጋርም ቆይታ አድርገናል:: ከግንቦት ሰባትና ከሽብርተኝነት ጋር በተያያዘ ተጠርጥረው ከታሰሩና ከተፈቱ ፖለቲከኞች መሀል የተወሰኑትን አነጋግረናል:: በአንዳርጋቸው ፅጌ መፈታት ስሜት ቆስቋሿቸው የፃፉ ፖለቲከኞችንና ጦማርያንን መጣጥፍም አስተናግደናል:: ለሁሉም መልካም ንባብ ይሆንላችሁ ዘንድ ከልብ እንመኛለን::

በመጨረሻም አንዳርጋቸው ፅጌ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ቆይታ ካደረገ በኋላ ሀሙስ ምሽት ወደ እንግሊዝ ተጉዟል:: ▶



**ግዮን፡- አቶ አንዳርጋቸው እንኳን ደስ ያለህ፤ እንኳን ለቤትህ አበቃህ?**

**አንዳርጋቸው፡-** አመሰግናለሁ እንኳን አብሮ ደስ ያለን::

**ግዮን፡- ቆይታችንን ከአፈታትህ ብንጀምርስ?**

**አንዳርጋቸው፡-** ደስ ይለኛል::

**ግዮን፡- መቼና እንዴት ነበር መፈታትህን የሰማኸው?**

**አንዳርጋቸው፡-** ከመፈታቴ በፊት ስድስት ሣምንት ቀደም ብሎ ቴሌቭዥን ክፍሌ ውስጥ አስገቡልኝ:: ከዛ በፊት በነበሩኝ የእስር አመታት ቴሌቭዥን፣ ሬድዮም ሆነ ሌሎች የመገናኛ ብዙኃንን እንድከታተል አልፈቀዱልኝም፤ እድሉም አልተሰጠኝም ነበር:: ከጠቀስኩልህ ወዲያ ግን ቴሌቭዥን ስላስገቡልኝ የወቅቱን ሁኔታ፣ የአዲሱን ጠ/ሚኒስትር መመረጥና ወደ ሥልጣን መምጣት ማወቅ የቻልኩት በዚህ አጋጣሚ ነው::

ቅዳሜ ቀን ቤተሰቦቼ ሊጠይቁኝ የሚመጡት ሠባት ሠዐት ስለሆነ ከእነሱ ጋር በማደርገው ቆይታ የሠዐቱ ዜና ስለሚያመልጠኝ እስኪ የስድስት ሠዐቱ ዜና ምን ይላል? ብዬ ቴሌቭዥኑን ከፈትኩት፡ በጊዜው ዜና የለም፤ የሆነ ገፅ ዳሰሳ ነው፣ ግምገማ የሚል ፕሮግራም አለ፤ እዛ ላይ ጋዜጠኞች ከበው “ዛሬ ፌስ ቡክ (ማህበራዊ ድረ ገፅ) አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ እንዲፈቱ በሚል ጥያቄ ነው የተሞላው፤ በዚህ መሠረት አቃቤ ህግ ዛሬ በጉዳዩ ላይ መልስ ሰጥቷል፤ ለአቶ አንዳርጋቸውም ይቅርታ እንደተደረገላቸው አስታውቋል” ብለው ሲናገሩ ሰማሁ:: “እንዴህ ነው እንዴ?” ብዬ ነው ያዳመጥኩት::

**ግዮን፡- ይቅርታ እንደተደረገልህና እንደምትፈታ ስታውቅ ምን ተሰማህ?**

**አንዳርጋቸው፡-** ብዙም የተለየ ስሜት አልነበረኝም፤ ዝም ብዬ ዜና እንደማድመጥ ያህል ነው የሰማሁት:: እስኪ ቤተሰቦቼ ሊጠይቁኝ ሲመጡ እነሱን በደንብ እጠይቃለሁ ብዬ ተውኩት:: በኋላ እነሱም የነገሩኝ ሽገር ሬድዮኖች ጉዳዩን ሰምተው ደውለውላቸው ነበር:: ስለ ጉዳዩ ያውቃሉ እና አባቴ ብዙ ጊዜ ቁጭ ብሎ ነበር የሚያነጋግረኝ፤ የዛ እለት ግን ከውስጥ ብቅ ስል ከተቀመጠበት ብድግ ነው ያለው:: “ዛሬ እንዴት ነው ይሄን ሁሉ ኢነርጂ ያገኘኸው አልኩት?” ያው ዜናውን እኔም እንደሰማሁት ነገርኳቸው::

**ግዮን፡- ተፈትተህ እዚህ አሁን ያለንበት የአባትህ መኖሪያ ቤት ስትደርስ የነበረው ከፍተኛ የህዝብ አቀባበል እንዴት አየኸው?**

**አንዳርጋቸው፡-** በህዝቡ አቀባበል በጣም ነው የተገረምኩት:: እኔ ከማረሚያ ቤቱ ቀጥታ ወደ ቤት ይዘውኝ ሲመጡ አባቴ ስላልተነገረው ግቢ ውስጥ ሲንጎራደድ፤ እኔ በር ተከፍቶ ስገባ እንዳይደነግጥ የሚል ሃሳብ ገብቶኝ ነበር:: እየመጣሁ በነበረበት ጊዜ እዚህ ስደርስ ግን ሌላ ነው፤ መጀመሪያ ከላይ ጀምሮ ብዙ ህዝብ ስለነበር “ምንድነው ሰፈሩ ወደ መርካቶነት ተቀየረ እንዴ?” የሚል ነገርም መጥቶብኛል:: ኦሎምፒያ ከላይ ከሸዋ ዳቦ ቤት መገንጠያ አንስቶ ያለው መንገድ ሁሉ በህዝቡ ቢጨናነቅም ነገሩ አልገባኝም:: ወደ ቤታችን መዞሪያ ላይ ልደርስ ስል ባሉ ምልክቶች ነው ህዝቡ እኔን ለመቀበል እንደወጣ የተረዳሁት::

በጣም ይደንቃል:: ፈፅም ይሆናል ብዬ የማልጠብቀው ነገር ነው የሆነው:: በጣም የሚያስደሰትና የሚያኮራ አቀባበል ነው የኢትዮጵያ ህዝብ ያደረገልኝ፤ የህዝቡ ፍቅርና አክብሮት ልብ የሚነካ ነው:: እንዳህ አይነት ተዐምረኛ አቀባበል ይደረጋል ብዬ መቼም ቢሆን አስቤ አላውቅም::

**ግዮን፡- ቅዳሜ ዕለት እንደምትፈታ ተነግሮ ብዙ ህዝብ ቅዳሜና እሁድ ቢጠብቅህም ግልፅ ባልሆነ ሁኔታ እስከ ማክሰኞ እንድትቆይ ተደረገ በዛ መሃል መጥቶ ያነጋገረህ አካል ነበር?**

**አንዳርጋቸው፡-** ሰኞ ዕለት ጠዋት የእስር ቤቱ አስተዳደር ሲያነጋግረኝ “ችግር ገጥሞናል ወረቀቱ እኛ እጅ አልደረሰም፤ የአንተ ብቻ ሳይሆን ይቅርታ ተደርጎላቸዋል የተባሉት 500 እስረኞች ወረቀት እኛ ዘንድ አልመጣም:: እና እሱን እየጠበቅን ነው፤ እነሱ ከላኩልን በእኛ በኩል ለመልቀቅ ዝግጁ ነን” ብሎኝ ሄደ::

ከሠዐት በኋላ አንድ ወረቀት ይዞ መጥቶ “አሁን ሁሉ ነገር ስለደረሰን እዚህ ላይ ፈርም” አሉኝ፤ ግልባጩን ለእነሱ አስቀርቶ ነው መሠለኝ ነጠላ ወረቀቱን ሰጠኝ:: ከዛ ያው እንዳያችሁት ዛሬ ማክሰኞ በአምቡላንስ መኪና ተጭኜ ነው እዚህ ድረስ ያመጡኝ::

**ግዮን፡- በተፈታህበት ዕለት ምሽት ቤተሰቦችህን አግኝተሃል፤ ባለቤትህን፣ ልጆችህን ማለት ነው እንደው በአጋጣሚው ምን ተሰማህ?**

**አንዳርጋቸው፡-** በቪዲዮ ነው ያየኋቸው በጣም ትንንሽ ልጆች ሆነው ነበር የተለየኋቸው፤ እኔ ስታሰር ሠባት ዓመታቸው ነበር:: አሁን አስራ አንድ ዓመት ሞልቷቸዋል፤ ትልልቆች ሆነዋል በመፈታቴ በጣም ተደስተዋል:: እኔም ሳያቸው የተሠማኝ ስሜት ልዩ ነው:: ግንኙነታችን በጣም ቅርበት ያለው ስለነበር እርግጠኛ ነኝ በእስር ላይ በሆንኩበት ወቅት እኔን ሲያጡ በጣም እንደተጎዱ ይገባኛል:: አሁንም ደግሞ ለወንድሜ እያነሱለት ሥለሆነ” በጣም እንደፈሩ ድጋሚ እንዳያስሩኝ እንደሠጉ”እገዘባለሁ:: ስለዚህ አሁን ቅድሚያ ለእነሱ ሰጥቼ ሞራላቸውን ትንሽ ማስተካከል ያለብኝ ይመስለኛል:: ገና ልጆች ስለሆኑ በሥነልቦና እየተጎዱ ነው:: ግን በመፈታቴ ልዩ ደስታ ተሰምቷቸዋል:: እኔም በጣም ነው ደስ ያለኝ::

**ግዮን፡- ወደ ኋላ እንመለስ፤ ከየት ተነስተህ ወዴት ስትሄድና እንዴት ባለ አጋጣሚ ነበር የተያዝከው?**

**አንዳርጋቸው፡-** ከዱባይ ወደ ኤርትራ ለመሄድ የመን ላይ ነው የተያዝኩት:: እኔ በየመን አየር መንገድ የመሄድ ፍላጎት አልነበረኝም:: ምክንያቱም ችግር እንደሚመጣ አውቂያለሁ:: ቡክ አድርጌ የነበረው በኤርትራ አየር መንድ ነበር፤ ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም:: ግን የእኔን ብቻ አጣሞታል፤ ከእንግሊዝ አገር በላኩለት ሳይሆን ከ አንድ ወር ወደፊት አድግጎ ነው የበረራ ጊዜዬን የመዘገበው፡፤ የሌሎችን ግን በስነስርአቱ ነው የመዘገቡት፤” ከዚህ ውጪ ቦታ የለንም ፤”ፈርስት ክላስ ግን አለ ሲሉኝ ስንት ነው የምጨምረው? አልኳቸው ”400 ዶላር ከጨመርክ መሄድ ትችላለህ” አሉኝ::

ያኔ አራት ሺህ ዶላር በኪሴ ይዤለሁ ለስራ የሚሆን፤ ግን 400 ዶላር የድርጅት ገንዘብ በጭማሪ አላወጣም በሙስናህዝብ ▶



◀ በሚሰቃይበት አገር የድርጅት ገንዘብማ አላባክንም፤ ተጨማሪ ወጪ ይቅርብኝ፤ ርካሹ ይሻለኛል ብዬ ነው በየመን አየር መንገድ የተጓዝኩት::

**ግዮን፡- የመን ላይ የኢትዮጵያ የደህነንት ሰዎች እንደት ነበር የያዙህ?**

**አንዳርጋቸው፡-** የየመኑን በረራ ቡክ ካደረግኩ በኋላ ነው የበለጠ አደጋ ሊገጥመኝ እንደሚችል እየተሰማኝ የመጣው፤ ከዛ በፊት አንድ ጊዜም በየመን አየር መንገድ ተጉዣለሁ:: ግን በዛ ወቅት የነበረው የሀገሪቱ ሁኔታና የሁለተኛው ጉዞዬ ሁኔታ የተቀያየረ ለመሆኑ የተወሰነ ጥርጣሬ ስለነበረኝ በጉዞዬ ላይ የተወሰነ ስጋት ተሰምቶኛል:: እዛ አገር ላይም ቢሆን በአየር በረራውላይ ብዙ ኢትዮጵያዉያን ነው ያሉት:: በመሃሉ የኢህአዴግ ሰላዮቹና የመረጃ ሰዎች ይኖራሉ፤ የመን በጣም ሙሰኛ ሰዎች ያሉባት አገር ናት:: ለእነሱ ስንት ብር ከፈሏቸው? ለሚለው እግዜር ይወቀው::ከፍተኛ የውጪ ምንዛሬ በጉቦነት ሳይሰጥ አይቀርም፤ ከዚህ ውጪ በነፃ ምንም ነገር የመኖች እንደማያደርጉ ግልፅ ነው::

በዚህ አይነት መንገድ አውሮፕላን ማረፊያው ላይ ነው ደህንነቶች የጠበቁኝ፤ በረራው የመን ላይ ትራንዚት አለው፤ ሰንአ ወርጄ ነው እንደገና ወደኤርትራ የምበረው:: ገና ከአውሮፕላን እንደወረድኩ አንድ የየመን ሰው ልክ ማፊያ እንደሚያደርገው ተንደርድሮ መጥቶ እንደ ዘመድ ነው ተጠምጥሞ የሳመኝ ፤ ለተላኩት ሰዎች እንደመለያ ጥቆማ እያደረገ ነው ያኔ ሁሉ ነገር ገብቶኛል፤ ሰውዬው የየመን የደህንነት ሰው ነው::


ትንሽ ቆይቶ የራሳቸው ሰዎች መጡ:: እዛው ኤርፖርት ውስጥ በጣም ሚያስፈራ ቦታ አለ:: የመኖች ኤርፖርታቸው ግቢ ውስጥ እንደዛ አይነት ቆሻሻና የገማ ቦታ ይኖራቸዋል ብሎ ለማሰብየሚከብድ ቦታ ነው፤ ወደ ትራንዚት ለመሄድ አውቶብስ ውስጥ ስገባ ሌላውን አስቀርቶ ብቻዬን እኔን ገንጥሎ ወደ እዛ መጥፎ ቤት ወሰደኝ:: እዛ ቁጭ ባልኩበት የእዚህ አገር የደህንነት ሰዎች አውሮላን ይዘው መጡ:: በእቃ ማሸጊያ ትልቅ ፕላስተር አይኔንም፣ አፌንም አሸጉ፣ እጄን ወደኋላ በካቴና አስረው፣ ፊቴን በጆንያ ሸፍነው አስረው ነው ያመጡኝ::

**ግዮን፡- ስለእዚህ ለአንተ መያዝ ተባባሪው የየመን የደህንነት ሰዎች ናቸው ማለት ነው?**

**አንዳርጋቸው፡-** በትክክል:: አሳልፈው የሰጡኝ እነሱ ናቸው:: በጊዜው እኔ የመንን አልረገምኳትም ነበር:: ግን ከዛ በኋላ ብዙም ሳትቆይ የኢትዮትያን ህዝብ ረግሟታል መሰለኝ እንዲህ አይነት አስከፊ ችግር ውስጥ ገብታለች::

**ግዮን፡- ያኔ የየመን ደህንነቶች ለኢህአደግ ደህንነቶች አሳልፈው ሲሰጡህ፤ ከነበሩት ሰዎች መሃል የምታውቀው ሰው ነበር?**

**አንዳርጋቸው፡-** አንዱን የማውቀው ይመስለኛል:: ሌሎቹን ግን አይቻቸውም አላውቅም:: ይሄን በተመለከተ በጣም ሰፊና ዝርዝር ጉዳይ ወደፊት ለህዝቡ አወጣለሁኝ ብያለሁ:: ምክንያቱም በጣም ጠቃሚ የሆኑ ጉዳዮች ናቸው፤ እኔ ሁሌ የምታገልባቸውና መሆን አለባቸው የምላቸው ጉዳዮች ብዙ ናቸው:: ለአገር የሚበጅ፤ ለሁሉም ህዝብ የሚበጅ በሚሆንበት መልኩ የሚወጣበት




አጋጣሚ ይኖራል:: ሌላ ነገር ታስቦ ሳይሆን መገለፅ ያለበት ተዛማጅ ብዙ ጉዳይ ስላለው ነው::

**ግዮን፡- የደህንነት አባላቱ ብዛት ስንት ነበር?**

**አንዳርጋቸው፡-** አራት ናቸው:: እጄን ጠምዝዘው በብዙ መከራ ነው መኪና ውስጥ የገባሁት፤ በግብግቡ ጊዜ እጄን ሰብረውታል:: ያው ቀደም ሲል እንደነገርኩህ ሙሉ ፊቴን ሸፍነው ነው ወደ አዲስ አበባ ያመጡኝ::

**ግዮን፡- በጊዜው ግን ከየመን በቀጥታ ወደ መቀሌ ወስደውሃል ሲባል ነበር እኮ?**

**አንዳርጋቸው፡-** እኔም መጀመሪያ ላይ መቀሌ የወሰዱኝ ነበር የመሰለኝ:: ምክንያቱም አሳሪዎቼ በሙሉ ትግሪኛ ነበር የሚናገሩት፤ ከተያዝኩም በኋላ ያለሁበት ቦታ እየመጡ የሚያዩኝ፣ የሚያነጋግሩኝ፣ የሚጠብቁኝ በጠቅላላ ከትግረኛ ውጪ ሌላ ቋንቋ ሲናገሩ ስላልሰማሁ መቀሌ ነውያመጡኝ ብዬ ደምድሜ ነበር:: ፈፅሞ አዲስ አበባ ውስጥ ያስሩኛል ብዬ አልጠበቅኩም ነበር::

በኋላ ግን የእንግሊዝ አምባሳደር ከታሰርኩ ከአንድ ወር በኋላ መጥቶ ሲያነጋግረኝ "አዲስ አበባ ውስጥ ነው እንዴ ያለሁት?" ብዬ በጠየቅኩት መሰረት እሱ ነው አዲስ አበባ ውስጥ እንዳለሁ ያረጋገጠልኝ::

**ግዮን፡-የታሰርክበት ቤት ምን አይነት ነበር?**

**አንዳርጋቸው፡-** አንድ ቪላ ቤት ውስጥ ነው:: አንዱ ክፍል ውስጥ ነውእኔን ያሰሩኝ፤ መስኮቱ ተነቃቅሎ ግድግዳ ላይ ትንሽ ቀዳዳ የተሰራለት ቤት ውስጥ ስለሆነ ያስገቡኝ የት እንዳለሁ በፍፁም ማወቅ አልቻልኩም:: የማገኛቸው ሰዎች በሙሉ የህወሃት የደህንነት ሰዎች ናቸው፡፤ ምንም አይነት ያለህበትን ቦታ ፍንጭ የሚያሳይ ነገር አታገኝም::

**ግዮን፡- በእስር ላይ በነበርክበት ጊዜ የደረሰብህ ችግር ነበር፤ ድብደባ፣ ግርፋት የመሳሰሉ ነገሮች ተፈፅሞብሃል?**

**አንዳርጋቸው፡-** ድብደባ የሚያሰፈልገው ነገር አልነበረም:: እጄን ግጥም አድርገው ወደኋላ አስረው ብዙ ቀናት መተኛት በማልችልበት ሁኔታ ነው ያስቀመጡኝ:: በጣም የሚገርም አይነት ህመም ነው የሚሰማህ፤ስቃዩ ከባድ ነው:: ከዛ ውጪ መጀመሪያ ላይ እንዳልኩህ እጄን ሰብረውታል:: ሌላ የተለየ ሰውነቴ ላይ የተደረገ ግርፋትና ድብደባ የለም::

**ግዮን፡- ከእንግሊዝ አምባሳደር ውጪ ከሌሎች የኢምባሲው ዲፕሎማቶች ጋርስ የመገናኘቱ እድል ገጥሞሃል?**

**አንዳርጋቸው፡-** ከአምባሳደሩ በስተቀር ሌላ ሰው መጥቶ ሊያነጋግር አይችልም ብለው ስለነበር ቆንስሎች እንኳን እንዲያዩኝ አልፈቀዱም፤ አምባሳደሩ ላይ ብቻ እዲንዲህ ▶



◀አይነት ስራ ለማብዛት ለምን እንደፈለጉ አልገባኝም፡፤ አንድ አመት ከአንድ ወር እዛው መጀመሪያ ያሰሩኝ ቦታ ነው የቆየሁት::

**ግዮን፡-ያን ያህል ጊዜ የቆየህበትን ቦታ ለማወቅ ጥረት አላደረግክም?**

**አንዳርጋቸው፡-** አምባሳደሩ ሲመጡ እሳቸውን ለማነጋገር ሲወስዱኝ ፊቴ በብርድ ልብስ ተሸፍኖ ነው:: ይህ እንቅስቀሴ ገና ከክፍሏ ስወጣ ነው የሚጀምረው፤ምንም ነገር እንዳታይ ነው የሚደረገው:: ግን በእኔ ግምት የተለያዩ ነገሮችን ደምሬ ቀንሼ በሃሳቤ የደረስኩበት ገነት ሆቴል አካባቢ ካሉ ቪላ ቤቶች ውስጥ በአንዱ እንደታሰርኩ ነው የሚገባኝ::

እንዲህ አይነት በርካታ ሰው ማሰሪያ ቪላዎች እንዳላቸው ነው የገባኝ፤ ከአውሮፕላን ከወረድን በኋላ የተለያዩ ቦታዎች ሄደን ሲጠይቁ እየመለሷቸው መጨረሻ ላይ ያሰሩኝ ቦታ ተገኘና እዛ አስገቡኝ::

**ግዮን፡- ያመጡህ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ነው ?**

**አንዳርጋቸው፡-** የኢትዮጵያ አየር መንገድ ነው፤ ያው እኔን ከየመን ደህንነቶች እንደተቀበሉኝ ፊቴን ስለሸፈኑት አላየሁም፤ ግን አማርኛ የምታወራ የሆስተስ ድምፅ ሰምቻለሁ:: ቻርተር ፍላይትእንጂ ትልቅ የመንገደኞች አውሮፕላን አይደለም ይዘው የመጡት:: አፌ፣አይኔ፣ አፍንጫዬ በፕላስተር ፊቴ በጆንያ የተሸፈነ በመሆኑ በግልፅ ለማየት ባልችልም አውሮፕላኑ ውስጥ ከእነሱ በስተቀር ማንም ሰው አልነበረም:: ወደአውሮፕላኑ ሲያስገቡኝ የወጣሁት ሶስትና አራት ደረጃ ብቻ ስለነበር የያዟት ፕሌን ትንሽ መሆኗን ተረድቻለሁ::

**ግዮን፡- ከምን ያህል ጊዜ በኋላ ነበር ወደ ቃሊቲ የወሰዱህ?**

**አንዳርጋቸው፡-** አንድ አመት ከአንድ ወር በላይ በዛ ቪላ ቤት ውስጥ ነው የታሰርኩት፡፤ ሐምሌ 3 ቀን 2007 ዓ-ም ነው ወደ ቃሊቲ የተዛወርኩት::

**ግዮን፡- በአንድ አመት ቆይታህ ከቤተሰቦችህ ጋር ተገናኝተሃል?**

**አንዳርጋቸው፡-** ማንንም አላገኘሁም:: እንዲጠይቁኝም የተፈቀደላቸው የት እንዳለሁም የሚያውቁ አይመስለኝም:: አምባሳደሩ ብቻ ናቸው የጠየቁኝ::

**ግዮን፡- ከመንግስት ባለስልጣናት በታሰርክበት ጊዜ መጥተው ያነጋገሩህ ነበሩ?**

**አንዳርጋቸው፡-** የደህንነት ሰዎች ናቸው በተለያየ ጊዜ ያናገሩኝ:: ያው በደንብ ባላውቀውም ጌታቸው አሰፋ የሚባለው የደህንነት ሃላፊውን ጨምሮ የተለያዩ የተቋሙ ውሳኝ ሰዎች አነጋግረውኛል::

ከዚህ በፊት በ1997 ዓ.ም በታሰርኩበት ጊዜ ዝዋይ መጥተው አነጋግረውኝ ነበር:: የኔ እነመለስ ዜናዊ ልከውት ነው መጥቶ ያነገገረኝ፤ የሚገርም ጥያቄ ነበር በወቅቱ የጠየቀኝ::" ኢህአዴግ እንደዚህ የሆነው ምን ሆኖ ነው የሚል ጥያቄ ጠይቀው ተብዬ ነው የመጣሁት" ነበር ያለኝ::

ኢንተለጀንትና በተወሰነ ደረጃ ነገሮች የሚገባው ሰው ነው፤ ውይይቱም ቢሆን ረጅም ሰአት የፈጀና ብዙ ቀን የፈጀ ውይይት ነው ያደረግነው:: ችግር ያለው ነገር አልነበረም::

**ግዮን፡- ያኔ ከፍተኛው የደህንነት አመራሮች ያቀርቡልህ የነበረው ጥያቄና የምትወያዩበት ጉዳይ ምን ነበር?**

**አንዳርጋቸው፡-** በአጠቃላይ እኛ /ግንቦት ሰባት/ የምናደርገውን እንቅስቃሴ ነው ለማወቅ የሚፈልገው:: አብዛኛው ነገር ግልፅ ነው፤ እንደ አጋጣሚ በጣም መጥፎ የሆነው ነገር ኦርጋናይዝ አደርጋለሁ ብዬ በፍላሽና በኤክስተርናል ድራይቮች ላይ የያዝኳቸውን ብዙ ዶክመንቶችን በያዙኝ ወቅት ስላገኙ ብዙ የተጫኑኝ ነገር አልነበረም::

ከዚህ ውጪ አንዳንድ ነገሮች በእጄ የሌሉ አሉ፤ እኔ ኤርትራ በመመለስ ሙሉ ለሙሉ ከንቅናቄው ውጪ ሆኜ ስለነበር እዛ ላይ ብዙ ጥልቅ የሆኑ መረጃዎች አልነበሩኝም:: ብዙው ነገር በአደባባይ የሚውቁት ነው፤ የኤርትራ ጉዳይ አለ ስለእሱ ከዛ በፊት ራሳቸው ሲያወሩት የነበረ ጉዳይ ነው:: የ500 ሺህ ዶላሩ ጉዳይም አለ:: ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ግብፅ ስብሰባ እንደሄደና እንደተነጋገረ ጠይቀውኝ እኔም ተገቢውን ምላሽ ሰጥቻቸዋለሁ::

**ግዮን፡- ከግብፅ ገንዘብ ተቀብላችኋል ወይ ነው ጥያቄው?**

**አንዳርጋቸው፡-** አዎ:: አላመኑም መሰለኝ፤ ይሄን ያህል ገንዘብ እንዴት ይሰጧቸዋል? ብለው አላመኑም ይመስለኛል::እንዴት እንዲህ ታደርጋለች ?የሚል ስሜት ነው ያላቸው:: ከጎረቤት አገሮች ጋር ያለንን ግንኙነት፣ ከሱዳንና ከደቡብ ሱዳን ጋር ያለንን ግንኙነት በተመለከተ ጠይቀውኛል::

ከዚህ በተረፈ የአገሪቱ ፖለቲካ ላይ ነው በጣም ሰፊ የሆነ ውይይት ያደረግነው:: ያለውን የኢትዮጵያ ፖለቲካ በተመለከተ በቃል ከማስረዳት ባሻገር በፅሁፍ መቶ ሰማኒያ አምስት ገፅ እንዴትና ምን ማድረግ እንዳለባቸው ገልጬላቸዋለሁ::

ከ1997 ዓ.ም ምርጫ ጀምሮ እስከ መጨረሻው ሰአት ድረስ ያሉትን ነገሮች በዝርዝር የሚያሳዩ ፅሁፍ ሰጥቻቸዋለሁ:: ኮምፒዩተር ሰጥተውኝ ጊዜ ወስጄ በችግሮቹና በልዩነታችን ላይ ብሎም በመፍትሔዎቻችን ላይ ጭምር ዝርዝር ማብራሪይያ ፅፌ ሰጥቻቸዋለሁ::

**ግዮን፡- ዶ/ር ቴዎድሮስ አድሃኖም የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር በነበሩበት ወቅት "አንዳርጋቸው መፅሃፍ እየፃፈ ነው፤ ላፕቶፕ አስገብተንለታል" ብለው ነበር፤ ይሄ ነገር እውነት ነው?**

**አንዳርጋቸው፡-** አዎ:: መጀመሪያ እኔ የምፅፈውን ነገር ከፖለቲካ አኳያ ስለፈለጉት ኮምፒዩተር የሰጡኝ ይመስለኛል:: ግን በእሱ አልቆመም:: ኮምፒዩተር ከሰጡኝ በኋላ ሌላ የምፅፈው ነገር እንዳለ ለጌታቸው ገልጬለት ተጨማሪ የምፈልገው ነገር ካለ እንደሚተባበሩኝ በገለጸልኝ መሰረት ለጽሁፌ የሚረዳኝ ሪፈረንስ መፅሃፍም እንዳስገባ ፈቅዶልኛል::

አሁን እንግዲህ ወደ 850 ገፅ ደርሷል የፃፍኩት ልክ እንደዘውዴ ረታን "አፄ ሃይለ ስላሴ" የተሰኘውን ትልቅ መፅሃፍ ያህላል መጠኑ:: በመፅሃፍ ደረጃ ኮምፒዩተሬ ላይ ተቀምጧል፤ "እኛም እንናገር፣ ትውልድ አይደናገር" የሚል ስምንት መቶ ሃምሳ ገፅ ያለው መፅሃፍ ነው:: በተለይ ድሮ በኢህአፓ ጊዜ፣የ የቤተሰባችንን የከተማዋን የአዲስ አበባን አጀማመርና አመሰራረትና ህይወቷን በጠቅላላ ማለትም እኔ ከእዚህ ከተማ እስከወጣሁበት 1970 ዓ.ም ድረስ የነበረውና የህዝቡን ህይወት የሚዳስስ ነው::

ስለዚህ ዶ/ር ቴዎድሮስ አድሃኖም ያለው እውነቱን ነው:: ግን የመጀመሪያው ከፖለቲካ ጋር የተያያዘ ነው፤ ያንን ካገኘሁት አገኘሀት ካላገኘሁት የሚሆነውን እስኪ እናያለን:: ዛሬ በአገሪቱ ውስጥ ያለውን ችግርና ድክመት አንድም ሳይቀር በዝርዝር የያዘ ዶክመንት ነው፤እኔ በተገኘው አጋጣሚ እነሱን ዙሪያቸውን የከበቧቸው አድርባዮች የማይነግሯቸው ችግሮች የሚያመላክቷቸውን እውነታዎች ነግሬያቸዋለሁ:: የሚቀጥለውአ ይነት ነገር ውስጥ መግባት ከፈለጉ ፤የፍርድ ቤቱን ውሰኔ የሚያስፈፅሙም ከሆነ አንድ ትልቅ ነገር ነው በሚል ምንም አይነት ቁጠባ በሌለው መንገድ መልኩ ነው ፅፌ የሰጧቸው::

**ግዮን፡- አንተ ችግሮቻችሁ እነዚህ ናቸው ብለህ ፅፈህ ስትሰጣቸው እነሱ የተከራከሩትና ያነሱት ነገር አለ?**

**አንዳርጋቸው፡-** በውይይታችን ጊዜ ነበር:: በድሁፉ ላይ ግን ውይይት አልተደረገም:: ለመንግስት ባለስልጣናት የሰጧቸው አይመስልም:: እኔም በግልፅ የፃፍኩት ለሌሎች ድርጅቶች ሳይሆን ለህወሃት ብዬ ነው:: ሌሎች ድርጅቶችን በተወሰነ ደረጃ ሊያስቀይም የሚችል ነገር አለው ::ምክንያቱምእኔ በዋነኝነት ሁሉን ነገር የምትሰሩት እናንተ ናችሁ ለልማቱም ለጥፋቱም ተጠያቂ፤ እናንተ ናችሁ አሁን ያለውም ችግር ይሄ ነው፤ ብዬ ህወሃቶችን በግልፅ የፃፍኩላቸው፤ የነገርኳቸው::

በዝርዝር ውስጥ ችግሮችን ከመጠቆምና ከማመልከት ባሻገር መደረግ ያለባቸውንም መፍትሔዎችን ገልጫለሁ:: በዛ መልኩ እነሱ የፈለጉት ነገር መጀመሪያ ስለነበረ ነው ኮምፒዩተር እንዲገባና እንድፅፍ የተፈቀደው::

**ግዮን፡- አሁን እነዛ ፅሁፎች በአንተ እጅ አሉ?**

**አንዳርጋቸው፡-** የሉም ::እነሱ ጋር ስለሚገኝ እጠይቃለሁ፤ ፅሁፎችን የማግኘት እድል ይኖረኛል ብዬ ነው የማስበው::

**ግዮን፡- ወደ ከተማ ወጥተህ በአዲስ አበባ የጎተራው ማሳለጫ መንገድን እንድትጎበኝ ተደርገሃል የሚባለውስ?**

**አንዳርጋቸው፡-** ብዙ ጊዜ በከተማ ልማት ላይ እንከራከር ስለነበር ከሰራነው መሃል አንዳንዱን ነገር እናሳይህ ብለው የተወሰኑ ቦታዎችን አሳይተውናል:: ከአዲስ አበባ ወደ አዳማ የሚሄደውን የፍጥነት መንገድ፣ኮንዶምኒየሞች፣ ማሳለጫውን አሳይተውኛል::

**ግዮን፡- የዛኔ በሚደያዎች ላይ የወጣው ፎቶ ትክክል ነበር ማለት ነው?**

**አንዳርጋቸው፡-** በዛ መንገድ ይጠቀሙበታል ብዬ አልጠበቅኩም:: ምክንያቱም በተወሰነ ደረጃ ያለውን ነገር አላውቅምና እነሱ ምንም የሆነው ነገር የለም ለማለት የተጠቀሙበት ይመስለኛል::

በመንገድ ስራ፣ በኮንዶማኒየም▶





ግንባታና በአጠቃላይ በከተማ ልማት ዙሪያ የሰራችሁት ዝም ብሎ ተራ የሆነ ነገር ነው የሚል ከፍተኛ ክርክር ስለዳረኩባቸው እኔን ለማሳመን የተጠቀሙበት ዘዴ ነው::

**ግዮን፡- አንዳርጋቸውን "ከድርጅቱ ሰዎች መሃል አሳልፎ የሰጠው ሰው አለ "የሚል ነገር አለ፤ አንተ ታምንበታለህ?**

**አንዳርጋቸው፡-** የለም:: ፈፅሞ ሊኖር አይችልም::ምክንያቱም ይሄ ነገር በጣም በቀላሉ ሊሆን የሚችል ነገር ነው፤ ስለዚህ እንዲህ አይነት መረጃ ላይ ያልተመሰረተ ዝም ብሎ የሚወራ ነገር ነው ፤ተገቢም አይደለም::

ነገሩን ከስሩ ካየነው ከዱባይ ስነሳ ከኤርፖርት ጀምሮ ብዙ ሰው ነው የነበረው፤ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ሰዎችም የሚሳፈሩበት አውሮላላን ነው:: እኔ በይፋ የምታወቅ ሰው በመሆኔ የእነሱ ሰው "አንዳርጋቸው እዚህ አውሮፕላን ላይ አለ "ብሎ ለመናገር በጣም ቀላል ነበር::

**ግዮን፡- ሲይዙህ ቤተሰቦችህ፣ ልጆችህን ፣በተለይም ደግሞ ኤርትራ በረሃ ድረስ ያወረደህን ትግልህን ስታስበው.. በቃ ሃሳቤን ከግብ ሳላደርስ ሊገሉኝ ነው የሚል ፍርሃት አላሳደረብህም?**

**አንዳርጋቸው፡-** እንደውም እኔ የመን ላይ ከመያዜ በፊት ኤርትራ ውስጥ ሆኜ የሚገለኝን ሰው የላኩ በመሆናቸው ለምንም ነገር እንደማይመለሱ አውቅ ነበር:: በየመን በኩል ለመሄድ ጉዞ ስጀምር ትንሽ ስለተጠራጠርኩ እዛ ያለው የኤርትራ አምባሳደርን እስከምሄድ ደረስ እንዲያገኘኝ ላኩልኝ ብዬ ለየማነ ነግሬው ነበርና አምባሳደሩ እንደሰማሁት እዛ ሰነአ ኤርፖርት ነበር::

በዚህ የተነሳም እንዲህ አይነት ነገር ሊኖር እንደሚችል መረጃው ስላላቸው ወሬው ይወጣል በሚል ስጋት ይሆናል እርምጃ ሳይወስዱብኝ የተረፍኩት ብዬ አስባለሁ::

**ግዮን፡- መረጃዎች እንዳይዙብህ ለማሸሸ አልሞከርክም?**

**አንዳርጋቸው፡-** አልቻልኩም:: በጊዜው ብቻዬን ነው የነበርኩት:: እንደያዝኳቸው ነው በቁጥጥር ውስጥ ያዋሉኝ::

**ግዮን፡- ቃሊቲ ከገባህ በኋላም ለብቻህ የታሰርክበት ክፍል ቀደም ሲል እነ ታምራት ላይኔና ስዬ አብርሃ የታሰሩበት ነው ::እንደውም ክፍሉ በተለየ ሁኔታ እየተሰራና እየታደሰ ስለነበር ከአንተ ቀድመው የታሰሩት እስክንድር፣አንዱአለምና አበበ ቀስቶ ሁኔታውን በንቃት ሲከታተሉት ነበር::**

**አንዳርጋቸው፡-** መጀመሪያ ቃሊቲ እንደሄድኩኝ አንድ ሰው ብቻ ያለበት ጠበብ ያለች ክፍል ነው ያስገቡኝ ::በኋላ ቤቱን በተባለው መንገድ አስተካከሉና ሌሎች ሁለት ሰዎችን ጨምረው እዛ ክፍል ውስጥ አስገቡኝ::... እነዛ አብረውኝ እንዲታሰሩ የተደረጉት በተራ ነፍስ ግድያ ተከሰው የታሰሩና ምንም አይነት የህይወት ተሞክሮ የሌላቸው ምንም አይነት ትምህርትና እውቀት የሌላቸው ኑሮን በጣም አስቸጋሪ ማድረግ የሚችሉ ሰዎች ናቸው::

ሌላው እስረኛ የሚያገኘው የቴሌቭዥንና ሬድዮ የመከታተል መብት እኔ ጋር አልተፈደልኝም፤ ማንኛውም ሰው ቤተሰቦቹ እንደፈለገ ይጠይቁታል እኔ ከአባቴና ባለቤቱ ሌላ ሰው እንዲጠይቀኝ አልተደረገም:: ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠበት ግልባጭ የሚባል ቅፅና ቁጥር ሁሉ እስረኛ አለው፤ እኔ ግን የእስረኛ ቁጥር የለኝም:: ጭራሹኑ አንደኛው የወህኒ ቤቱ ሰው "በአደራ ነው የተቀመጥከው እንጂ እኛ ብዙም የሚያገባን ነገር የለም" ነው ያለኝ፤ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ነው የቆየሁት:: ኤምባሲው በመደበኛነት መፅሃፎችን ያመጡልኛል፤ አንዳንድ አማርኛ መፅሃፎችን ማን እንደላከልኝ ባላውቅም አገኛለሁ:: ምናልባት እህቴ ትሆናለች፤ የዶክተር ምህረትን ሁለቱን መፅሃፎች እዛ ነው ያነበብኩት:: ወደ ሁለት መቶ የሚጠጉ መፅሃፎችን እስር ላይ እያለሁ አንብቤያለሁ::



**ግዮን፡- ምግብና ህክምናን በተመለከተስ ያለው ነገር እንዴት ነው?**

**አንዳርጋቸው፡-** ምግብ ያው ወላጆቼ በሳምንት አንዴ የሚያመጡት ነገር ነው፤ አልፎ አልፎ ጉድለት በሚኖርበት ሰአት ላይ እኔ ብዙም ለምግብ የምጨነቅበት ሁኔታ ስለሌለ እዛ ያለውንም ምግብ እጠቀማለሁ:: እዛ ያለው ምግብ የኢትዮጵያ ህዝብ ዘጠና በመቶ የሚሆነው እንጀራ በወጥ በመሆኑ ያንን የእስረኞች ምግብ እጠቀማለሁ:: መሆንም ያለበት ይሄ ነው ::የኢትዮጵያ ህዝብ ምሳና እራቱን በአግባቡ የማይበላ ከሆነ አንደኛውን መቀነስ አለብኝ የምል ፖለቲከኛ ነኝ እኔ:: ስለዚህ በምግብ ረገድ አማርሬ አላውቅም::



◀ሌላውን ነገር አማርሬ አላውቅም:: ህክምና ከጥርስ ጋር በተያያዘ ለሰባት ጊዜያት ያህል ጉንጬን አሳብጦት ከፍተኛ ህመም ገጥሞኛል:: ግን ከማደንዘዣዝና አንቲ ባዮቲክ በስተቀር ሌላ ቦታ የተሻለ ህክምና እንዳገኝ ማድረግ የማይታሰብ ነገር ነው:: አራቱን አመት ከእኔ ጋር የታሰሩት ሰዎች ጥቁር አንበሳ፣ኢቭን የግል ሆስፒታሎች ጭምር ወስደው ያሳከሙበትና ያስመረመሩበት ሁኔታ አይቻለሁ:: እኔን ግቢው ውስጥ መጥታ የምትመለከተኝ አንድ የጤና ኦፊሰር ነው የመደቡት:: ለማንኛውም ነገር እሷ ነች የምትመጣው::

**ግዮን፡- በቅርቡ ቴሌቭዥን የታሰርክበት ክፍል ገብቶልህ ነበር፤ ለመሆኑ አዲሱን ጠ/ሚኒስትር እንዴት አየሃቸው?**

**አንዳርጋቸው፡-** የዶክተር አብይን ንግግራቸውን ነው የሰማሁት ፊታቸውን ነው ያየሁት:: ከዛ በፊት አላውቃቸውም ግን አጀማመራቸው በጣም ጥሩ ነው:: እንደ ነጂ ሳይሆን እንደመሪ ነው የሚናገሩት:: አንድን ሰው መጀመሪያ በንግግሩ፤ ከዛ በድርጊቱ ነው የምትለካው እስካሁን ድረስ ግን አዲሱ ጠ/ሚኒስትር ባደረጓቸው ንግግሮች፤ ከንግግሮቻቸው ጋር በፊት ገፅታቸው ላይ የምታየው ስሜት ዝም በለው ለለባጣ የሚናገሩ ሰው እንዳልሆኑ በስሜታቸው የሚናገሩ ሰው እንደሆኑ ትመለከታለህ:: ከዚህ በመነሳት የተሻለ ነገር ሊሰሩ ይችሉ ይሆናል የሚል ተስፋ አሳድሮብኛል::

**ግዮን፡- “አንዳርጋቸውን በማሰራችን 11 ቢሊየን ዶላር አጥተናል፤ አንዳርጋቸው እንዲፈታ እምነቴ በመሆኑ ወስኛለሁ “ብለው ለትግራይ አርቲስቶችና ባለሃብቶች ባደረጉት ግብዣ ላይ የተናገሩት ዶ/ር አብይ ከመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር አንተን ለማስፈታት ከፍተኛ አለመግባባት ውስጥ እንደነበሩ ተናግረዋል… በዚህ ላይ ምን ትላለህ?**

**አንዳርጋቸው፡-** እኔ ይሄ ነገር መኖሩ አይገርመኝም:: ግን የተባለው ነገር እውነት ከሆነ የህወሃት ሰዎች ተሳስተዋል:: የህወሃት ሰዎች ከእኔ በላይ ወዳጅ የላቸውም:: ምክንያቱም በዙሪያቸው የተሰበሰበው አድርባይ የማይነግራቸውን እየነገርኩ በጊዜ ገና በ1983 እና 84 ዓ.ም ላይ የተናገርኩት ኢትዮጵያ ቴሌቭዥን አለ::

በዛን ጊዜ ችግር ሊመጣ እንደሚችልና ምን መስተካከል እንዳለባቸው ነው የነገርኳቸው ::ይሄ ደግሞ ከማንኛውም አገሪቷ ውስጥ ካለው ህዝብ የበለጠ በቅርበት አብሬው በመኖር ብዙ የችግርና የመከራ ጊዜን ከልጆቼ አፍ ቀንሶ መግቦ ላኖረኝ ለትግራይ ህዝብ ካለኝ ፍቅር፣ ያ ህዝብ ከዋለልኝ በመነሳት ነው::

በህዝቡ ላይ ምንም አይነት ችግር ሊደርስ የሚችልበት ሁኔታ እንዲመጣ ስለማልፈልግ መሪዎች በሚያጠፉበት ሰአት ላይ በጊዜ ነው መስተካከል የሚኖርባቸውን ነገሮች ለመናገር የሞከርኩት:: እነዛ አመራሮች እንዲህ አይነት ተቃውሞ ማቅረብ አልነበረባቸውም::

በዙሪያቸው አድርባይ የሆኑ፣ በጣም አጎብዳጅ የሆኑ፣ እውነቱን የማይነግሯቸውና በጊዜ መስተካከል ያለባቸውን ችግሮች የማይጠቅሟቸውን ሰዎች እንደ ወዳጅ አድርገው ማየት የለባቸውም ነው ያልኩት:: እኔ እዚህ አገር በ1983 ዓ.ም ስመጣ ኢህዴንን ወይም ሌላውን ድርጅት አይደለም የማውቀው:: ያኔ የማውቀው ህወሃቶችን ነው:: እንግሊዝ አገር ሆኜ ህወሃትን መደገፍ ፋሽን ባልነበረበት ሰአት እኔ ነበርኩ የምደግፈው:: ከእነሱ ጋር ያለኝ ግንኙነት በመርህ ላይ የተመሰረተ በከፍተኛ ወዳጅነት ላይ የተመሰረተ እንጂ በጠላትነት ላይ የተመሰረተ አልነበረም ::ግን ስህተት ሲሰሩ በአድርባይነት የማለፍ ባህሪይ የለኝም:: እኔ በምናገርበት ሰአት ላይ ራሳቸውን መመርመር ነው እንጂ የሚገባቸው በጠላትነት ፈርጀው ማየት አልነበረባቸውም::

እነሱን ሊጠቅሙ የሚችሉ ያላቀረብኳቸው ሃሳቦች የሉም:: እኔ ክርክሬ በሙሉ ድርጅቱን ይጠቅማል ፣ድርጅቱን በህዝቡ ተወዳጅ ያደርጋል በሚል መልኩ ነው አቅርብ የነበረው::ያልኳቸው ነገሮች ሁሉ በተግባር ውለው ቢሆን ኖሮ እንደ ጣኦትነት የሚመለኩበት ሁኔታ መፍጠር እንችል ነበር::

**ግዮን፡- ከእስር እንደተፈታህ ዶ/ር ብርሃኑ፣ጃዋር መሃመድ፣ ኦኤምና ኢሳት ክሳቸው ተቋርጧል የሚል ነገር ተናግሯል::ይሄ የፖለቲካ ምህዳሩን ያሰፋዋል?**

**አንዳርጋቸው፡-** ተስፋ የሚሰጥ ነገር ነው፤ መደረግም ያለበት ነገር ነው:: በአጠቃላይ እኔ የተቃውሞ ሱስ የለብኝም፤ እውነት ለመናገር ሁሉን ነገር ጨርሼ ወደ ስነ ፅሁፍ እገባለሁ ባልኩበት ሰአት በ1997 ምርጫ ወቅት የሰሩት ስራ ነው መልሶ ፖለቲካ ውስጥ የጨመረኝ:: እዚህ አገር ውስጥ ያየሁት ከፍተኛ የሆነ የመብት ገፈፋና ኢ ሰብአዊ ድርጊት ነው መልሶ ፖለቲካ ውስጥ የጨመረኝ እንጂ እኔ በስፋት ወጣቱ ሊያነባቸው የሚችል ፣ማንነትን ሃገሩን የኢትዮጵያ ህዝብ ያደረገውን ትግል የሚገልፅ አራት አምስት መፅሃፎችን ፅፌ መጨረሻዬ ሰአት ላይ እሆን ነበር::

በዚህ አይነት ወደፊት የሚሰራ ከሆነ አስተማማኝየሆነየፖለቲካምህዳር እስከተፈጠረ ድረስ ፤ደጋግመን እኛ ያስቀመጥነው ነገር አለ እንደ ግንቦት ሰባት:: እኛ ስልጣን የመያዝ ጉዳይ አይደለም ጥያቄያችን፤ ሁሉንም ህዝብ በነፃነት በእኩልነት የሚያገለግሉ፣ ነፃ ተቋማት መኖር አለባቸው ነው የምንለው፤ ነፃ ተቋማት ጥያቄ የፖለቲካ ምህዳሩን እናሰፋለን ስለተባለ ብቻ የሚቃለል አይደለም:: በተጨባጭ እነዚህ ተቋማት መታየት አለባቸው::

ነፃ ተቋማት ስንል መከላከያውን ፣ነፃ ተቋማት ስንል ደህንነቱን፣ ነፃ ተቋማት ስንል የፍርድ ስርአቱን፣ ነፃ ተቋማት ስንል ፖሊስን፣ ነፃ ተቋማት ስንል ሚዲያውን፣ የምርጫቦርዱን ነው:: እነዚህን በነፃ ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅትና አጠቃላይ የአገሪቱ ህዝብ ነፃና ገለልተኛ ናቸው ብሎ በእርካታ በሚቀበልበት ሰአት፤ እውነትም ይህች አገር በተረጋጋ ሁኔታ ውስጥ ገብታለች::

በዚህ አጋጣሚ ባለፉት አመታታት ለታየው የህዝብ ንቅናቄና ለተሳተፉትና እኔን ለማስፈታጽ በተደረገው እንቅስቃሴ ላይ ለተሳተፉት ኢትዮጵያዊያን በሙሉ ትልቅ አክብሮት እንዳለኝ በዚህ አጋጣሚ እገልፃለሁ:: አመሰግናለሁ ::ይሄን መሰሉ ድጋፍ የበለጠ በመንገዳችን እንድንገፋ ያደርገናል፤ ህዝቡም ለመብቱ መታገሉን ችግሮች እስካልተፈቱ ድረስ ወደ ፊት መቀጠል ይኖርበታል::

**ግዮን፡- እናመሰግናለን::**





# “ሀገሪቱ እየተመራች ያለችው በአዋጅ እንጂ በሕግ አይደለም”

## ብ/ ጄነራል ተፈራ ማሞ

**ግዮን፡ በግንቦት ሠባት ተከሣችሁ ከታሰራችሁት መካከል አንዱ እርስዎ ነዎት፤ ቀደም ብለው እርስዎና ሌሎች ተከሳሾች ተፈታችሁ:: ነገር ግን የክሳችሁ ዓቢይ ጉዳይ የነበረው አንዳርጋቸው አልተፈታም ነበርና በወቅቱ እርስዎ ሲወጡ አንዳርጋቸው ሳይፈታ ሲቀር የተሰማዎት ስሜት ምን ነበር?**

**ብ/ ጄነራል ተፈራ፡-** ምንም ሙሉነት አልተሰማንም:: ጉዳዩ የተያያዘ ስለነበር ከጅምሩ ያው የህዝብ ግፊት ስላለው አለመፈታቱ ዋናው ጥያቄያችን ነበር::

**ግዮን፡- ከአንዳርጋቸው ጋር እንዴትና የት ነው የምትተዋወቁት?**

**ብ/ ጄነራል ተፈራ፡-** አንዳርጋቸውን የተዋወቅሁት በ1983 ዓ.ም. አዲስ አበባን እንደተቆጣጠርን ነበር:: በተለያዩ የሥራ ቦታዎች ይሠራ ነበር:: አጋጣሚ ማታ ማታ የሚደረገውን የሠላም ማረጋጋት ስናደርግ አልፎ አልፎ ይገኛል:: በዚያን ጊዜ አንዳርጋቸው ዝም ብሎ ነው ይታዘብ የነበረው:: የሚደረገውን እንቅስቃሴ በትዝብት ነበር የሚከታተለው:: በዋነኛነት አንዳርጋቸው ማን መሆኑን ያወቅሁት በ1985 ዓ.ም. ደሴ ላይ የኢትዮጵያ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ ኮንፈረንስ አድርጎ በነበረበት ወቅት ነው::

በኮንፈረንሱ “ከጅምሩ ድርጅቱ ወደ ተሳሳተ እንቅስቃሴ እየሄደ ነው:: ለህዝብ የገባችሁትን ቃል ተግባራዊ እያደረጋችሁት አይደለም:: የግል ቤታችሁን ለማሟላት ነው እየተሯሯጣችሁ ያላችሁት:: መኪናና ቤት ስትቀይሩ ነው የምትውሉት፤ ይሄ መስተካከል አለበት:: ይህ ህዝብ የሚጠብቀው ከእናንተ ይህንን አይደለም” በሚል የኢህአዴግን አጠቃላይ ብልሹ አካሄድ በጽኑ ሲቃወም ነው አንዳርጋቸውን ማወቅ የቻልኩት::

**ግዮን፡- በዚያን ጊዜ የአንዳርጋቸው ተቃውሞና ሀሳብ የህዝብ ተቀባይነት ነበረው?**

**ብ/ ጄነራል ተፈራ፡-** አዎ:: የእርሱን ሃሳብ ተቀብለውታል:: መሪው ወደሥራ ገብቶ ለህዝብ የገባውን ቃል ተግባራዊ ከማድረግ የራሱን ቁሳዊ ፍላጎት ለማሟላት ሲሯሯጥ ስለነበርና አብዛኛው አባላትም ይህንን የአንዳርጋቸውን ሀሳብ ይደግፍ ስለነበር በትክክል ምን አይነት ሠው መሆኑን መረዳት ችለናል::

**ግዮን፡- ከዚያ ስብሰባ በኋላ እሱን አጣችሁት ማለት ነው?**

**ብ/ ጄነራል ተፈራ፡-** በዚህ ጊዜ ነው ከእንዲህ አይነት ድርጅት ጋር አልቀጥልም ብሎ ያቆመው:: በስብሰባው ላይ በግልፅ አስተያየቱን ከሰጠን በኋላ ድርጅቱን ጥሎ ወደ መጣበት ተመለሰ::

**ግዮን፡- አንዳርጋቸው በዚህ ዕድሜው በረሃ ገብቶ ትግል ማድረጉን፣ ለዓመታት ያለመታከት ለሀገርና ለሕዝብ መድከሙን፣ ለተከታታይ ዓመት በዚህ ምክንያት መታሰሩንና ጽናቱን ስትመለከት በአንተ ዕይታ ይህን ታላቅ ኢትዮጵያዊ እንዴት ትገልጸዋለህ?**

**ብ/ ጄነራል ተፈራ፡-** አንዳርጋቸው ፋና ወጊ ከሚባሉት የፖለቲካ መሪዎች የሚመደብ ነው፤ በተፈጥሮአቸው አቅጣጫ የሚያስይዙ፣ ለሕዝብ የሚቆሙ አንዳንድ ሰዎች አሉ:: እሱም ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው ለሀገር የቆመ ሰው ነው:: ሥርዓቱ ለሕዝብ እንደማይሠራና እንደማይሆን አውቆታል:: ከወጣትነቱ ጀምሮ



የመጣና ሕይወቱ በትግል የተመሰረተ ለሕዝብና ለሀገር ሕይወቱን አሳልፎ የሰጠ መሪ ነው::

የሚገርምህ ግላዊ ሰብዕናውም በዚያ ደረጃ ነው፤ ገና ቀድሞ ኢህአዴግ ሥልጣን ላይ በወጣበት /1983 ዓ.ም/ ጊዜ "ይህ አምባገነናዊ አሠራርና የሥልጣን ዋልጌነት አያስፈልግም:: የሕዝብ ጥያቄ ሊመለስ ይገባል::" በማለት በግልጽ ነው የተቃወማቸው:: ይህንን አቋሙን እስካሁን ድረስ ይዞ የዘለቀ ትልቅ ሰው ነው::

**ግዮን፡- ከአራት ዓመት እስር በኋላ መፈታቱን ስታውቅና ስታገኘው ምን ተሰማህ?**

**ብ/ ጄነራል ተፈራ፡-** አንዳርጋቸው ተፈትቶ መጥቶ ስንቀበለው ሁለት ስሜት ነው የተሰማኝ:: አንደኛው በእስር ቤት ሰውነቱ አልቆ፣ ያ ግርማ ሞገስ ያለው አካሉ በዚያ ደረጃ ቀንሶ ሳየው በጣም ነው ያዘንኩት:: መጀመሪያ በአካል ስንገናኝ ማለት ነው:: ሁለተኛው ደግሞ በዚህ መልክም ቢሆን በሕይወት መትረፉና መገናኘቱ ደስታን ፈጥሮብኛል:: አካል ቢጎዳ ምንም አይደለም፤ በጊዜ ሂደት ይመለሳል፤ ይታደሳል::

ፅናቱ በጣም የሚገርም ነው:: አሁንም ፊቱና አዕምሮው ላይ ይህን ነገር በግልፅ ታገኘዋለህ:: በዚህ ጊዜም ቢሆን ለሀገርና ለሕዝብ መከፈል ያለበትን ነገር ሊከፍል የተዘጋጀ መሆኑን ስትመለከት ለአንዳርጋቸው ያለህ ፍቅርና አክብሮት ይጨምራል::

**ግዮን፡- በተፈታ ማግስት /ረቡዕ ዕለት/ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዓቢይ አህመድ አንዳርጋቸው ፅጌን ጠርተው አናግረውታል:: እንዲህ አይነቱ መቀራረብ የፖለቲካ ምህዳሩን ይቀይረዋል ብለህ ታምናለህ?**

**ብ/ ጄነራል ተፈራ፡-** የሚሆነውን ነገር ወደፊት በሰፊ የምናወቀው ነው:: ግን ጅምሩ ጥሩ ነው:: መሪ ምንጊዜም ሆደ ሰፊ መሆን አለበት:: ትዕግስትኛ መሆን አለበት:: በስሜት የመነዳት ነገር አያስፈልግም:: ነገሮችን በማቻቻል ነው ማየት ያለበት:: ወደተለያየ አቅጣጫ የሚሄዱት ሰዎች ሁሉም የአንድ ሀገር ሕዝቦች ናቸውና በሰከነ መንገድ መመልከት ያስፈልጋል::

በአሁኑ ሰዓት ዶ/ር ዓቢይ እየተከተሉት ያለው መንገድ የሚደገፍና ሊበረታታ የሚገባው ነው:: ሰዎችን በእስር በማቆየት የምትፈይደው ነገር የለም:: አዲስ ነገር ነው አሁን የምታይባቸው… ቅድሚያ ለዜጎች በመስጠት በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ያሉ ኢትዮጵያውያንን የማስፈታት ሂደታቸው በጣም የሚደንቅ ነው:: ጊዜ ወደፊት የበለጠ ነገር ሊያሳየን ይችላል፤ የአሁኑ ሥራቸው ግን ሊደነቅ ይገባዋል::

**ግዮን፡- ወደፊት ከአንዳርጋቸው ጋር ምን ለመሥራት አስበሃል?**

**ብ/ ጄነራል ተፈራ፡-** አሁን ይህን አስበናል ማለት አይቻልም:: የሕዝብ ጥያቄ እስካልተመለሰ ድረስ ከትግል አትቆምም:: ይህቺ ሀገር የሁላችን ሀገር ነው መሆን ያለባት፤ አንዱ እንደፈለገ ሲሆን ሌላው በዝምታ ሊመለከት አይገባም:: ይህች ሀገር የሁላችን እስክትሆን፤ በእኩልነት መላው ኢትዮጵያዊ የሚጠቀምባት እስክትሆን ድረስ ትግሉ ይቀጥላል:: ግን ትግሉ ምን አይነት ቅርፅ ይኖረዋል? የሚለውን በሂደት የምናየው ይሆናል::

በነራችን ላይ የአንዳርጋቸው እምነትና ቃል ይህ ነው:: ይህቺ ሀገር የተሻለች ሀገር መሆን አለባት:: የተሻለች ሀገር ማለት ሌላ አይደለም፤ ሁሉም ዜጎች በእኩልነት የሚኖሩባት፣ የበይ ተመልካችነት የሚቀርባት ማለት ነው::

**ግዮን፡- ዶ/ር ዓቢይ አንዳርጋቸውን ለመፍታት ከፍተኛ የሆነ ሙግት ከህወሓት ሰዎች ገጥሟቸው እንደነበር ተናግረዋል:: አሁን ከተፈታ በኋላ ባለው ሂደት ሲታይ ህወሓት የበላይነቱን እያጣ ነው ማለት ይቻላል?**

**ብ/ ጄነራል ተፈራ፡-** ህወሓት የበላይነቱን አጥቷል ማለት አይቻልም:: ምክንያቱም የእነሱ የበላይነት በሳምንታት የቆመ ሳይሆን በ27 ዓመታት የተገነባ ነው፡ 27 ዓመት ሙሉ በሥልጣን መዋቅሩ ሁሉንም ቦታዎች የራሳቸው አባላት ናቸው የያዙት:: የፖለቲካ መዋቅሩም ሆነ ሌላው ነገር በእነሱ ውስጥ ነው የነበረው::

የግለሰብ ውሳኔ የበላይነታቸውን ማጣትን አያሳይም:: አሁንም የበላይነታቸው እንዳለ ነው:: የአንዳርጋቸውን መፈታት በትክክል ካየነው እነሱንም አይጎዳቸውም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ “ይፈታ፣ መሪያችን ነው” እያለ ዝም ማለት ምንድን ነው? እዚህ ላይ ዶ/ር ዓቢይ በልጧቸዋል፤ ምን ያህል የሕዝብን የልብ ትርታ አውቆ እንደሚሄድ በአንጻሩ እነሱ ደግሞ ከሕዝብ እየራቁ መሆኑን ያሳያል::

በአሁኑ ሰዓት ሀገር በአዋጅ እንጂ በሕግ አይደለም እየተመራ ያለው:: አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አልተነሣም:: እነሱ ሕዝቡን በጠመንጃ ኃይል ይዘው የሥልጣን እድሜያችን ማራዘም አለብን ብለው ነው የሚያምኑት:: ቢገባቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደዚህ አቅጣጫ መምጣታቸው ህወሓትን ከገደል አፋፍ እንደማውጣት ያሳያል:: እንደመሪ ዶ/ር ዓቢይ ላደረጉት ብናመሰግንም የህወሓት የበላይነት ተጥሷል የሚባለው ውሸት ነው::

**ግዮን፡- አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሳይነሣ እስረኞችን ብቻ መፍታቱ የጠቅላይ ሚኒስትር ዓቢይን መንግሥት በትክክል ተለውጧል ማለት ይቻላል?**

**ብ/ ጄነራል ተፈራ፡-** ይሄ እኮ ነው ችግሩ:: አካሄዳቸው መያዣ መጨበጫ አጥቷል:: ወደትክክለኛ ነገር ከመጣህ እስረኞች ሁሉም ነው መፈታት ያለባቸው:: የፀረ ሽብር ሕጉና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁም ተነሥቶ ነው ወደትክክለኛ ውይይት መገባት ያለበት::

ይህንን ነገር በተመለከተ ዶ/ር ዓቢይ ሥልጣኑን ተጠቅሞ፣ ነገሮችን ተጋፍጦ ከላይ ያልናቸውን ነገሮች ወደ ተግባር ለውጦ እናያለን የሚለውን አሁን መፍረድ ይከብዳል::



# "ጠ/ሚኒስትሩ የቂም በቀል ሰንሰለት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሰበረው ይመስለኛል"

## ስዩም ተሾመ



**ግዮን፡- በአንዳርጋቸው ፅጌ መፈታት የኢትዮጵያ ፖለቲካ ወዴት እያመራ ነው ማለት ይቻላል?**

**ስዩም፡-** የዜጎች መብት፣ ነፃነትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ይረጋገጥ የሚል ጥያቄ ይዞ ነው የተነሣው:: ያ ጥያቄ መልስ ባለማግኘቱ የትጥቅ ትግል ጀምሯል:: ድርጅቱም በአሸባሪነት ተፈርጇል:: አንዳርጋቸው በሽብርተኝነት ተፈርጇል:: በዚሁ አግባብ ነው እንግዲህ ከየመን ተይዞ፣ ታስሮ የሞት ፍርድ የተፈረደበት:: ሕጉ ምን ይላል? ወይም ደግሞ የተፈረደበት ምን ነበር? የሚለው ሳይሆን የአንዳርጋቸው ፅጌ የትግል መሠረታዊ ዓላማና ግብ ምንድነው? የዜጎች መብትና ነፃነት የተከበረበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይገንባ የሚለው ነውና አንዳርጋቸው ሲታሰር የታሰረው አንድ ግለሰብ ወይም አንድ የፖለቲካ ቡድን መሪ አይደለም፤ የህዝቡ ጥያቄ ነው የታሰረው፤ ዴሞክራሲ ነው የታሰረው፤ ነፃነት ነው የታሰረው:: የህዝቡ ጥያቄ ምላሽ እስካላገኘ ድረስ በአገሪቱ ውስጥ የተከሰተውን ግጭትና አለመረጋጋት ማስወገድ እንደማይቻል መንግሥት ተገንዝቦ እነዚህን የፖለቲካ መሪዎች የለቀቀበት ሁኔታ ነው ያለው:: ስለዚህ ህዝቡ ነው የተፈታው ማለት እንችላለን::

**ግዮን፡- የአንዳርጋቸው ፅጌ ከእስር መፈታት ጠቅላይ ሚንስትር ዓቢይ አህመድ "የፖለቲካ ምህዳሩን እናሰፋለን፤ በውጪም በሀገር ውስጥም ካሉት ጋራ ተረዳድተን እንሠራለን" ያሉበትን መንገድ ያሳምናል ብለህ ታምናለህ?**

**ስዩም፡-** የፖለቲካ ምህዳሩን ማስፋት ሲባል ነፃና ገለልተኛ የሆነ የዴሞክራሲ ተቋማትን መገንባት፣ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች እንዲካሄዱ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣ ከመንግሥት አመለካከት ነፃ የሆኑ የዴሞክራሲ ተቋማትን ማጠናከር እና መሰል ነገሮችን ያካትታል:: ይህ እንዳለ ሆኖ ግን በቅድሚያ የመጀመሪያው ተግባር ከገዢው ፓርቲ የተለየ የፖለቲካ አቋምና አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ወገኖች በሀገሪቱ ላይ በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ ማስቻል ሲሆን፣ በዚህ ረገድ የአንዳርጋቸው ፅጌ መፈታት አንዱ ነገር ነው:: ከዚህ አኳያ እነእስክንድር ነጋን፣ እነአንዷለም አራጌን ስትመለከት ተጨባጭ የለውጥ እየመጣ ነው ብለን ማለት እንችላለን:: አንዳርጋቸው ፅጌ እንዳይፈታ የሚፈልግ ወገን እንዳለ ሊሰመርበት ይገባል:: በዋናነት የህወሓት አባላትና ደጋፊ የሆኑ ወገኖች ይሄን ነገር በፅናት የሚቃወሙ ናቸው:: ዝም ብሎ ይህንን ህዝብ ለማስደሰት ብቻ የተወሰነ ውሳኔ ሳይሆን የተለያዩ ነገሮችን ጨምሮ ዲፕሎማቲክ ግንኙነቱን በተለይ የእንግሊዝ ዜጋ መሆኑ ከምግት ውስጥ ገብቶ የተለያዩ ጫናዎች እንደነበሩ ከግንዛቤ ማስገባት አለብን:: ስለዚህ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተወሰደው እርምጃ በእውነቱ ሊበረታታና ሊደነቅ የሚገባ ነው:: የአገሪቱን የፖለቲካ ምህዳር ከማስፋት አንፃር ተጨባጭ የሆነ ለውጥ ሊያስገኝ የሚችል ነው::

**ግዮን፡- ይህ ነገር ከተጀመረ በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው ድርድር ይቀጥላሉ ነው የምትለው?**

**ስዩም፡-** አዎ! አሁን የፖለቲካ መሪዎች መፈታታቸው ብቻ አይደለም፤ ማህበረሰቡ በጠቅላላ እየተፈታ እኮ ነው:: ህዝቡም ሀሳቡን፣ ነፃነቱን፣ ዴሞክራሲያዊ መብቱን ለማስከበር እንዲንቀሳቀስ ሁኔታዎች እየተፈጠሩለት ነው:: መሪዎቹን የምታስረው እኮ ህዝቡ የፖለቲካ ጥያቄ እንዳያነሣብህና የህዝቡን የፖለቲካ ናቅናቄ ለማኮላሸት ነው:: እናም መሪዎችን ስትፈታ ህዝቡን ነው የፈታኸው:: ህዝቡ መብቱን ለማስከበር መንቀሳቀስ ይችላል:: ፍትሐዊ ሕገ መንግሥት እንዲረጋገጥ ይጠይቃል:: ከዚህ አንፃር ስታስበው የፖለቲካ ምህዳሩ እየሰፋ፣ ፍርሃት እየጠፋ ይሄዳል:: ከዚህ አንፃር ላለፉት 27 ዓመታት የኊሊት የነበረውን የፖለቲካ ጉዞ አቁሞ ወደፊት አንድ እርምጃ መራመድ ይቻላል::

**ግዮን፡- ብዙ ሰዎች እንደሚሉት መፈታት ብቻ አይደለም፤ ማንኛውም ሰው የታሰረበት የራሱ ዓላማ አለው፤ ቁጭ ብሎ ተደራድሮ ሀገሪቱ ላይ ሰላማዊ ነገር እንዲፈጠር ስለሚፈልግ ነው:: ኢህአዴግ ፈርቻለሁና በሚል እስሮ በመፍታት የማያቆም ከሆነ ትግሉ ተጠናክሮ ይቀጥላል የሚሉ አሉ፤ ያንተ ሀሳብ ምንድነው?**

**ስዩም፡-** ይሄ በጣም ትክክል ነው፤ አንደኛው ነገር የፖለቲካ መሪዎች የሚፈቱት ሲጀመር መታሰር ስላልነበረባቸው፣ መታሰራቸውም ስህተት ስለነበር ነው:: ስለዚህ ያሰራቸው ማነው ስንል መንግሥት ነው፤ ያሰራቸውም በስህተት ነው:: አሁን መንግሥት እነዚህን ሰዎች በመፍታቱ ከዚህ በፊት የፈጠራቸውን ስህተቶች እያስተካከላቸው ነው:: ሆኖም ግን ይህ የለውጥ መጀመሪያ እንጂ የለውጥ እርምጃ አይደለም:: በተጨባጭ ሥር ነቀል ለውጥ ሊመጣ የሚችለው እነዚህ የፖለቲካ መሪዎች፣ የመብት ተሟጋቾች፣ ጋዜጠኞች፣ ጦማርያን የታሰሩበትን ምክንያት በማወቅ ሲሆን የታሰሩበት ምክንያትም የህዝቦች መብት፣ ነፃነትና ፍትሕ እንዲረጋገጥ ዴሞክራሲ እንዲሰፍን የሕግ የበላይነት እንዲከበር የሚል ነው::

እነዚህ የፖለቲካ መሪዎች የታሰሩት ይህንን ጥያቄ በማንሳታቸው ነው:: አሁን እነዚህ ሰዎች ተፈትተዋል:: ይህ አንድ እርምጃ ነው፤ ስለዚህ የታሰሩበትን ዓላማ ለማሳካትና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ እድል ይፈጥርላቸዋል:: ህዝብም መብቱን ለማስከበር መጠየቅ ይጀምራል:: ስለዚህ የፖለቲካ ንቅናቄው መሽከርከር ይጀምራል ማለት ነው:: የጠቅላይ ሚኒስትር ዓቢይ ካቢኔ ወይም አመራር ለውጥ ያመጣል ብሎ ዳር ቆሞ መጠበቅ ሳይሆን የተፈቱ ጋዜጠኞችም ሥራቸውን ይሥሩ፤ የተፈቱ የፖለቲካ መሪዎችም መተማመንን ይዝሩ፤ የሲቪል ማኅበራትም የሚጠበቅባቸውን ሚና ይወጡ:: ውጪ የቆሙ ሚዲያዎችም ወደሀገር ውስጥ መጥተው ለማህበረሰቡ በማሳወቅ ሚናቸውን ይወጡ:: የኢህአዴግም መንግሥት እንደመንግሥት ያፈረሳቸውን የዴሞክራሲ ተቋማት መልሶ ይሥራ::

ስለዚህ ድርሻው የመንግሥት ብቻ አይደለም፤ የሁላችንም ነው:: ከዚህ በፊት ዴሞክራሲን ለማምጣት የተሣነን መሪዎች ስለታሰሩ ነው፤ አሁን እነዚህ ሰዎች ተፈትተዋል:: ከስደትም እየመጡ ነው ያሉት:: ስለዚህ በፖለቲካ ውስጥ የሚጠበቅባቸውን ሚና ይወጡ:: የዶክተር ዓቢይ አመራርም በተግባር ሊያስተካክላቸው የሚጠበቅበት ►





በዋናነት ያፈረሳቸው የፖለቲካ ተቋማት እንዲሁም ደግሞ አፋኝ የሆኑ አዋጆች አሉ:: የፀረ ሽብር ሕጉ አለ:: የበጎ አድራጎት መመሪያ አለ:: የሚዲያ አዋጅ አለ:: እንዲሁም የደህንነት ተቋም አሠራር አለ፤ ከዚህ አልፎ ኃላፊነትና ተጠያቂነት አለ:: የሕግ የበላይነት መስፈን አለበት:: ለህዝቡ ተጠቃሚነት መንቀሳቀስ አለባቸው:: በኢኮኖሚው በራሱ እድገቱን በተጨባጭ ማስመዝገብ አለበት:: እነዚህ ነገሮች ይጠበቃሉ:: እነዚህ እንግዲህ በመንግሥት ደረጃ የሚጠበቁ ሥራዎች ሲሆኑ፣ ሌላው የፖለቲካ ማህበረሰብም የሚጠበቅበት ሥራ አለ:: አሁን በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በጋዜጠኞችና በሌሎች እየታየ ያለው ጠባቂነት ነው:: ዳር ቆሞ ይህን ያድርግ፣ ይተው ከማለት በዘለለ በተጨባጭ እያደረጉት ያለ ነገር የለም:: ከአዲስ አበባ ወጥተው በመላው ሀገሪቱ መዋቅራቸውን እየዘረጉ ነወይ? በአደረጃጀታቸው እየሠሩ ነወይ? ስንል ይህ ሁኔታ የለም:: ስለዚህ እኛም የቤት ሥራችንን መሥራት አለብን ብዬ ነው የማምነው::

**ግዮን፡- ግንቦት 21/2010 ዓ.ም. ክሳቸው የተቋረጠው የፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋና የጃዋር መሃመድ እንዲሁም የኦ ኤም ኤን እና የኢሳት ቴሌቪዥን ጣቢያዎች ክስ መነሣትን እንዴት ታየዋለህ?**

**ስዩም፡-** ይህ ደስ የሚል ዜና ነው፤ ወደሀገሪቱ ውስጥም መጥተው ቢሮአቸውን ከፍተው እንዲሠሩ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥሪ ቀርቦላቸዋል::

ኢሳትም ሆነ ኦ ኤም ኤን ከዚህ በኋላ አዲስ አበባ ውስጥ ቢሮአቸውን ከፍተው ነፃና ገለልተኛ የሆነ ዘገባ በቀጥታ ላለማቅረብ ምንም ምክንያት ያላቸው አይመስለኝም:: ከዚህ በኋላ መጥተው የማይሠሩ ከሆነ ከራሳቸው ድክመትና የሚጠበቅባቸውን ግዴታ ካለመወጣት በዘለለ ሌላ ተጨባጭ ምክንያት ማቅረብ የሚችሉ አይመስለኝም::

**ግዮን፡- ይህንን ማመን ይቻላል፤ ኢህአዴግን ላለፉት 27 ዓመታት ጠንቅቀው የሚያውቁት በመሆኑ ጥሪ ስለተደረገ ብቻ ትክክለኛው ነገር ይደረጋል ተብሎ ይታመናል? ቅድመ ሁኔታ መኖር የለበትም?**

**ስዩም፡-** ሁሉም ነገር ተመቻችቶና ተስተካክሎ ባለበት ሁኔታ መጥተን እንኖራለን ብሎ መጠበቅ በፍፁም አግባብነት የለውም:: ምክንያቱም አውቃለሁ፤ ይህ መንግሥት ጨካኝና አፋኝ ነው፤ ከሃዲም ጭምር ነው፤ በተግባርም አይተነዋል:: ውጪ ያለው ማህበረሰብ የራሱን ሚናና አስተዋፅዖ አበርክቷል:: ሆኖም ግን አገሪቱ ውስጥ እኔና አንተ እዚህ ኢህአዴግ ፊት ቆመን ክህደቱንም፣ ዱላውንም፣ መከራውንም እየተቀበልን ኖረናል፤ ስለዚህ ዴሞክራሲው ተረጋግጦ ለመኖር የሚመጣበት ከሆነማ እሱ ሽርሽር ነው:: ይህ ግን ፖለቲካ ነው፤ ፖለቲካ ውስጥ መሥራት የማትችልበት ሁኔታ ብቻ ሲኖር ነው አገር ጥለህ የምትሰደደው:: ልትሠራ የምትችልባት አንዲት ቀዳዳ ከተፈጠረች ያቺን ቀዳዳ በአግባቡ ተጠቅመህ ከህዝቡና ከሀገሪቱ የሚጠበቅብህን ግዴታ መወጣት መቻል አለብህ:: የኢህአዴግ መንግሥት ገና ቃሉን ሊያጥፍ ይችላል ብሎ ዳር ቆሞ ማህበረሰቡን ለተቃውሞ መቀስቀስ ፈፅሞ ተቀባይነት የለውም:: በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ዋጋና ተቀባይነት ያሳጣቸዋል:: ከሀገር እንዲሰደዱ ያደረጋቸው መንግሥት ወደሀገራችሁ ኑ ብሏቸዋል:: አሸባሪ ተብሎ የተፈረጀው የቀድሞው የኦነግ አመራሮች ሀገር ውስጥ ገብተዋል:: አሸባሪ ተብሎ የሞት ፍርድ



የተፈረደበት አንዳርጋቸው ፅጌ ተፈቷል:: ይህንን በተግባር አይተናል:: ከእስር ቤት ገብተን ወጥተናል:: ይህ ሂደት እንዳይቀለበስ ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል የሚጠበቅበትን መወጣት አለበት:: የኢህአዴግ መንግሥት ቃሉን ያከብራል ብሎ ዳር ቆሞ መጠበቅ በፍፁም ኃላፊነት የጎደለው ነገር ነው::

**ግዮን፡- የአንዳርጋቸው ፅጌ መፈታት የማን ተፅዕኖ ነው ትላለህ?**

**ስዩም፡-** ባለፈው እነበቀለ ገርባና እነእስክንድር ነጋ ሲፈቱ ተናግሬያለሁ:: እነዚህ ሰዎች የራሳቸውን ጥቅም ለማስከበር አይደለም አደባባይ የወጡት:: የራሳቸውን ጥቅም ለማስከበር ብለው አይደለም ከዚህ ጨቋኝ መንግሥት ጋራ ፊት ለፊት የተጋፈጡት:: እነዚህ ሰዎች የዜጎች መብትና ነፃነት ይከበር ብለው አደባባይ ወጥተው ነው መሥዋእት የከፈሉት፤ ለእስርና ለስደት፣ ለመከራም የተዳረጉት:: ጥያቄው የእነሱ የግል ጉዳይ አይደለም፤ የህዝብ ጉዳይ ነው፤ የህዝብ ጥያቄ ነው፤ እነሱ ሲፈቱ ህዝቡ ነው የሚፈታው:: አንዳርጋቸው ፅጌ የፖለቲካ መሪ ነው፤ ያነሳውም የህዝብ ጥያቄ ነው፤ የተፈታውም የህዝብ መሪ በመሆኑ በህዝብ ጥያቄ እንጂ በኢህአዴግ መንግሥት ፈቃድና ችሮታ፣ አሊያም በይቅርታ ወይም በሌላ ነገር አይደለም:: በህዝባዊ አመፅና ተቃውሞ በተፈጠረ ጫናና ግዴታ አስገዳጅ ሁኔታ ስለሆነ ያስፈታው ህዝቡ ነው:: አንዳርጋቸው ፅጌን ጨምሮ በስደት ላይ ያሉት የፖለቲካ መሪዎች ሁሉም ወደዚህ ደረጃ አደረሱት:: አንዳርጋቸው ፅጌን መፍታት ብቻ አይደለም ዶ/ር ዓቢይን ጨምሮ አዲሱ የመንግሥት የፖለቲካ ቡድን በአጠቃላይ ዛሬ የአመራርነት ሚና የያዘው በህዝቡ አመፅ፣ በህዝቡ ተቃውሞ፣ በህዝቡ መሥዋእትነት ነው::

**ግዮን፡- ጠቅላይ ሚንስትሩ አቶ አንዳርጋቸውን በቤተ መንግሥት መጋበዛቸውን እንዴት ትረዳዋለህ?**

**ስዩም፡-** አንዳርጋቸው እንደሚታወቀው የሞት ፍርድ የሚጠብቅ ግለሰብ ስለነበር ይቅርታ ከማግኘቱ በላይ ቤተ መንግሥት ተጠርቶ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ማግኘትና መወያየት መቻሉ፤ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ለዘመናት እየተከታተለ ሲመጣ የነበረውን የቂም በቀል ሰንሰለት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሰበረው ይመስለኛል:: ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ጀምሮ ሥርዓቱን የተቃወሙ ሰዎች እነ መንግሥቱ ንዋይ፤ እነ በላይ ዘለቀ፤ እነ ጀነራል ደምሴ ቡልቱ፤ በኢህአዴግ ዘመን ደግሞ እነፕሮፌሰር አስራትና ሌሎችም የሞቱት እንዲሁም አቶ አንዳርጋቸው ፅጌና ዶ/ር ብርሃኑ ለእስርና ለስደት የተዳረጉበት ምክንያት መንግሥትን በመቃወማቸውና የተለየ የፖለቲካ አቋምና አመለካከት በማራመዳቸው ነው:: ካለፉት ሦስት ሥርዓቶች በጣም የተለየ አካሄድ ነው አሁን ያለው:: ይህ ደግሞ ለሀገሪቱ ትልቅ ፖለቲካዊ ፋይዳ ይኖረዋል::

**ግዮን፡- አንዳርጋቸው ጽጌ በምን ጉዳይ ላይ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር እንደተወያዩ ሊገልጹ አልፈለጉም፤ ለምን ይመስልሃል?**

**ስዩም፡-** በመጀመሪያ ደረጃ አንዳርጋቸው ፅጌ ማንን ወክሎ ነው የሚናገረው? የግንቦት ሠባት መሥራችና መሪ ነው:: ግንቦት ሠባት ደግሞ አሁን በሀገሪቱ ተግባር ላይ ባለው ሕግ መሠረት በአሸባሪነት የተፈረጀ ነው:: የግንቦት ሠባትን መሪ ቤተ መንግሥት ቁጭ አድርገህ አናግረህ፤ በተወያየበት ጉዳይ ላይ ሀሳብ፣ አስተያየት፣ ጋዜጣዊ መግለጫ እንዲሰጥ መጠበቅ የለብንም:: ይሄ የለውጥና የትብብር ምልክት ነው::





ክንፈሚካኤል ደበበ(አበበ ቀስቶ)

# የአንዳርጋቸው የአራት ዓመት የእስር ቤት ቆይታ ምን ይመስላል

ቅዳሜ ግንቦት 18/2010 ዓ.ም. ማለዳ ላይ የአቶ አንዳርጋቸው ፅጌ የመፈታት ዜና አየሩን ሁሉ ሞልቶታል:: የእኔም ጆሮ ይህን ዜና በተመስጦ፣ ባለማመንና በማመን አድምጦታል:: ሁኔታውን በአካል ለማየት ግን ቃሊቲ መሄድ እንዳለብኝ ወሰንኩ:: እናም ማልጄ ደረስኩ፤ ለምን እንዳትሉኝ:: ከሦስት ወራት በፊት በየሳምንቱ ቅዳሜ ከሰዓት በቀዳዳ ሳየው የነበረውን የነጻነት ታጋይ አንዳርጋቸው ፅጌን ሲፈታ በአካል ተገኝቶ ለማየት በመጓጓት ነው:: ግን፣ ግን

የአቶ አንዳርጋቸውን የመያዝ ዜና እኔና ጓደኞቼ የሰማነው በከፍተኛ ኃዘን ውስጥ ሆነን በዝዋይ ወህኒ ጨለማ ቤት ውስጥ ታስረን በነበርንበት ጊዜ ነው:: እንዲህ ዓይነቱን ዜና እስር ቤት ውስጥ ያውም ጨለማ ቤት ታስሮ መስማት ሲበዛ በጠና ያማል:: እናም ዜናውን የሰማነው በሙሉ አመመን ብቻ ሳይሆን አበድን ማለት ይቻላል:: ይህ ስሜት የእኛ ብቻ ሳይሆን የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ስሜትና ሕመም ነበር ብል ዕውነቱን ተናገርኩ እንጂ አላጋነንኩም::

ለመግቢያ ያህል ይቺን ካልኩ የዛሬው ጽሑፌ ትኩረት ወደሆነው ጉዳይ ሳመራ በዛሬው ጽሑፌ አቶ አንዳርጋቸው ቃሊቲ ከመምጣታቸው በፊትና ከመጡ በኋላ ያለውን ነገር አጠር አድርጌ ላሳያችሁ::

## ለአቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ማሰሪያ የሚሆን ቤት መረጣና ዝግጅት

በታኅሣሥ ወር 2007 ዓ.ም. የመጨረሻ ቀናት ላይ ቃሊቲ ዋይት ሐውስ /ጨለማ ቤት/ ሳለን የተለዩ አዳዲስ ፊቶች ማየት ጀመርን:: ለምን ይሆን? የሚል ጥርጣሬም አደረብን:: ግን ለማወቅ አልቻልንም:: አንድ ቀን እኔ ለሕክምና ሆስፒታል በሄድኩበትና አቶ ገ/ዋሕድ ፍ/ቤት በሄዱበት ቀን የደኅንነት ሰዎች ወደኛ እስር ክፍል መጡ:: እነሱ ከመግባታቸው በፊት ግን ኢ/ር መስፍን አበበ ዕቃውን ይዞ ከክፍሉ እንዲወጣና እነአንዱዓለም አራጌ ያሉበት የእስር ክፍል እንዲገባ ተደረገ:: ከዚያ ቤቱ ባዶ ሲሆን የመጡት ሦስት የአቶ ጌታቸው አሰፋ የደኅንነት ሠራተኞች የእስር ክፍላችንን በካሜራ ቀርፀው ፎቶ አንሥተውት ሄዱ::

> ግንቦት 21 ቀን 2010 ዓ.ም. በአባታቸው ቤት በአካል አገኘሁዋቸው፤ በዓይኔም አየሁዋቸው፤ አቀፍኳቸው ሳምኳቸው ግን አልወጣልኝም:: ለምን? በእስር ዘመን ታሪኬ እንደርሳቸውና እንደ ኢ/ር መስፍን አበበ በግፍ የታሰረ ሰው አለ ብዬ አላምንም:: ሁሌም በቀዳዳ ባየሁዋቸው ቁጥር በቁጭት እበግንና እብከነከን ነበር

ይህ በሆነ በአራተኛው ቀን ጠዋት ሱፐር ኢንቴንዳንት ሐጎስ ወዳጄ መጣና ወደ ክፍላችሁ ግቡ ብሎ በሩን ቆለፈብን:: ከዚያም አንዱዓለም አራጌና እና እስክንድር ነጋ መጥተው እኛ ግቢ እንዲገቡ ተደረገና በሩ ተዘጋባቸው:: ቀጥሎ ልክ እንደኛው ቤት ሁሉ የእነሱም የእስር ክፍሎች በቪድዮ ካሜራ ተቀርፀው ፎቶ ተነሡ::

ከዚያ በ15ኛው ቀን ጥር 17/2007 ዓ.ም እሑድ ቀን ከሰዓት በኋላ ደኅንነቶች እየተተራመሱ መጥተው ዕቃችሁን ይዛችሁ ውጡ አሉን:: እኛም እቃችንን ይዘን ወጣን፤ ከኢንጂነር መስፍን አበበ በቀር ሁላችንም የዋይት ሐውስ እስርኞች ለሰዓታት አንድ ላይ ሆንን:: ከሠባት ሰዓት ቆይታ በኋላ እኔ፣ እስክንድር ነጋ፣ አቶ መላኩ ተፈራ፣ አቶ ገ/ዋሕድ፣ ሌ/ኮ ጌታቸው ብርሌ ዕቃችንን ይዘን ወደ ዞን 3፣ 6ኛ ቤት እንድንሄድ ሲደረግ፤ አንዱዓለም አራጌ እና አቶ መላኩ ፈንታ ከኢ/ር መስፍን አበበ ጋር አንድ ላይ ሆኑ፤ በቃ ተለያየን::

እኛም ቤቱ ለምንና ለማን ቢፈለግ ነው እንድለቅ የተደረገው? በቃ አንዳርጋቸው ሊመጣ ነው ብለን ማሰላሰልና መጠርጠር ያዝን:: ከዚያም በቅርብ ቀናት ውስጥ የተለቀቀው ቤት ባለበት ሁኔታ ይታደስ፣ ይሠራ ያዘ:: ለራሱ የሚሆን የደኅንነት ቢሮ ለብቻው ተሠራለት፤ በዚህን ጊዜ ለአንዳርጋቸው ነው የሚል ጥርጣሬያችን ወደ ዕምነት ተቀየረ፤ ቤቱም ከታደሰ በኋላ ከስድስት ወር በላይ ባዶውን ቆየ፤ በኋላም የገመትነው ዕውን ሆነ::

## የአቶ አንዳርጋቸው ወደ ቃሊቲ መምጣት

በሐምሌ ወር 2007 ዓ.ም. መጀመሪያ አካባቢ አንዳርጋቸው ወደ ቃሊቲ እንደመጣና ዋይት ሐውስ /ቅጣት ቤት/ እንደገባ በጭምጭምታ ሰማን፤ ማጣራት ግን አቃተን:: በዚሁ ወር ▶

አንዳርጋቸው ከሁለት ሰዎች ጋር አንድ ላይ መታሰሩን መረጃው ደረሰን። ይህን እንዴት ማጣራት እንደሚቻል ግራ ገባን። በዚህ ሁኔታ እያለን የደኅንነት መ/ቤት ምን ሊያስቀምጥ እንደፈለገ ባናውቅም አቶ አንዳርጋቸው ለሦስት ቀናት ወደሌላ ቤት ተዛወረ፤ በዚህን ጊዜ አቶ አንዳርጋቸውን አንዱዓለም አራጌ በግድግዳ በኩል አነጋገራቸውና መረጃ ተለዋወጡ። እኛም አቶ አንዳርጋቸውን ቃሊቲ ስለመግባቱ በአንዱዓለም በኩል ትክክለኛውን መረጃ አገኘን።



### ሁለቱ የአቶ አንዳርጋቸው ልዩ የደኅንነት ጠባቂዎች

አቶ አንዳርጋቸው ወደቃሊቲ እንደመጡ ወያኔ ልዩ ጠባቂዎችን ከራሷ ሰዎች መልምላ መደበች። ምግብ እንኳን የሚያቀብሏቸው እነሱ ብቻ ናቸው። ካለእነዚህ ሰዎች የአቶ አንዳርጋቸው በር አይከፈትም።

1ኛ. ዋና ኦፊሰር ብርሃኔ ይባላል። ይህ ሰው ከህወሓት ነባር ታጋዮች አንዱ ነው። ላላፉት አራት ዓመታት አንዳርጋቸው ፅጌን በታማኝነት ሲጠብቅ ሲቆጣጠርና በሩን ላዩ ላይ ሲዘጋና ሲከፍት የነበረ የወያኔ ሰላይ ነው። ሰውዬው ያልተገራ አንደበት ያለውና በዕውቀት ያልገፉ ሲሆን ከዚህ ሥርዓት ውጪ ሕይወት ያለች አይመስለውም። በዚህም የተነሣ ተመርጦ ላለፉት አራት ዓመታት ሲያሰቃየውና ሲያበሳጨው ኖሯል።

2ኛ. ኦፊሰር በሪሁን ይበላል። ይህ ሰው እጅግ ሲበዛ ዝምተኛ፣ ነገር ግን እጅግ አደገኛ ሰው ነው። ለሥርዓቱ ባለው ታማኝነት የተነሣ የተመደበ መሆኑን ብናውቅም እንደሰው የሰው መራራትና ማዘን እንደሚገባው ባለመረዳቱ ግን እናዝናለን። ይህ ሰው ከአቶ አንዳርጋቸው ፅጌ መግባባት የሌለውና እስከመጋጨት የደረሰ፣ የሥርዓቱ ታማኝ ለመምሰል ሲል ያልተገባ ተግባር ሲፈጽማባቸው እንደነበር ይታወቃል። ኃዘኔታም ከፊቱ ላይ አይነበብም።

### አቶ አንዳርጋቸው ላይ የተመደቡ የእስረኛ ሰላዮች

ወያኔ አቶ አንዳርጋቸውን ካሰረች በኋላና የራሷን ታማኝ ሰላዮች በጠባቂነት ከመደበች በኋላም የውስጥ እንቅስቃሴያቸውን ለመከታተል ደግሞ ከእስረኛው መካከል ሁለት ሰላዮችን መርጣ መደበች እነሱም፦

1ኛ/ አቶ አሰፋ ቁሴ ናቸው። እኚህ ሰው ከመታሰራቸው በፊት በዶ/ር መረራ ጉዲና የሚመራው የኦብኮ አባል የነበሩና ንቁ ተሳትፎ ያደረጉ፤ በጊዜው ጠንካራ ታጋይ እንደነበሩ ለአንድ ዓመት ያህል ከእኛ ጋር ታስሮ የተፈታው ኦልባና ሌሊሳ አጫውቶኛል። ነገር ግን በደረቅ ወንጀል ተከሶ ቃሊቲ ከገባ በኋላ ያን ጥንካሬውን የት እንዳደረሰው አይታወቅም። ምክንያቱም ይህ ሰው በቃሊቲ ዞን አንድ በነበረበት ጊዜ የወያኔ ሰላይ ነው በሚል በመላው እስረኛ በእጅጉ የሚጠላ ሰው ነው። በዚህም የተነሣ ቀድሞ የነበረውን የፖለቲካ ስብዕና በገዛ እጁ አጥቶታል። ወያኔም በሚገባ አጥንታ ነው ከታማኝነቱ የተነሣ አንዳርጋቸው ጋር የመደበችው። እሱም ታማኝነቱን ለማረጋጥ ሲል አቶ አንዳርጋቸውን ሲረብሽና ሰላም ሲነሳው ከርሟል። የዚህን ሰው ታሪክ አንድ ቀን አቶ አንዳርጋቸው እንደሚያወጋን አምናለሁ። አሁን እንደሰማሁት ወደዞን አራት ተቀይሯል። አቶ አሰፋ ቁሴ ለአቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ብቻ ሳይሆን የዞን አንድ እስረኛ አስተዳደር ሆኖ ሲሠራ ከወያኔ በላይ ታሳሪውን ሁሉ ሲረብሽና ሲያምስ የነበረ ሰው ነው።

2ኛ/ ዳዊት ድባቤ፦ ይህ ልጅ አቶ አንዳርጋቸው ጋር እንዴት ሊመደብ እንደቻለ የሁሉም እስረኛ መነጋገሪያ ነው። ይህ ሰው በእስር ቤት ውስጥ የሚታወቀው ቀንደኛ የወያኔ ተቃዋሚ መሆኑን በየስብሰባው ላይ እስር ቤት ውስጥ፣ "የአማራ ተወላጆች መብት ተደፍሯል" እያለ ሲከራከር ነው፤ ነገር ግን ከወያኔ ጋር ምን እንዳፋቀራቸው ባናውቅም ወያኔ ለአገልጋይነት መርጣው ላለፉት አራት ዓመታት በአቶ አንዳርጋቸው ለወያኔ ታዛዥና ታማኝ በመሆን ታሪክ ይቅር የማይለውን ስህተት ፈጽሟል።

የሚገርመው እነዚህ ሁለት ሰዎች ፍጹም የማይግባቡ በጠላትነት የሚታዩ ሲሆን በእነሱ ጠብና አንቧጓሮ የተነሣ የአቶ አንዳርጋቸው ሰላም ሲታወክ መክረሙን እናውቃለን።

ወያኔም ይህንን በሚገባ ስለምታውቅ ሁለት በጠላትነት የሚፈላለጉ ባላንጣዎችን ለአንድ ዓላማ አቶ አንዳርጋቸው ጋር በመመደብ አቶ አንዳርጋቸውን ሰላም አሳጥታቸው ኖረች።

### የአቶ አንዳርጋቸው የቤተሰብ ጥየቃ ሁኔታ

አቶ አንዳርጋቸው ከቤተሰብ ጋር የሚገናኙት በሳምንት አንድ ቀን ቅዳሜ ከሰዓት ሲሆን ላለፉት ሦስት ዓመታት እንዲጠይቋቸው የተፈቀደላቸው አባታቸው አቶ ፅጌ ሀብተ ማርያምና ወይዘሮ ታደለች ብቻ ናቸው። ከቤተሰብ የሚገናኙትም በልዩ ሁኔታና ጥበቃ ነው። ሁልግዜ ከእስር ክፍላቸው ወደ ቤተሰብ ጥየቃ ቦታ የሚሄዱት በመኪና ሲሆን ሁሌም ቢሆን በስህተት ደኅንነት ከአጠገባቸው ለደቂቃ አይርቅም። የሚያሳዝነው በሳምንት አንድ ቀን እየተየጠቁ እንኳን የሚፈቀድላቸው የጥየቃ ሰዓት 30 ደቂቃ ብቻ ነው።

አባታቸው በዚህ ዕድሜያቸው ለብቻቸው እንዲጠይቋቸው መደረጉ የግፎች ሁሉ ግፍ ነው ማለት ይቻላል። እህቶቻቸውም ሆኑ ሌሎች ቤተሰቦቻቸው እንዲጠይቋቸው አይፈቀድላቸውም።

### ከአቶ አንዳርጋቸው ጋር ስለመተያየት

አቶ አንዳርጋቸው በሕይወት መኖራቸውን ለማረጋገጥ በጣም ሲጓጉ ከነበሩት መካከል አንዱ ነበርኩ። ይህም ጉጉቴ ዕውን ሆኖ አቶ አንዳርጋቸውን ለመጀመሪያ ጊዜ ኅዳር 8 ቀን 2007 ዓ.ም. በቀዳዳ በኩል አየሁዋቸው። ለሌሎችም ጓደኞቼን ጠርቼ አሳየሁዋቸው፤ በጣም ተደሰትን፤ በሕይወት ስላገኘናቸውም የመፈታት ያህል አስደሰተን።

ከዚህ በኋላ ሁሌም በሳምንት አንድ ቀን ቅዳሜ ቤተሰብ ጥየቃ ሲወጡም ሆነ ሲገቡ በቀዳዳ ስናያቸው ኖረናል። ይህም ስለሳቸው በቅርበት ለመከታተል አስችሎናል።

በመጨረሻም የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ በቀዳዳ ሳያቸው የነበርኩትን ወዳጄን አቶ አንዳርጋቸው ፅጌን ግንቦት 21 ቀን 2010 ዓ.ም. በአባታቸው ቤት በአካል አገኘሁዋቸው፤ በዓይኔም አየሁዋቸው፤ አቀፍኳቸው ሳምኳቸው ግን አልወጣልኝም። ለምን? በእስር ዘመን ታሪኬ እንደርሳቸውና እንደ ኢ/ር መስፍን አበበ በግፍ የታሰረ ሰው አለ ብዬ አላምንም። ሁሌም በቀዳዳ ባየሁዋቸው ቁጥር በቁጭት እበግንና እብከነከን ነበር። ለእሱ ምን ይሳነዋል አንድዬ ሁሉንም አሳካልን። "ሁሉ በእርሱ ሆነ" እንዲል መጽሐፍ ሁላችንም አንድዬን አጅበን ጨፈርን፣ ተደሰትን፣ የደስታ ርችት ተኮስን፤ አቤቱ ምን ይሳንሃል፤ ክብር ምስጋና ሁሉ ያንስሃል።



# “የተሻለ ሕይወት መኖር እየቻለ በረሃ መግባቱን ሳስብ ይጨንቀኛል”

## እማዋይሽ አለሙ



***ግዮን፡- እናንተ በአንዳርጋቸው የፖለቲካ ድርጅት በግንቦት ሠባት ተከሳችሁ ለዓመታት ለእስር ተዳርጋችሁ ተፈታችኋል:: እናንተ እስር ላይ እያላችሁ አንዳርጋቸው ሲያዝ ምን ዓይነት ስሜት ተሰማሽ?***

**እማዋይሽ**፡- እኔ በጣም አዝኛለሁ:: በእኔ ላይ፣ በወንድሞቼ ላይ የደረሰውን መከራ ሳስብ ምን እንደሚያደርጉት ሳስብ በእጅጉ በጣም አዝን ነበር:: እኔ ራሴ ተይዤ ያ ሁሉ መከራና ስቃይ ደርሶብኝ፣ ያሳለፍኩትን ያንን ሁሉ መከራ ከቁብም አልቆጠርኩት፤ ምክንያቱም የእርሱ ደግሞ የከፋ እንደሚሆን ስላወቅኩኝ:: ገና ከመነሻው ዓለም አቀፍ ሕግ ጥሰው በየመን አየር ማረፊያ ላይ ነው አፍነው ያመጡት:: እሱን ለማምጣት ከፍተኛ ኦፕሬሽን ነበር፤ ብዙ ነገር ከፍለዋል፤ ስለዚህ ምን ያደርጉታል እያልኩ ነበር ስጨነቅ የነበረው:: እኔ እንኳን ብዙ መከራ ሲፈራረቅብኝ አላለቅስም፤ የአንዳርጋቸውን መያዝ ስሰማ ግን አልቅሻለሁ:: አሁን ለእኔ ያ ሁሉ ነገር ከሚደርስብኝ ቢገድሉኝ ምንም ማለት አልነበረም:: ምን ያህል ሰቆቃና ሥቃይ ያደርሱበት ይሆን እያልኩ እብሰለሰል ነበር::

***ግዮን፡- ከእስር ከፈተታችሁ በኋላ ግን የተከሰሳችሁበት ጉዳይ የሆነው አንዳርጋቸው አለመፈታቱን ስታውቂ ምን ተሰማሽ?***

**እማዋይሽ**፡- በመጀመሪያ ደረጃ እንደምትሰሙት ሰው አዲስ ሆነበት እንጂ እነዚያ ሦስቱ ድርጅቶች አንድ ላይ ተሰብስበው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሰማይ በታች ከምድር በላይ ያሉትን ነገሮች ሁሉ ተነጋግረውባቸው የፖለቲካ ፍርደኞችን በሙሉ እንደሚፈቱ ተናገሩ:: በሌላ ቀን ደግሞ በጊዜው የፖለቲካ ሐላፊ የነበሩት አቶ ሽፈራው ሽጉጤ በዝርዝር ሲናገሩ እስከ ነሐሴ መጨረሻ በሙሉ እንደሚፈቱ ተናግረው ነበር:: በዚህ መነሻ ይፈታል ብዬ እጠብቅ ነበር::

***ግዮን፡- ቅዳሜ ይፈታል ተብሎ ከሦስት ቀን ቆይታ በኋላ ማክሠኞ ሲፈታ በአንቺ ላይ ተስፋ የመቁረጥና የሥጋት ስሜት አልተሰማሽም?***

**እማዋይሽ**፡- በፍፁም ተስፋ አልቆረጥኩም፤ ነገር ግን አቶ አንዳርጋቸው እንግሊዛዊ ዜግነት አላቸው ይባል ስለነበር ምናልባት ከህዝቡ ጋር ሳያገናኟቸው በቀጥታ ወደ እንግሊዝ እንዲወጡ ያስገድዷቸው ይሆን? ከሚወዳቸው ህዝብና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሳያገናኟቸው ይቀሩ ይሆን? የሚል ጥርጣሬና ሥጋት ነበረብኝ::

***ግዮን፡- አቀባበሉን እንዴት ታዘብሽው? ከዓርብ እለት ጀምሮ ህዝቡ በከፍተኛ ዝግጁነትና ጉጉት ሲጠብቀው ቆይቶ እጅግ ብዙ ታዳሚ በተገኘበት ነው የጀግና አቀባበል የተደረገለት፤ ይህንን ጠብቀሽ ነበር?***

**እማዋይሽ**፡- እኔ ጠብቂያለሁ፤ ምክንያቱም እንኳን አቶ አንዳርጋቸውን እኔ ለምሳሌ ወደክልል ስገባ ያልጠበቅኩት ነበር:: የተፈቱ ሰዎች በየቦታው ድንኳን እየተጣለ ከፍተኛ የሆነ አቀባበል ነው የነበረው:: ስለዚህ አንዳርጋቸው ሲወጣ ደማቅ የሆነ አቀባበል እንደሚኖረው ጠብቄ ነበር:: አሸባሪ ያለን ገዥው እንጂ ህዝቡ እንዳልሆነ በደንብ አድርጌ አውቅ ነበር:: ለምን ቢባል ለህዝቡ ነው የጮህነውና መከራ ያየነው፤ ህዝቡ ነው ጮሆ ያስፈታን:: ሕፃናት እየሞቱ፣ ነፍስ ጡር ሴቶችና አረጋውያን እየተገደሉ ነው ያስፈቱት፤ ስለዚህ በተፈታ ጊዜ ባገኘው መድረክ ስሜቱን እንደሚገልፅ እርግጠኛ ነበርኩ:: እስካሁን ድረስ እዚህ ጎንደር ያለን የተፈታን እስረኞች ምሳ ግብዣ ፕሮግራም እንጠራለን:: ስለዚህ ህዝባችን ከጎናችን እንዳለ፣ እኛም እንደጮህንለት እጅግ ተረድቻለሁ::

***ግዮን፡- አንዳርጋቸውን እንዴት ትገልጪዋለሽ?***

**እማዋይሽ**፡- አቶ አንዳርጋቸው ከልጅነት ሕይወቱ ጀምሮ እጅግ በጣም አገሩን ህዝቡን የሚወድ ሰው ነው:: እንደምታየው ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለህዝቡ ያለውን ተቆርቋሪነት ነው የምትረዳው:: “ህዝቡ የፈለገውን ዴሞክራሲና ነፃነት አላመጣንለትም:: ይሄ አይደለም ህዝቡ የሚሻው” በሚል ፊት ለፊት የተጋፈጠ ሰው ነው:: ከዚህም አልፎ የተሻለ ሕይወት መኖር እየቻለ በረሃ መግባቱን ሳስብ እንዴት እንደምገልፀው ይጨንቀኛል:: ለእኔ አርአያዬ ነው፤ በቃ:: እኔ አሁንም እስከመጨረሻው በእርሱ ጎዳና፣ በእርሱ መንገድ መጓዝ ነው ምርጫዬ:: እኔ ሥልጣን ፈላጊ አይደለሁም፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ግን የሥልጣን ባለቤትነቱን አግኝቶ የራሱን አስተዳደር መርጦ እፎይታ እስኪያገኝ ድረስ የማርፍ አይመስለኝም:: ምናልባት የሰላም መንገድ ተፈቅዶአል፤ በሰላሙ መንገድ የምንታገል ከሆነ እጅግ በጣም ጥሩ ነው፤ ይህ ካልሆነ ግን በተቻለኝ ሁሉ ለዚህ ህዝብ ነፃነት እስከመጨረሻው መሥዋእትነት እንድከፍል አንዳርጋቸው ሞዴል ሆኖኛል::

***ግዮን፡- ከአንዳርጋቸው ጋር ወደፊት ምን ለመሥራት አስበሻል?***

**እማዋይሽ**፡- ይህን በሚመለከት አላውቅም፤ ከዚህ በኋላ አቶ አንዳርጋቸው ምን እንደሚያደርግ ለጊዜው የማውቀው ነገር የለኝም:: ለራሴ ግን አርአያ የሆነኝ ሰው ነው፤ ራሱን ለህዝብ አሳልፎ የሰጠ ነው:: ከጊንጥ፣ ከእባብ፣ ከበረሃ ጋር ታግሏል:: ነፃነት እስኪመጣ፣ እስከደሜ ጠብታ ድረስ ለዚህ ህዝብ ከጎኑ እቆማለሁ::

***ግዮን፡- ግንቦት 21 ማክሠኞ እለት አቶ አንዳርጋቸው በተፈቱ እለት በአሸባሪነት የተፈረጁት ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ እና ጃዋር መሃመድ እንዲሁም ኢሳት እና ኦ ኤም ኤን ክሳቸው መቋረጡን እንዴት ታይዋለሽ?***

**እማዋይሽ**፡- እነዚህ ሰዎችና ሚዲያዎች ክሳቸው ተነሣ ተባለ እንጂ እንደምታውቁት በምክር ቤት ግንቦት ሠባት በሽብርተኛነት ተፈርጇል:: ይህ እስካልተነሣ ድረስ የሽብርተኛነት ድርጅት አባል ነው የተባለ ሰው ክሱ ቢቋረጥለትም ምናልባት እነሱ በሚፈልጉት መንገድ ካልሄዱላቸው ችግር ይኖራል ብዬ ስለምገምት መልካምና አግባብ እንደሆነ አላስብም::

***ግዮን፡- አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር አንዳርጋቸውን ለመፍታት ብዙ ፈተናዎች ገጥመውኛል ብለዋል፤ ለመፈታቱም ብዙ ዋጋ እንደከፈሉ ተናግረዋል፤ ይህንን ነገር እንዴት ትመለከቺዋለሽ?***

**እማዋይሽ**፡- እንግዲህ ቀናነታቸው፣ መልካምነታቸው፣ ለሀገር አሳቢነታቸው ሁሉ መልካም ነው:: ይህንን ትግልም አድርገው ከሆነ ጥሩ ጅምር ነው፤ ነገር ግን ብቻቸውን የሚያመጡት ነገር የለም ብየ አስባለሁ:: የኢትዮጵያ ህዝብ እርሳቸውን ነው የሚጠብቃቸው፤ ከዳር እስከ ዳር እርሳቸውን ሲጠብቅ ግን፣ ለምሳሌ፡- ኮማንድ ፖስት ተብሎ በተቀነባበረ ድምፅ የፀደቀ አዋጅ እስካሁን እንደተቀመጠ ነው:: እነዚህን ነገሮች ስናይ ዶክተር ዓቢይ ብቻቸውን ምንም አያደርጉም:: ይህ ምናልባት የኢህአዴግ የማዘናጊያ ዝምታ ሊሆን ይችላል:: ኢህአዴግ ዝም ሲል የተሸነፈ መስሎን የምዘነጋ ከሆነ ትክክል አይደለንም፤ ለ27 ዓመት አይተነዋል:: ምርጫ 97 በራሱ ለእኛ አስተማሪ ነው:: በነገራችን ላይ እኛ በ98 ዓ.ም ቅንጅቶች ታስረው በነበረ ሰዓት “የኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ጋርድ” የሚል በአቶ ያረጋል ይማም ሊቀ መንበርነት በኔ ምክትልነት መሥርተን እነርሱን ለማስፈታት በኅቡዕ ተደራጅተን የህዝብ ድምፅ ይከበር በሚል ውስጥ ለውስጥ እንንቀሳቀስ ነበር:: ከዚያ በኋላ ከወታደሩ ጋራ ተገናኝተን ጠንካራ ሥራ እየተሠራ ነበር:: ያን ሁሉ ሦስት ዓመት ተጉዘን መጨረሻ ላይ ታሰርን:: ስለዚህ ይህ ሥርዓት አሰቃቂና በክህደት የተሞላ ታሪክ ያለው ድርጅት ነው፤ የሚያወሩትና ተግባራቸው በፍፁም አንድ አይደለምና እንዳንዘናጋ ነው የምለው:: በእርግጥ ዶ/ር ዓቢይ በንግግራቸው መልካምነትን የተላበሱ፣ በባህርያቸው መልካም ናቸው:: ነገር ግን ከማን ጋር ነው ያሉት? እርሳቸው ጠንካራ ከሆኑ አላሠራቸው ቢሉ እንኳ አላሠራኝ አሉ ካሉ ህዝቡ ቀጥ ብሎ ከእርሣቸው ጋር እንደሚቆም እርግጠኛ ነኝ:: ነገር ግን ህወሓቶች ባስቀመጡላቸው መስመር እሄዳለሁ ብለው ህዝቡን የሚያዘናጉት ከሆነ ደግሞ ሞት ነው::

***ግዮን፡- አንቺ እንደምትዪው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር እንዲሠፋ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መጀመሪያ መነሣት አለበት ነው?***

**እማዋይሽ**፡- በትክክል:: እንደማሣያ ልንገርህ፤ አሁን እኔ ባለሁበት አካባቢ በዚህ አላስፈላጊ አዋጅ ምክንያት በየጣቢያው የታሰሩ ልጆች አሉ:: አሁን እኮ እየዳኘን ያለው ወታደራዊ መንግሥት ነው:: በኮማንዱ ፖስቱ ስም እየገዛን ያለው ወታደራዊ ቡድኑ ነው:: በዚህ ምክንያት ብዙ እስረኛ አለ:: እስረኛ ተፈቷል ብለን መናገር የለብንም፤ አልተፈታም:: ከአማራ ክልል እየታፈኑ ትግራይ የታሰሩትስ? ደደቢት እኮ ማሠልጠኛ ብቻ አይደለም አሁን እስር ቤት ነው፤ እዚያ ያሉትንስ አስበናቸዋል? አይተናቸዋል? ዶ/ር ዓቢይ እነዚህን አይተውልናል? ስለዚህ እስከክረምት ድረስ በሙሉ እስረኞችን ይፈታሉ ብለን እንጠብቃለን እግዚአብሔር ይርዳቸው::

***ግዮን፡- በመጨረሻ ማስተላለፍ የምትፈልጊው ነገር አለ?***

**እማዋይሽ**፡- አዎ:: ኢትዮጵያውያን በጋራ፣ በአንድነት፣ በፍቅር ዶ/ር ዓቢይ እንዳሉት የእርቅ ጊዜው በተግባር እንዲሆን እንፈልጋለን:: በውጭም ሆነ በሀገር ውስጥ ዜጎች የሚጮሁት፣ የሚታገሉት ለሚቀጥለው ትውልድ የተረከብናትን አገር በሠላም ለማስረከብ ነው እንጂ ይህ ሁሉ ሰው ሥልጣን ሊይዝ አይደለም:: እውነተኛውንና የምንናፍቀውን ነፃነት አሁን ያሉት ገዥዎች ሥልጣን አፍቃሪ ሆነው አንለቅም ካላሉ በስተቀር ያንን ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ:: ለውጥ ሊመጣ የሚችለው ደግሞ እነሱ ሁልጊዜ ወንበር ቁጭ ብለው አይደለም:: ቶሎ ወደ ሠላም መምጣት አለብን:: የሀገር ነፃነት እንዲመጣ ፈጣን የሆነ እውነተኛ ህዝባዊ ውይይት ሊኖር ይገባል::



# የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ እገታ




የግንቦት 7 ዋና ጸሐፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ የመን ሰንዓ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርሱ በየመን የፀጥታ ኃይሎች በቁጥጥር ሥር ውለው መታሠራቸው ታውቋል። የተለያዩ የዜና ምንጮች እንደዘገቡት አቶ አንዳርጋቸው በየመን የፀጥታ ኃይሎች ተይዘው ታሥረዋል የተባለው ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ.ም ሲሆን፣ ሰንዓ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ከመያዛቸው ውጪ ከየት ተነስተው ወዴት እንደሚሄዱ አልታወቀም። አንዳንድ የዜና ምንጮች ከኤርትራ ተነስተው ሰነዓ ትራንዚት አድርገው ወደ ኳታር ዋና ከተማ ዶሃ ሊያቀኑ ሲሉ መያዛቸውን ይዘግባሉ። በተቃራኒው፣ ወደ ኤርትራ በማቅናት ላይ ሳሉ ነው የታሠሩት የሚሉም አሉ። ከመያዛቸው ውጪ መድረሻቸውና መነሻቸውን የሚመለከቱት መረጃዎች እስካሁን ግልጽ አይደሉም።

በኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአሸባሪነት ከተፈረጁት አል-ቃይዳ፣ አል-ሻባብ፣ ኦነግ እና ኦብነግ ጋር በአሸባሪነት የተፈረጀው ግንቦት 7፣ ዋና ጸሐፊውን በሚመለከት ያወጣው መግለጫ እንደሚያስረዳው፣ አቶ አንዳርጋቸው በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን ካወቀ ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ መንገዶች ለማስለቀቅ ውስጥ ለውስጥ ጥረት ቢያደርግም አልተሳካለትም። አቶ አንዳርጋቸው ደርግ የዐፄ ኃይለሥላሴን መንግሥት ካስወገደ ከሁለት ዓመታት በኋላ በ1969 ዓ.ም ይከታተሉት የነበረውን የምሕንድስና ትምህርት አቋርጠው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ሊግ መቀላቀላቸውንና ከሊጉ ንቁ አባላት አንዱ መሆናቸውን የትግል ጓዶቻቸው ይናገራሉ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ወታደራዊ ክንፍ (ኢሕአሠ) ወደ ሚንቀሳቀስበት አሲንባ አቅንተውም ተሳትፎ አድርገዋል። ይሁን እንጂ ከኢሕአፓ አመራሮች ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ላይ መግባባት ባለመቻላቸው የበረሃ ትግላቸውን ከተወሰኑ ጊዜያት በላይ መግፋት አልቻሉም። እንግሊዝ በነበሩበት የስደት ዘመናቸው የደርግ መንግሥትን ይታገሉ ለነበሩ የኢሕአዴግ ታጋዮች የተለያዩ ዕርዳታዎችን ሲያደርጉ መቆየታቸውም ይታወቃል።

ኢሕአዴግ የደርግ ሥርዓትን አስወግዶ ሥልጣን ሲይዝ በተደረገላቸው ጥሪ በ1983 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱት አቶ አንዳርጋቸው፣ በተለይ አባል የሆኑበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢሕዴን) የተባለው ድርጅት ስሙን ወደ ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) ሲቀይር ባሕር ዳር ላይ በተካሄደው ጉባኤ የውይይት መነሻ ጽሑፍ ማቅረባቸው የሚታወቅ ነው።

ከሁለት ዓመት በላይ ባልዘለቀው የሥራ ዘመናቸው፣ በሽግግሩ ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ጸሐፊ በመሆን ሠርተዋል። ሆኖም ‹‹ነጻነትን የማያውቅ ነጻ አውጪ›› በሚለው መጽሐፋቸው እንደገለጹት፣ በድርጅቱ አሠራር ተስፋ በመቁረጣቸው በ1985 ዓ.ም መጨረሻ አካባቢ መልቀቂያ አስገብተው የተመደቡበትን ኃላፊነትና የኢሕአዴግ አባልነታቸውን በመተው በስደት ወደኖሩበት እንግሊዝ መመለሳቸው ይታወሳል።

አቶ አንዳርጋቸው በድጋሜ ወደ ሀገር ቤት የተመለሱት በ1997 ዓ.ም መጀመሪያ አካባቢ ሲሆን፣ ወዲያውኑ የቅንጅት አባል በመሆን ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ለመሆንም ጊዜ አልወሰደባቸውም። በ1997 ዓ.ም የነበረውን ሀገራዊ ምርጫ ተከትሎ ተፈጥሮ በነበረው የኢሕአዴግና የቅንጅት አለመግባባት ከሌሎች የቅንጅት መሪዎች ቀደም ብሎ ዝዋይ በሚገኘው እስር ቤት ለተወሰኑ ጊዜያት በእስር ላይ ቆይተዋል። ወደ እንግሊዝ ሀገር ከተመለሱ በኋላ ከፍተኛ የሆነ ድብደባና የዘረኝነት ስድብ ሰለባ እንደነበሩ ተናግረዋል።

የተወካዮች ምክር ቤት በሽብርተኝነት የፈረጀው የግንቦት 7 ድርጅት አመራር አባል የሆኑት አቶ አንዳርጋቸው፣ ሀገር ውስጥ በህቡዕ ተደራጅተው መንግሥትን እና ሕገ- መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመገልበጥ ሲንቀሳቀሱ ተደርሶባቸዋል በሚል ክስ ተመሥርቶባቸው ከነበሩት እነብርጋዴር ጄኔራል ተፈራ ማሞና አቶ አሳምነው ጽጌ (ማዕረጋቸው ተገፎ ነው)፣ እንዲሁም የግንቦት 7 ድርጅት አመራር ከሆኑት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ጋር መከሰሳቸውን መዘገባችን ይታወሳል። ጉዳዩን ሲመረምር የነበረው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እነጄኔራል ተፈራ ማሞ በዕድሜ ልክ እስራት እንዲቀጡ ሲወስን፣ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋና አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በሞት እንዲቀጡ መወሰኑ ይታወሳል።

## የአቶ አንዳርጋቸው ዕጣ ፈንታ

የየመን መንግሥት አቶ አንዳርጋቸውን ለኢትዮጵያ መንግሥት አሳልፎ እንዳይሰጥ በዳያስፖራ ኢትዮጵያውያንና በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች በኩል ከፍተኛ እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን የአሜሪካ ድምጽን ጨምሮ በርከት ያሉ የዜና ምንጮች ዘግበዋል። አቶ አንዳርጋቸው አዲስ አበባ ገብተዋል የሚሉም አሉ። ወደ ማተሚያ ቤት እስከገባንበት ድረስ ያሉበትን ቦታና ሁኔታ በሚመለከት ያገኘናቸው መረጃዎች እስር በርሳቸው የሚጋጩ ናቸው። አቶ አንዳርጋቸው ግንቦት ሰባት የተሰኘውን ድርጅት በመመሥረትና በመምራት ከፍተኛ ሚና በመጫወታቸው ምክንያት የኢትዮጵያ መንግሥት መያዛቸውን በእጅጉ እንደሚፈልገው ግን መጠራጠር አይቻልም።

በተለያዩ ተቋማትና የመገናኛ ብዙኃን የሚቀርቡትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ፣ የአቶ አንዳርጋቸውን ቀጣይ እጣ ፈንታ በተመለከተ ሁለት የተለያየ ይዘት ያላቸው ትንታኔዎች/ዕይታዎችን ማስቀመጥ ይቻላል። በአንድ በኩል፣ የኢትዮጵያ መንግሥት አቶ አንዳርጋቸውንና የሚመሩትን ድርጅት በሽብርተኛነት ቢፈርጃቸውም ግለሰቡ የእንግሊዝ ዜጋ መሆናቸው የሚታወቅ ነው። ኑሯቸው እንግሊዝ ሀገር ሲሆን አሜሪካን ጨምሮ በተለያዩ ሀገራት እየተዘዋወሩ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ቆይተዋል። የውጭው ዓለም በተለይም ምዕራባውያኑ ሌላው ቢቀር የመኖሪያ ፈቃድ በመስጠት ይተባበሯቸዋል ማለት ነው። ከቦታ ቦታ በነጻነት ይንቀሳቀሳሉ። አዳራሽ ተከራይተው ስብሰባ ይመራሉ። ገንዘብ ይሰበስባሉ። ከዚያም አልፈው ከመንግሥት ኃላፊዎች ጋር ይወያያሉ ወዘተ.። ስለዚህ እንግሊዝ አቶ አንዳርጋቸው ዜጋዋ ስለሆኑና እንደ አንድ ዴሞክራት ሀገር ወደ ኢትዮጵያ ተላልፈው ቢሰጡ የሚገጥማቸውን ሁኔታ በማጤን እንዲለቀቁ ወይም ተላልፈው እንዳይሰጡ ግፊት ልታደርግ ትችላለች። እንግሊዝ የየመን ዋነኛ የሰብዓዊና የልማት ዕርዳታ ሰጪ ሀገር በመሆኗ እንዲሁም የመን ከአል-ቃኢዳ ጋር ተያይዞ በተደቀነባት የደህንነት አደጋ ምክንያት የምዕራባውያን ጥገኛ በመሆኗ ከምር ከተንቀሳቀሰች በየመን ላይ ተጽእኖ ማድረግ የምትችል ሀገር ናት።

ኢትዮጵያና የመን ባደረጉት እስረኛን አሳልፎ የመሰጣጠት ስምምነት ማድረጋቸው የሚታወቅ ቢሆንም፣ ስምምነቱ በፍላጎትና ብሔራዊ ጥቅምን መሠረት አድርጎ የሚደረግ እንጂ አስገዳጅነት ያለው ስምምነት አይደለም። ስለሆነም የመን አቶ አንዳርጋቸውን አስልፋ ለመስጠት የሚያስችላት የተለየ ምክንያት ከሌለ በስተቀር የምትገደድበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለም።

እንደነ አምንስቲ ኢንተርናሽናልና ሂውማን ራይትስ ዎች ያሉ ተደማጭነት ያላቸው ድርጅቶችም አቶ አንዳርጋቸው ወደ ኢትዮጵያ ተላልፈው ቢሰጡ የሚገጥማቸውን በመጥቀስ መንቀሳቀሳቸው አይቀርም። ከሁሉም በላይ በውጭ የሚኖሩ ብዙ ኢትዮጵያውያን አቶ አንዳርጋቸው ተያዙ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማድረግ ጀምረዋል።

ጥያቄው ‹‹የውጭ ተጽእኖ ጫና ይፈጥራል ወይ?›› የሚለው ነው። አዎ ይፈጥራል። ከዚህ በፊትም በሀገራችንም በሌሎች ሀገሮችም በሚገባ ታይቷል። አሜሪካን የሚያክል ኃያል ሀገር ‹‹የሀገሬን ምስጥር አባክኗል፤ ወንጀለኛ ነው፤›› ያለችው ኤድዋርድ ስኖውደን ተላልፎ እንዲሰጣት ያልፈነቀለችው ድንጋይ ባይኖርም አልተሳካላትም። የዊኪሊክሱ መሪ ጁሊያን አሳንጅ ሁኔታም ተመሳሳይ ነው። በሀገራችንም ቢሆን በውጭ በሚኖሩት ኢትዮጵያውያን ያልተቋረጠ ተቃውሞና በምዕራባውያን ሀገራት ተጽእኖ ምክንያት የቅንጅት መሪዎችን ጨምሮ ብዙ ሰዎች ከእስር እንዲፈቱ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል። አቶ መለስ ዜናዊ በሕዝብ ተወካዮች ፊት ወንጀለኝነታቸውን አውጀው ‹‹በምንም ዓይነት ሁኔታ አይፈቱም!›› ሲሉ ያወጁባቸው ሁለቱ ስዊድናውያን ጋዜጠኞች ተፈትተዋል። ሌሎችንም ብዙ አብነቶች ማንሳት ይቻላል።

ሁለት ነገሮችን ግን ልብ ማለት ያስፈልጋል። አንደኛ፣ የሚፈጠረው ተጽእኖ ደረጃ ምን ያህል ነው? የሚለው። እንግሊዝና ኢትዮጵያ የጠበቀ ወዳጅነት ያላቸው ሀገሮች መሆናቸው የታወቀ ነው። ‹‹እንግሊዝ በአቶ አንዳርጋቸው ምክንያት ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ግንኙነት ማሻከር ትፈልጋለች ወይ? የኢትዮጵያ መንግሥትስ ቢሆን አንደኛ የሰብዓዊና የልማት እርዳታ ሰጪው ከሆነችው እንግሊዝ መቀያየም ይፈልጋል ወይ? ወዘተ.›› የሚሉት ነጥቦች መሠረታዊ ናቸው። ከእንግሊዝ መንግሥትና በአጠቃላይ ከምዕራባውያን ሀገራት በተጨማሪ የዓለም አቀፍ ድርጅቶችና የዳያስፖራው ተጽእኖ መጠን/ደረጃ ለአቶ አንዳርጋቸው ተላልፎ መሰጠት ወይም አለመሰጠት አስተዋፅኦ ያደርጋል። የተጽእኖው መጠን ዝቅተኛ ከሆነ ማንኛውም ሰው የፈለገውን ያህል የውጭ ሀገር ዜግነት ቢኖር ተላልፎ ከመሰጠት አያመልጥም። አቶ ኦኬሎ አኮይ የተባሉትን የቀድሞው የጋምቤላ ክልል አስተዳዳሪ የኖርዌ ዜግነታቸው አላዳናቸውም። ከዚህ ቀደምም አንድ ነጋዴ ከባንኮች ብድር ወስደው ካገር ከወጡ በኋላ የመን በመያዛቸው፣ የየመን መንግሥት አሳልፎ መስጠቱ የሚታወስ ነው።

ሁለተኛ ነጥብ የመንግሥትን ፍላጎት የሚመለከት ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት አቶ አንዳርጋቸውን በጥብቅ እንደሚፈልጋቸው የሚያጠራጥር አይደለም። በአንድ በኩል አቶ አንዳርጋቸው ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ከኢሕአዴግ መሪዎች ጋር አብረው የሠሩ ሰው በመሆናቸው ከተለቀቁ በኋላ የድርጅቱንና የመሪዎችን ገመና እያጋለጡ ከፍተኛ የራስ ምታት ሲፈጥሩ መቆየታቸውን መካድ አይቻልም። አቶ አንዳርጋቸው ሲፈጥሩ ከቆዩት ተጽእኖ በላይ ግን የመንግሥት ሰዎች ግለሰቡን መያዛቸው ‹‹ማንኛውንም ሰው ከእኛ አቅም በላይ አይደለም›› ለማለት ብቻ ሳይሆን፣ ይህን ድል በማውራት መሠረታዊ ነገሮችን ለማስቀየስ ይጠቅማቸዋል። ስለዚህ አቶ አንዳርጋቸው ተላልፈው እንዲሰጧቸው ያለ የሌለ አቅማቸውን እንደሚጠቀሙ መገመት አይከብድም።

***ዕንቁ መጽሔት አንዳርጋቸው ጽጌ መታገታቸውን በተመለከተ ሰኔ 18 ቀን 2006 ዓ.ም የሰራችውን ዘገባ ለማስታወስ ያክል አቅርበነዋል። አንዳርጋቸው ጽጌ ግንቦት 21 ቀን 2010 ዓ.ም ከእስር ተፈተዋል።***



# “አንዳርጋቸው የሚያደርገውን በትክክል ያውቅ”

## አቶ ፅጌ ሃብተማሪያም (የአንዳርጋቸው አባት)



**ግዮን፡- እንኳን ደስ አለዎት! ለዓመታት እስር ቤት እየተመላለሱ ልጅዎን አንዳርጋቸውን ይጠይቁ ነበርና ምን ተሰማዎት?**

**አቶ ፅጌ**፡- እኔ ከልጅነቴ ጀምሬ ብዙ ነገር ስላየሁ የእሱ መታሰር ቢያሳዝነኝም ያን ያህል የሚያስጨንቀኝ ግን አልነበረም፤

**ግዮን፡- እንዲያው ለመንደርደሪያ ያህል ትንሽ ስለራስዎ ቢነግሩኝ...**

**አቶ ፅጌ**፡- ደስ ይለኛል... የእናቴና የአባቴ ወገን ከአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ጃንሆይ ዘመናዊ የወታደር ሥርዓት እስከሚያመጡ ድረስ የአገራችንን ዳር ድንበር ሲጠብቁ ነበር፤ መጨረሻ ላይም ቢሆን በውጊያው ሰዓት ዘመናዊ የጦር መሣሪያ የያዘውን የጠላት ጣልያንን ጦር መቋቋም ቢያቅታቸውም ዝም ብለን ቁጭ ብለንማ አንበላም ብለው ትንንሽ ሕፃናት ልጆችን ይዘው ነው ጫካ የገቡት።

በጊዜው አባቴ ሞተ፣ አራት ታናናሽ ወንድሞቼ ታርደው ተገደሉ፤ በኋላ እኔም ከቀሩት ዘመዶቼ ተለየሁ፤ ከማላውቃቸው ሰዎች ጋር ሆኜ በተለያዩ አገሮች እየተዋጋን ስንሄድ ቡታጅራ የሚባለው ቦታ ላይ ጠላት ተዘጋጅቶ ጠበቀን።

ራስ ደስታ፣ ደጃዝማች ገ/ማርያም፣ ፊታውራሪ ሽመልስና ሌሎችም የታወቁ መሪዎች በዚህ ውጊያ ላይ ነው የተሠውት። ከእነርሱ ጋር የነበሩ ብዙ አርበኞችም በውጊያው ላይ ተሠውተዋል። የእኔ ዘመዶችም በብዛት እዚህ ውጊያ ላይ ሞተዋል። ጥቂት የተረፉ ሰዎች ወደ ኬንያ ለመሄድ ፈልገው ሰው ገንዘብ ሲረዳቸው ያኔ እኔ ልጅ ስለነበርኩና እድሜዬ ገና ሠባት በመሆኑ በአደራ ሰጥተውኝ ከሰዎች ጋር እዚያው አምስት ዓመት ተቀመጥኩ።

ጃንሆይ ሲመጡ ታሪኬን የሚያውቁ ሰዎች ለጃንሆይ ነግረዋቸው ስለነበር በዚያ መሰረት ጃንሆይ ቤተ መንግሥት ተቀምጬ ተፈሪ መኮንን ት/ቤት እንድማር ቢፈቀዱልኝም ቤተ መንግሥት ቦታ ባለመኖሩ የአርበኞች ልጆች የሚማሩበት ት/ቤት ደጃዝማች ገ/ማርያም ተጽፎልኝ ገባሁ። በዚህ ት/ቤት ሁለት ዓመት እንደተማርኩ ወደተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ተዛወርኩ፤ በመጨረሻም መምህራን ማሠልጠኛ ገብቼ ሁለት ዓመት ከተማርኩ በኋላ በአስተማሪነት ሠራሁ።

በፍጥነት ወደ ዳይሬክተርነት አድጌ በትምህርት አስተዳደር ዘርፍ ስሠራ ቆይቻለሁ። እንዲህ እንዲህ እያለ ብዙ ቦታዎች የመሥራት እድሉ ገጥሞኛል።

**ግዮን፡- መቼ ነበር ትዳር የመሠረቱት?**

**አቶ ፅጌ**፡- ወደ ትዳር ስገባ ገና የ18 ዓመት ወጣት ነበርኩ። አጠቃላይ ዘጠኝ ልጆች ነው የወለድኩት በሕይወት የሌሉ አሉ።

**ግዮን፡- አንዳርጋቸው ፅጌ በታሰረ ጊዜ እርስዎ ተይዘው ታስረው ነበር፤ ለምን ለነበር የታያዙት?**

**አቶ ፅጌ**፡- ግብረ አበር ነህ በሚል ነው፤ እኔ ደግሞ አባቱ እንጂ ግብረ አበሩ አይደለሁም አልኩኝ፤ ሰሚ ባይኖርም።

**ግዮን፡- ምን ያህል ጊዜ ነው የታሰሩት?**

**አቶ ፅጌ**፡- ሁለት ዓመት ተቁል ታስሬ ነው የተፈታሁት።

**ግዮን፡- በሽምግልና እድሜዎ ከሁለት ዓመት በላይ ያስለፉት የእስር ሕይወት ምን ይመስላል?**

**አቶ ፅጌ**፡- እስር ቤት እስር ቤት ነው፤ ብዙ ነፃነት ባይኖረውም የሚበላ፣ የሚጠጣ እንዲሁም መኝታ አለው፤ ያው ቁርስ፣ ምሳ፣ እራት በጊዜው ይቀርብልን ነበር።

**ግዮን፡- መጨረሻ ላይ ምን ብለው ፈቱዎት?**

**አቶ ፅጌ**፡- በጊዜው የእስረኞችን ሁኔታ የሚከታተል፣ የታሰሩ እስረኞችን በተለያዩ መንገዶች ይቅርታ የሚያስደርግና የሚያስፈታ አንድ ኮሚቴ ነበር። በእነርሱ በኩል የእኔ ጉዳይ ታይቶ ምንም ጥፋት አልተገኘበትም፣ ወንጀለኛ አይደለም በሚል እድሜዬም ከግምት ውስጥ ገብቶ ጠይቀውልኝ ነው የተፈታሁት።

**ግዮን፡- ያኔ ሲታሰሩ እድሜዎ ምን ያህል ነበር?**

**አቶ ፅጌ**፡- እነሱ ሲያስሩኝ 78 ዓመቴ ነበር፤ አሁን 87 ዓመት ሞልቶኛል። በእርጅና እድሜዬ አስገብተው ሰማኒያኛ እድሜዬን ከደፈንኩ በኋላ ነው ያስወጡኝ።

**ግዮን፡- አንዳርጋቸው ተይዞ ወደ አገር ቤት ገብቷል የሚለውን ዜና መጀመሪያ ሲሰሙና በኋላም እስር ላይ ሲጠይቁትስ ምን ተሰማዎ?**

**አቶ ፅጌ**፡- አንዳርጋቸው በሚያደርገው ነገር ሁሉ ምክንያታዊ መንገዱ የማይዋጥላቸው ሰዎች ሲይዙት ቢያስገርመኝም የተያዘው ባመነበትና በሚሠራው ሥራ በመሆኑ በፍርድ የሚሰጠውን ውሳኔ ከመጠበቅ ውጪ ከፍተኛ ድንጋጤ አልተሰማኝም።

አንዳርጋቸው ልዩ የሆነ ሰው ነው፤ እንዲህ አድርግ አታድርግ ብዬ የምመክረው አይደለም፤ በጣም ጠንካራና በእኔ ቤተሰቦች ላይ የደረሰውንም መከራ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ የሚጠብቅበትን መሥዋእትነት ከፍሎ ፍትሕን እንደሚያገኝ የታገለለትንም ሕዝብ እንደሚያከብር እርግጠኛ ነበርኩ።

እሱ ብቻ ሳይሆን ሁሉም ልጆቼ የቀደመ ታሪካቸውን የሚያውቁ ቤተሰቡ ያሳለፈውን እንግልት የሚረዱ ስለሆነ ከእኔ ብዙም ምክር የሚያስፈልጋቸው አይደሉም።

**ግዮን፡- አንዳርጋቸው ከሌሎች ልጆችዎ ለእርስዎ በምን መልኩ ይለያል?**

**አቶ ፅጌ**፡- እርሱ ያለው አዕምሮ ትልቅ ነው፤ በጣም አስተዋይ ሰው ነው። ልጅም ሆኖ ይህ እውቀትና ንቁነቱ አብሮት ነበር። ገና በለጋ እድሜው በደርግ ሥርዓት ብዙ መከራ አይቷል፤ ያኔ አለመሞቱ በራሱ ይገርመኛል። አንድ ወንድሙ በጊዜው ተገድሏል።

አንዳርጋቸው የሚታገለው ለሕዝቡ ነው። ባወቀውና በተረዳው መጠን አገሩ ሰላምና ሕዝቦች በነፃነት የሚንቀሳቀሱባት እንድትሆን ይፈልጋል። ጥቃትን፣ በደልን አይወድም። ሁሌም የሚታገለው ለሀገሩና ለወገኑ መብት ነው እንጂ ሥልጣን ወይም ሌላ ነገር አገኙቶት አይደለም።

**ግዮን፡- እስር ቤት በነበረ ጊዜ ልጄን አንድ ነገር ያደርጉብኛል ብለው ሠግተው ነበር?**

**አቶ ፅጌ**፡- የሚደረገውን ነገር ሁሉ ስለማውቀው ያን ያህል አልጨነቅም ነበር፤ ቀደም ሲል እንደነገርኩህ የታሰረው በወገንና በአገር ጉዳይ ስለሆነ ምንም ነገር ቢገጥመው ለአገሩ የከፈለው መሥዋእትነት ነው ብዬ ነው የወሰንኩት። እግዚአብሔር ራሱ ጊዜውን ጠብቆ ፍርድ ይሰጣልና።

**ግዮን፡- ሌላ ጊዜ አንዳርጋቸውን ሊጠይቁ ሲሄዱ ቁጭ ብለው ነበር የሚጠብቁት፤ ቅዳሜ ዕለት ሊጠይቁት በሄዱ ሰዓት ግን እሱን እንዳዩ ነው ብድግ ያሉት፤ የመፈታቱ ዜና የፈጠረብዎት ስሜት ይሆን?**

**አቶ ፅጌ**፡- ይህችን ደግሞ ከየት አገኘሃት። ያው የፈነጠቀው ፀሃይ ነው እንደዚያ ያደረገኝ። መፈታቱን መስማቴ በውስጤ የሚያሳድረው ነገር እንዳለ መዘንጋት የለብህም። እንደዚያ በፍጥነት ያስነሣኝ በቀጣይ የሚኖረው ተስፋ ነው። ያ ለእሱ ልዩ የሆነ ነገር ስለነበር በጊዜው አንዳርጋቸው በጣም ተገርሟል። ደስታው ውስጤ ስለገባና እሱን ተፈትቶ ማየት እመኝ ስለነበር ነው ብድግ ያልሁትና እርጅናዬን የረሣሁት።

**ግዮን፡- በመኖሪያ ቤትዎና በአካባቢው ሕዝቡ ያደረገውን አቀባበል እንዴት አዩት?**

**አቶ ፅጌ**፡- አንድ ሰው ብቻውን አይደለም የሚኖረው፤ ሕይወቱ ከአገሩና ከሕዝቡ ጋር ነው። አንዳርጋቸውም የታገለው ለዚህ ሕዝብ ነው፤ እድሜውን በሙሉ የደከመላት ለአገሩ ነው። እንስሳትም በጋራ ይሄዳሉ፣ በጋራ ይፋለማሉ፤ ሰው ከእንስሳ በላይ ስለሆነ የጋራ ሕብረትና ስሜት ያስፈልገዋል። አንዳርጋቸው በዚህ መንገድ የትግል ዘመኑን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አድርጓል።

ራሱን ለመሥዋእትነት ያቀረበለት ይህ ሕዝብ በይፋ እንዳያየኸሁት ውለታውን በይፋ ከፍሎታል። በጣም ደስ በሚልና እንኳንም ታገልኩ በሚያስብል ሁኔታ ነው ህዝቡ የተቀበለው። አንዳርጋቸው የሚያደርገውን በትክክል ያውቅ ስለነበር የታገለለት ሕዝብ በክብር ተቀብሎታል።

**ግዮን፡- በመጨረሻ በዚህ አጋጣሚ የሚያስተላልፉት መልእክት ምንድነው?**

**አቶ ፅጌ**፡- ለኢትዮጵያ የሚያስፈልገው አንድነት፣ ሰላምና ፍቅር ነው። ልዩነታችንን በሰላማዊ መንገድ ፈትተን ሕዝቡ በምግብ፣ በጤና፣ በኢኮኖሚና በነፃነት ተጠቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ መፈጠር አለበት። ይህ ነገር ለኢትዮጵያችን ያስፈልጋል።

**ግዮን፡- አመሰግናለሁ።**







# “እስኪፈታ ድረስ እንዳየው፤ እንድጠይቀው አልተፈቀልኝም”

**ወ/ሮ አይኔ ፅጌ /እህት/**

**ግዮን፡- ወንድሽ አቶ አንዳርጋቸው ከእስር በመለቀቁ እንኳን ደስ ያለሽ?**

አይኔ፡- እንኳን አብሮ ደስ አለን::

**ግዮን፡- እስኪ ራስሽን አስተዋውቂን?**

አይኔ፡- አይኔ ፅጌ እባላለሁኝ ፤የአንዳርጋቸው ታናሽ እህት ነኝ::

**ግዮን፡- አንዳርጋቸው የመን ላይ ተይዞ መታሰሩን ስትሰሚ ውስጥሽ ያደረው ስሜት ምን ነበር?**

አይኔ፡- በጊዜው በጣም ከባድ ስሜት ተሰምቶኛል:: ያልጠበቅኩት ነገር ስለነበር ደንግጫለሁ:: ምን ማድረግ እንዳለብኝ በጭራሽ አላውቅም ነበር፤ ወቅቱ በጣም መጥፎ ሰአት እንደነበር ነው ትዝ የሚለኝ::

**ግዮን፡- ለመጠየቅ እሱን ለማግኘት ሞክረሽ ነበር?**

አይኔ፡- ያው እንደተያዝ ምን ያደርጉት ይሆን? በሚል ሃሳብ መባዘንና በአካል ለማየት ነበር የሁላችን ፍላጎት:: ግን ያው እንደምታውቁት ለመጠየቅ ስላልተፈቀደልኝ እስኪፈታ ድረስ አላየሁትም::

**ግዮን፡- እስር ላይ ረጅም ጊዜ እህቶቹ እንድትጠይቁት አልተፈቀደላችሁም ነበር ፤ምክንያቱ ምን ይመስልሻል?**

አይኔ፡- በርግጠኝነት ምክንያቱን አላውቅም:: ግን በጊዜው እንዲጠይቁት የተፈቀደላቸው አባቴና ባለቤቱ ወ/ሮ ታደለች ስለሆኑ ከእነሱ በስተቀር ሌላ ሰው መግባትና ማየት አይችልም ብለው ከለከሉ:: ከዛ በኋላ በኤምባሲው በኩል አባትየው የዘጠና አመት ሽማግሌ ነው፤ለምንድነው እህቱ እንድትጠይቀው ያልፈቀዳችሁት? ተብለው ተጠይቀው እንደማይቻል ነው ለእነሱም የተነገራቸው:: አንድ ጊዜ ግን በሰው ሰው አጠያያቄ የአንዳርጋቸው ቤተሰብ ሆኖ መጥቶ ለመጠየቅ የከለከልነው ሰው የለም በማለታቸው እነሱ በሚገቡበት ቀን ቃሊቲ አባቴን አስቀርቼ ከወ/ሮ ታደለች ጋር ሄድኩኝ::

እዛ ስደርስ ግን ጠባቂው አንቺ እንድትገቢና እንድትጠይቂው የሚፈቅድ መመሪያ አልተሰጠኝም:: አትገቢም አሉኝ፤ መጥቶ የከለከልነው ሰው የለም ስላላችሁ ነው የመጣሁት፤ ሌላ ሴት ነኝ ብለህ አስበህ ከሆነ እህቱ ነኝ ብለውም ለከለኝ:: በዚህ መሰረት እኔ ቀረሁ ወ/ሮ ታደለች ስንቁን ይዛ ገባች ማለት ነው:: እንግዲህ ምክንያቱ ግልፅ ባልሆነ ሁኔታ እስኪፈታ ድረስ ከነገርኩህ ሰዎች ውጪ ማንም የቤተሰቡ አባላት እንድንጠይቀው አልተፈቀደም፡

**ግዮን፡- ሌላ ያመለከትሽበት ጉዳዩን ያስረዳሽበት ቦታ የለም?**

አይኔ፡- ምንም የምታመለክትበት ቦታ የለም:: የት ትሄዳለህ? ምንም ቦታ ብትሄድ ሊፈቅዱልህ እንደማይችሉ ሁኔታዎች አመላካች ናቸው::

**ግዮን፡- በራስሽ እንደው የጠረጠርሽው ነገር አለ?**

አይኔ፡- ነገሩ ሁሉ የተቀነባበረው ደህንነቶች አካባቢ ነው የሚመስለኝ:: የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር የነበረው አቶ ካሳ ተክለብርሃን አምባየን አንድ ወቀት ጠይቄው ነበር:: ግን በሰአቱ የማረሚያ ቤቱ ሃላፊ ቤተሰቡ ገብቶ ይጠይቀዋል፤ ይጎበኘዋል የሚል ምላሽ ነው የሰጠው:: ግን እኔ እንደማላየው ለአቶ ካሳ አስረግጬ ስነግረው አቶ ካሳ በድጋሚ የማረሚያ ቤቱን ሰው ሲያነጋግረው ፈፅሞ የከለከልነው ሰው የለም በማለቱ ነበር አንድ ጊዜ ተነስቼ ለመጠየቅ የሄድኩት:: ግን ያው አላስገቡኝም፤ መልሰውኛል::

የመጀመሪያውን አንድ አመት ከማንም የቤተሰብ አባላት ጋር እንዲገናኝ አልተፈቀደለትም ነበር፤ ሶስቱን አመት ግን አባቴ ያየው ነበር፤ ከሰው ጋር እንዲገናኝ ከተፈቀደበት ጊዜ አንስቶ እንኳን እንዳየው እስከ መጨረሻው ሰአት አልተፈቀደልኝም:: እኔ ብቻ ሳልሆን ዘመድ ጓደኛ ማንም ሰው ሊያየው አልቻለም::

**ግዮን፡- ለአንድ አመት መጀመሪያ ላይ የት እንዳለ ሳታውቁ በቆያችሁበት ጊዜ ስለ ጉዳዩ በቂ መረጃ እንዲኖራችሁ ያቀረባችሁት ማመልከቻ ነበር?**

አይኔ፡- ምንም ማድረግ አልቻልንም:: አህቴ ከአሜሪካ ድረስ መጥታ ቀይ መስቀል፣ ለአምባሲዎች የት እንዳለ በመጠየቋ እኮ ነው በሶስተኛው ቀን ከአገር እንድትወጣ የተደረገው:: ይሄ ባለበት ሁኔታ እኔ ምን ማድረግ እችላለሁኝ:: እኔም የእሷ እጣ ፈንታ ከደረሰኝ የምጦረውን ሽማግሌ አባቴን ትቼ ለእሱ ስንቅ ማዘጋጀቴን ትቼ መባረር ነው እጣ ፈንታዬ::

ከማየው ነገርና መጀመሪያ ላይ እህቴ ካደረገችው ሙከራ የተነሳ የትም ብሄድ ለውጥ ይመጣል ብዬ ስላላመንኩ አርፌ ፍርዱን ለእግዚአብሄር ሰጥቼ ነው የተቀመጥኩት::

**ግዮን፡- እንደውም በግልፅ ሲባል የነበረው የአቶ ተፈራ ዋልዋ ባለቤት እንደመሆንሽ አንዳርጋቸውን ለመጠየቅ ከሌላው የተሻለ እድል ታገኚያለሽ የሚል ነበር?**

አይኔ፡- ተፈራ ባለቤቴ በመሆኑ ተጨማሪ የማገኘው ነገር አልነበረም:: ደግሞም አልተቻለም::

**ግዮን፡- በባለቤትሽ በኩል ይህን ነገር በተመለከተ ያደረግሽው ጥረት የለም?**

አይኔ፡- ምንም ነገር የለም:: እኛ በትዳራችን ላይ ሁላችንም የሆነ ድንበር አለን፤ ከዛ ድንበር በላይ አናልፍም፡፤ በሚያገናኘን ነገር እንገናኛለን፤ በማያገናኘን ነገር እንለያያለን:: እነዚህ ነገሮች እሱም ቢያውቃቸው መፍትሔ የማያመጣ ነገር ስለሆነ ጉዳዩን ለእሱ አሳልፎ መስጠት አግባብ አይደለም::

**ግዮን፡- አራት አመት የእስር ቤት ቆይታው በቤተሰቡ ውስጥ ምን አይነት ገፅታ ነበረው?**

አይኔ፡- ከአራት አመት እስሩ ላይ የመጀመሪያው አንድ አመት ለእኛ የጨለማ ዘመን ነበር:: ያ በጣም ከባድ ነው:: አንድ ሁለት ጊዜ የእንግሊዝ አምባሳደር በማየቱ ትንሽ ቢያረጋጋንም ሁኔታው ለእኛ በጣም ከባድ ነው:: የት እንዳለ ራሱ አናውቅም ነበር:: በጣም የማዝነው አንድ ቀን አባቴ “ይሄ ልጅ እንደው ምግብ ያገኝ ይሆን” ብሎ የጠየቀኝ ነገር ውስጤን ነክቶታል:: በሰአቱ ምድር ከሰማይ ነው የጨለመብኝ::

ብዙ ነገሮችን በየጊዜው በአስረኞች ዙሪያ ስለምንሰማ እሱ ላይማ ነገሮች ምን ሊሆኑ ይችላሉ የሚለውን ስታስቡ የመጀመሪያው አንድ አመት ለእኛ የጨለማ ዘመን ነበር:: በኋላ ቅዳሜ ቅዳሜ ቃሊቲ እየገቡ እንዲጠይቁት ለአባቴ ሲፈቀድ በህይወት መኖሩና እነሱን ማግኘት መቻሉ ነው ትንሽ ያረጋጋን እንጂ ሌላው ነገር በሙሉ የከፋ ጊዜ ነበር ማለት ይቻላል::

**ግዮን፡- በርግጥ ይሄ ራሱ አንድ ትልቅ ተስፋ አለው::**

አይኔ፡- በጣም:: ከሶስተኛው አመት በኋላ ጠበቃ ሲባል ጠበቃውን የመረጡለት እነሱ ራሳቸው ናቸው:: የትኛው አለም ላይ ነው አንድ ተከሳሽ የከሰሰው መንግስት እነዚህ ናቸው የአንተ ጠበቃ መሆን ያለባቸው ብሎ መርጦ የሚያቀርብልህ? ጠበቃ ለምን እንዳስፈለገውም እግዚአብሄር ይወቀው::

እነሱ ካቀረቡለት አምስት ጠበቆች መሃል እኚህኛው ይሻላሉ ብሎ ዶክተር ብርሃኔ የሚባሉ ጠበቃን አንዳርጋቸው መርጦ ስለነበር እሳቸውን ለማነጋገር ስንፈልግ መጀመሪያ እምቢ በለው ነበር:: በኋላ ግን በጉዳዩ ላይ የእንግሊዝ አምባሳደር ጣልቃ በመግባታቸው እሺ ብለው ተገናኘን::

የአጋጣሚ ነገር ሆኖ መንግስት ካቀረበላቸው ጠበቆች መሃል የተመረጡ ቢሆንም እሳቸው ግን በጣም አሪፍና የሚመሰገኑ ሰው ናቸው:: ጥሩ ሰው ናቸው:: የተሰጣቸው ዶክመንት አልነበረም፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ገብተው ካዩት በኋላ ያደረጉት “እስኪ መጀመሪያ ይተንፍስ፤ ይሄን ሁሉ ዘመን በእስርና በስቃይ ነው ያሳለፈው፤ ትንሽ ይረጋጋ” ነበር ያሉት:: በገቡበት ሶስት አራት ጊዜ ረጅም ሰአት እንደልቡ አብረውት የሚያወሩት እሳቸው ስለነበሩ በነፃነት ሰፋ ባለ መልኩ እንደልቡ የሚያወራው ሰው በማግኘቱ በእሳቸው በጣም ደስ ብሎኛል::

**ግዮን፡- ጠበቃ ያስፈለገበትስ ምክንት ምን ነበር?**

አይኔ፡- ግልፅ አይደለም:: ምናልባት እንግሊዞች ጠበቃ ይዞ ጉዳዩን ይከታተል ባሉት ምክንያት እንጂ እነሱማ በ2001 ዓ.ም ነው የሞት ፍርድ የፈረዱበት:: ከሞት ፍርድ በኋላ ደግሞ በሁለተኛ ዙር እድሜ ልክ እያሉ እሱም እኛ በሌለበት ነው ሲፈርዱበት የኖረው::

**ግዮን፡-እንደሚፈታ ስትሰሙ ምን አይነት ስሜት ተሰማሽ?**

አይኔ፡- የዛን ሰአት ስሜት ለመግለፅ በጣም ይከብደኛል:: ቅዳሜ እንደተለመደው ስንቅ እያዘጋጀሁ ስለነበር ልሂድ ብዬ ልቅር የሚለው ድብልቅልቅ ያለ ስሜት ነው የተሰማኝ፤ በመጨረሻ ተዘጋጀሁ:: እነ አባቴ ሄደው ሲያገኙት መስማቱንም እራሱ ነገራቸው:: ከዛ በኋላ ከቅዳሜ ጀምሮ እስከ ትላንት ማክሰኞ ድረስ እየተጠበቀ ነበር::

**ግዮን፡- ከቅዳሜ እስከ ማክሰኞ ድረስ መጠበቁስ እንደገና የፈጠረብሽ ስሜት ምንድን ነበር?**

አይኔ፡- እሱ ልጅ የመውለድ ያህል ምጥ ነበር:: ከአሁን አሁን መጣ ነው እነኛ አብረውን የነበሩ ሰዎች ናቸው ከምንም በላይ ያሳዘኑኝ:: በዝናብ በፀሃይ ቁርስ ምሳ እራት ሳይሉ ከእኛ ጋር እዚሁ ተጣብቀው ነው ያሳለፉት::

**ግዮን፡- አንዳርጋቸው ሲመጣስ የነበረው ሁኔታ አቀባበሉ እንዴት ነበር፤ አንዳርጋቸውን ስታየው ምን ተሰማሽ?**

አይኔ፡- ሳየው በጣም አንጀት ይበላል:: ምክንያቱም በጣም ነው የተጎሳቆለው፤ አንዳርጋቸውን ያገኘሁት በ13 አመቴ ነው ፤በጣም ተጎሳቁሏልሁ:: በፍቶግራፍ ሳየው ደህና ነበር:: ግን አሁን ሲወጣ በጣም ተጎሳቁሎ ቢሆንም በህይወት መውጣቱ ትልቅ ደስታ ነበር::

**ግዮን፡- ከቅዳሜ ጀምረው አብረዋችሁ ለነበሩ ዜጎችም ሆነ ላለፉት አራት አመታት ስለ አንዳርጋቸው መስዋዕትነት የከፈሉ ህዝቦች በተመለከተ የምትይው ምንድነው?**

አይኔ፡- የቅዳሜዎቹ በእርግጥ አብረውን ስለነበሩ ነው፤ ነገር ግን ባለፈው አራት አመት በአገር ውስጥም ሆነ በወጪ አገር ፀሃይ፣ ዝናብ፣በረዶ ሳይሉ ሳይሰለቹ የእርሱን ስም በማንሳት እንዲፈታ ሲያደርጉት የነበረው ጫናና ትግል በጣም የሚያስመሰግናቸው ነው:: ምንጊዜም ቢሆን በህይወታችን እስካለን ድረስ የምንረሳቸው አይደሉም:: ምስጋናዬ በጣም ከፍ ያለ ነው:: አመሰግናለሁ::





# “አንዳርጋቸው ቡድን መገንባትና መምራት የሚችል ፖለቲከኛ ነው”

ብርሃኑ ተክለያሬድ

**ግዮን፡- በመጀመሪያ ለአንባብያን ራስህን በማስተዋወቅ እንጀምር፤ብርሃኑ ማነው? መቼ ወደ ፓለቲካው ተቀላቀለ?**

**ብርሃኑ**፡- ብርሃኑ ተክለያሬድ እባለለሁ:: በፖለቲካ ተሳተፍዬ በቀድሞው የሰማያዊ ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ በኋላም የውጭ ጉዳይ ሃላፊ ነበርኩ፡ ከ2007 ዓ.ም የካቲት ወር ጀምሮ ወደ ግንቦት ሰባት ድርጅት ለመሄድ ከማይካንትራ አካባቢ ተይዤ እስከ 2010 ዓ.ም የካቲት 7 ድረስ በእስር ላይ ቆይቻለሁኝ:: አሁን ደገሞ ከመፈታት በኋላ በኢትዮጰያ የፖለቲካ ትግል ውስጥ እንቅስቃሴ እያደረግኩኝ ነው::

**ግዮን፡- እናንተ በግንቦት ሰባት ታስራችሁ ስትፈቱ አንዳርጋቸው በመቅረቱ ምን አይነት ስሜት ነበር የተሰማህ፤ ከእስር ከወጣህ በኋላስ?**

**ብርሃኑ**፡- የአቶ አንዳርጋቸው ፅጌ አለመፍታት ሁላችንም የሚያመን ነበር:: ምክንያቱም እኛ በቤተሰብ እንጎበኝ ነበር:: ሚዲያው ያለንበትን ሁኔታ ያያል፤ ፍርድ ቤት ቀርበናል:: የውሸትም ቢሆን ተመስክሮብናል:: በጫናም ቢሆን ተፈርዶብናል:: የማይገባን ቢሆንም ፍርዳችንን እናውቃለን:: እርሱ ያለበትን ሁኔታ እንኳ ህዝቡ ሊያውቀው የሚችልበት ሁኔታ የለም:: የድርጅቱ መሪ፣ ስርአቱ በጣም ይጠላዋል:: ይሄን ስርአት ሊገዳደር የሚችል ትልቅ ድርጅት መፍጠር የቻለ ትልቅ መሪ ነውና እሱ ያለበት ሁኔታ በጣም ያስጨንቀን ነበር፤ ሳንፈታም ከተፈታንም በኋላ በእያንዳንዷ ሰአት ስለእሱ እንነጋገር ነበር:: ዞሮ ዞሮ ስርአቱ ያለበትን ሁኔታ እያየነው ስለነበር እጁ ተጠምዝዞ ቢሆን ሳይወድ በግድ አቶ እንዳርጋቸውን እንደሚታፈው እርግጠኞች ነበረን:: ነገር ግን የተሰማኝ ስሜት በእውነት ነው የምልህ በወቅቱም ሚዲያዎችን ሳገኝ እንደተናገርኩት ምንም ደስታ አልተሰማኝ በመፈታቴ:: ምክንያቱም አንዳርጋቸውን የመሰሉ ሰዎች አልተፈቱም ነበር ፤ድሮ በነበረው መከፋት ውስጥ ነበርኩኝ::

**ግዮን፡- አንዳርጋቸው ይፈታል ተብሎ እናንተም ዝግጅት አድርጋችሁ እየጠበቃችሁ ሳለ ለቀናት ሊዘገይ ችሏል:: የአንዳርጋቸው ይፈታል ከተባለበት ቀን መዘግየቱ በእናንተ ላይ የፈጠረባችሁ ነገር አለ?**

**ብርሃኑ**፡- ይሄንን ዝግጅት ሲያስተባብር የነበረው ኮሚቴ አብዛኛው በኢትዮጵያየ ፖለቲካ ውሰጥ ተሳተፎ ያለው ሰው ነው:: የስርአቱን ውሸተምነትና ቃልአባይነት ይደረገሉ ተብለው ሳደረጉ የቀሩ በዙ ነገሮች ተመልክተናል:: ስለዙህ አቶ አንዳርጋቸው ይፈታል በተባለበት ወቅት ደስታ ተሰምቶናል:: ይፋዊ የተገለፀው በቅረቡ ነው:: ከዛ በፊት ሰዋች ከውስጥ መረጃ አይነት ወሬዎች ነበሩ በይፋ በጠቅላይ ሚነስትሩ ተገልጿል:: ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ በጣም ከፍተኛ ጉጉት እርሱን ለመቀበል ዝግጅት ስናደርግ ነበር:: ነገር ግን ጥርጣሬዎች ነበረ ምናልባት ኢህአዴግ ቃሉን ሊያጥፍ ይችላል ሌላው ጥርጣሬ ደግሞ ብዙ ሰው እንደገመተው ወደ እንግሉዝ አገር ተልከው ሊሆን ይችላል የሚል ሃሳብ ነበረን:: ዞሮ ዞሮ እዚህም ሆነ ለንደን መለቀቃቸው ትልቅ ዜና ነው:: ትልቅ ዜና መሆን ብቻ ሳይሆን አራት እመት ሙሉ ከህዝብ ጋር እንዳገናኘ ተደርገው የታሰሩ ሰው ስለነበሩ በአራት እመት ውስጥ ህዝቡ ስለእርሳቸው እያደረገ የነበረውና ድገፍ ኢህአዴግ ደግም እዛ ውስጥ የነበረውን ሚና በደንብ ይመለከቱት ዘንድ አሁን ደግም ለጀግናችን ክብር እንዳለው ለማሳወቅ እግልዝ አገር እንኳን ቢሄድ ቤተሰበቸው ቤት ትልቅ ፕሮግራም አዘጋጅተን እርሱን ህዝቡ ይበልጥ እንዲያውቀው ስርአቱ አሁንም ለመሪያችን ክብር እንዳለን እንደያውቅ እንዲሁም ደግሞ ለአቶ አንዳርጋቸው ይለን ክብር እንዲረዳ ለማድረግ ፕሮግራሞች ጀመርን ማለት ነው:: በመዘግየት ጭንቀተ ውሰጥ ነበርና:: እንደምታውቀው ማህበራዊ ሚደያውም የተረጋጋ አልነበረም የተለይዩ ሰበር ዜናዎች ይወጡ ነበር ሁሉም ሰው በየራሱ ሰበር ዜናዎች ያውጣ ነበርእና ከራሱ ቤተሰብ አካባቢ ጭንቀት ፈጥረው ነበር::

**ግዮን፡- የአንዳርጋቸው አላማና መንገድ ተከትለህ ወደ በርሃ ድረስ ተጉዘህ ነበር በንግግር እንጂ በአካል አይተኸው የማታውቀውን ሰው ፊት ለፊት ስታገኘው ምን ተሰማህ?**

**ብርሃኑ**፡- ደስታ ከተባለ ደስታ ነው የሚሰማኝ:: የማይገለፅ ነው:: አንዳንድ ሰዋች ከሰውነት በላይ ገዝፈው መንፈስ ሆነው ይታዩሃል:: አንዳርጋቸው በሰራቸው ስራዎች፣ በሚናገራቸው ንግግሮች ለእርሱ ፖለቲካ ማለት ስብከት አይደለም:: ፖለቲካ ማለት መሬት ላይ ወርዶ በተግባር ከሁሉ ጋር እየሰሩ ማሳየት ነው:: በድርጅቱ የመሪነት ብቃቱን በሚዲያ ተመልክተነዋል:: ድርጅቱ እያደገ ሲሄድ አይተናል:: የእርሱ ጓደኞች የነበሩት እስር ቤት ያሳለፉ ሰዎች ብዙ ስለ ስብዕናው ነግረውናል:: ስለዚህ ወደ መንፈስ ደረጃ ተጠግቷል:: አንዳርጋቸውን እንጠብቀው የነበረበት ከፍታ በጣም በሚገርም ጉጉት ውስጥ ነው የነበርኩትና ከመኪና ወርዶ ቤት ውስጥ ሳገኘው የማይገለፅ ነገር ቃላት የማይችሉት ነገር ነው የተሰማኝ:: ሰዎች እንደሚናገሩለት በጣም ትሁት ነው፤ እያንዳንዱ ነገር በግልፅ መናገር ይችላል ሲናገር የእያንዳንዱን ሰው ቀልብ መግዛት ይችላል:: ሃሳቡን በሚገልፅበት ወቅት ሁሉም ሰው በሚያዳምጠው ነገር ለእርሱ ስሜት ውስጥ ገብተው እንዲረዳው ማድረግ የሚችል ሰው ነው:: በአጠቃላይ አንዳርጋቸው ከቃል በላይ ነው::

**ግዮን፡- በቀጣይስ ከአንዳርጋቸው ጋር ምን ለመስራት አስባችኋል? የእርሱን ፈለግ ለመከተል?**

**ብርሃኑ**፡-ከኢትዮጵያ የፖለቲካ እንቅስቀሴ ውስጥ ተፅዕኖ ፈጣሪ ከሚባሉት ሰዋች አንዱ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ነው:: ከልጅነቱ ጀምሮ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ መራርና የማይደፈሩ ነገሮችን እየደፈረ ተጉዟል:: ይሄ ሁሉ የህዝብ ተቀባይነት፤ ይሄ ሁሉ የመሪነት ብቀት የመጣው በጊዜዎች ሁሉ ሂደት በመጣውና ባካበተው ልምድ ነው:: አሁን ስለ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ስናስብ እንደ አንዳርጋቸው አይነት የተግባር ሰው የሆነ መሪ ያስፈልገናል:: ፖለቲካ ሱፍና ከረባት አድርጎ በአራት ማዓዘን ቢሮ ተቀምጦ መግለጫ እየሰጡ የሚሰራ አይደለም:: ተግባር ነው የሚጠይቀው:: ከአባላት ጋር እየታሰሩ እየተደበደቡ አየተራቡ እየተጠሙ መሬት ወርዶ የሚሰራ ስራ ነው:: እንደዚህ አይነቱ መሪዎች በብዛት ያስፈልጉናል::አንዳርጋቸው ተፈታ ሲባል የምንደሰተው ታሰረ ሲባል የምንከፋው ግለሰቡን በጭፍን በመውደድ ሳይሆን እነዚህን ሁሉ ኳሊቲዎችን እየተመለከትን ስለሆነ ነው:: በቀጣይ እንግዲህ እሱም ትላንትና ሲያደርገው በነበረው ንግግር እንደሰማኸው የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስር ቤት በነበርኩበትም ወቅት ብዙ መስተካከል ያለበት ነገር እንዳለ ተረድቻለሁ::ድሮ ከነበረኝ ነገር በብዙ እጥፍ ጨምሬ ነው ከእስር የወጣሁት:: በቀጣይ ስለኢትዮጵያ ፖለቲካ ከህዘቡ ጋር የምንነጋገርበት መድረክ ይኖረናል ብሏል::

አንዳርጋቸው ፅጌ ለኔ መሪዬ ነው፤ በቀጣይ ለሚያደርጋቸው የተለያዩ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ከጎኑ ሆኜ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የሚከፈለውን ነገር ሁሉ ለመክፈል በጣም ዝግጁ ነኝ:: በዛ እንቅስቃሴ ውስጥ ነኝ:: እግዲህ እየበሰሉ ከአባልነት ጀምሮ እያንዳንዱ ሃላፊነት ደረጃ ታልፎ ነው ለመሪነት የሚበቃው:: ከእንደዚሀ አይነት መሪዎች አንዱ የሆነው ከአንዳርጋቸው ጎን ሆነን በምናደርገው ትግል አገራችንን ወደምንፈልግበት የተሻለ ነገር እናደርሳታለን ብዬ አምናለሁ::

**ግዮን፡- አንዳርጋቸውን በአጭሩ እንዴት ትገልፀዋለህ?**

**ብርሃኑ**፡- አንዳርጋቸው ከሌሎች ፖለቲከኞች በጣም የሚለየው ነገር የራሱን ስብዕና የማይገነባ ፍፁም ጥልቅ ኅዳዊነት ያለው፣ ቡድን መገንባትና መምራት የሚችል አገሩን ከግለሰብ ጀምሮ እስከ

ላይኛው ድረስ ተመልክቶ እያንዳንዷ ጥቃት የምታመው፣ በእያንዳንዱ ስኬት ውስጥ አገሩን የሚያስገባ በእያንዳንዱ ድክመት ውሰጥ ስለአገሩ የሚያዝን፣ ለአገሩ መልካም ራዕይ ያለው

አሁን አገራችን የተጠናወታት ገንዘብ መውደድ የስልጣን ጥመኝነት የግለሰብ ስብዕናን ማግኘት አሸንፎ የወጣ ለትግል የተፈጠረ ሰው ነው ብዬ አምናለሁ::





# “የአንዳርጋቸው ጥያቄዎችና ፍላጎቶች የኔ ጥያቄዎች፣ ፍላጎቶች ናቸው”

## ሸዋቀና አባትነህ



**ግዮን፡- እስኪ ራስህን በጥቂቱ አስተዋውቀን... ወደ ፖለቲካ ትግሉ ያስገባህ ነገር ምንድነው?**

**ሸዋቀና**፡- እኔ ሸዋቀና አባትነህ እባላለሁ:: አሁን 31 ዓመቴ ነው፤ ነገር ግን በፖለቲካው መሳተፍና ፖለቲካውን መከታተል የጀመርኩት ከ2001 ዓ.ም. ጀምሮ ነው:: በእርግጥ እንደማንኛውም ወጣት በ97 ዓ.ም. ተመልካች እንጂ ተሳታፊ አልነበርኩም:: 97 ዓ.ም. ላይ የተፈጠረው ነገር እዚህች ሀገር ላይ ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ለማድረግ እጅግ በጣም ከባድ እንደሆነ ያየንበትና ፖለቲካውን ዳር ሆነን ከመመልከት ሁላችንም የበለጠ ወደ ውስጡ ገብተን የአቅማችንን መሥራት አለብን ብዬ ስላመንኩ በ2001 ዓ.ም. አንድነት እስከሚፈርስ ድረስ ለመሥራት አባል ሆኛለሁ:: በ2007 ዓ.ም. አንድነት እስከሚፈርስ ድረስ አባል ነበርሁኝ፤ ከዚያ በኋላ እስካሁን ድረስ የየትኛውም ፓርቲ አባል አይደለሁም:: እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ በማኅበራዊ ሚዲያ ፖለቲካውን እከታተላለሁ:: ስለሰብአዊ መብት፣ ስለእኩልነትና ስለዲሞክራሲ ለመጮህ ግዴታ በፖለቲካ ፓርቲ መታቀፍ የለብህም:: ባገኘሁት አጋጣሚ ድምፄን አሠማለሁ:: በዚህ መልኩ ነው ያለሁት::

**ግዮን፡- አንዳርጋቸውን ለመቀበል ዝግጅት ያደረጋችሁት ስንት ሆናችሁ ነው? አቀባበሉስ እንዴት ነበር?**

**ሸዋቀና**፡- አንዳርጋቸውን ለመቀበል ዝግጅት ስናደርግ መጀመሪያ በማኅበራዊ ድረ ገፅ ‘አንዳርጋቸው’ የሚል ግሩፕ ፔጅ ተከፈተ:: በዚህ ገፅ ዓርብ እለት ማታ አወራን:: ቅዳሜ ጠዋት መገናኘት እንዳለብን አዲስ አበባ ያለን ልጆች ተነጋግረን ቅዳሜ ጠዋት ከተገናኘነው የቡድን አባላት ውስጥ አሥር ኮሚቴዎችን መርጠን ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ገባን::

**ግዮን፡- ጠቅላላ ስንት ነበራችሁ?**

**ሸዋቀና**፡- ብዙ ሰው ነው ያለው:: በውጪም አዲስ አበባም ክፍለ ሀገርም የነበሩ ናቸው:: ሥራውን ለመሥራት እንዲመቸን ዋናው ግሩፕ እንዳለ ሆኖ አሥሩ ሰዎች እንደገና የአዲስ አበባ ግሩፕ ፔጅ ከፍተን መነጋገር ጀመርን:: አሥሩ ሰዎች የተለያየ የሥራ ክፍፍል አድርገን ወደ ሥራ ነው የገባነው::

**ግዮን፡- የእስር ፍቺው መዘግየት የፈጠረባችሁ ስሜት ምንድነው? ከዓርብ ዕለት ጀምሮ ስትጠብቁ ማክሠኞ ግንቦት 21/2010 ዓ.ም. ነው የተፈታው::**

**ሸዋቀና**፡- ከፍቺው በፊት የሥራ ክፍፍል አድርገን ወደሥራ ስንገባ አንዳርጋቸው በየትኛው ሰዓት እንደሚፈታ፣ በየትኛው ሰዓት የት እንደሚሆን አናውቅም:: ከአሁኗ ደቂቃ ጀምሮ ሊፈታ ስለሚችል ፈጥነን ወደሥራ መግባት አለብን ብለን ተነጋግረን ወዲያውኑ መግዛት ያለብንን የሚዲያና የተለያዩ ነገሮችን ገዝተን በፌስቡክ ሕዝቡን አቀባበል እንዲያደርግ የሚቀሰቅሰው እየቀሰቀሰ ከዚያም ቅዳሜ ዕለት የአንዳርጋቸው ቤተሰቦች ወዳሉበት ወደአባቱ ወደአቶ ፅጌ ሀብተ ማርያም ቤት መጣን:: እዚሁ ስንሠራ እስከ ማታ አልመጡም:: አደርን:: እሁድንም ደገምን:: አንዳርጋቸው እስከማታ አልመጣም:: ከቅዳሜ ጀምሮ እስከተፈታበት ማክሰኞ ድረስ ጠበቅን:: እኛ በሌለንበት ሌሊት ሊያመጡት ስለሚችሉ እዚያው እያደርን ነበር የምንጠብቀው:: በአጠቃላይ አንዳርጋቸው ከአራት ዓመት በላይ ታስሯል:: እኛ ግን አራት ቀን አብረነው ታስረናል:: በመንግሥት ሚዲያዎችና በማኅበረሰብ ሚዲያዎችም ተፈቷል የሚል ዜና ከመፈታቱ በፊት ስለተለቀቀ በሕብረተሰቡ ዘንድ የተፈጠረውን ተፈቷል፣ አልተፈታም የሚለውን መረጃ እኛ ማስተባበል እስከምንቸገር ድረስ አቅቶን አራት ቀን አብረነው ታስረን ማክሠኞ ዕለት አንድ ላይ ተገናኝተናል::

**ግዮን፡- ማክሠኞ ግንቦት 21 ቀን 2010 ዓ.ም. አንዳርጋቸው ፅጌ ሲፈታና ስታገኙት ምን አይነት ስሜት ፈጠረባችሁ?**

**ሸዋቀና**፡- በጣም ከባድ ነው:: እኔ 31 ዓመቴ ነው፤ አንዳርጋቸው ከ40 ዓመት በላይ በትግል ውስጥ ያሳለፈ ሰው ነው:: አንዳርጋቸውን በአካል አይቼው አላውቅም:: እኔ ከመወለዴ በፊት ትግል ጀምሮ እኔ እንደገና አድጌ ለአቅመ ፖለቲካ ደርሼ ይህ ሥርዓት መለወጥ አለበት በምልበት ወቅት መሪዬ ነው፤ እኔን የሚገዛ ሃሳብ ይዞ የታሰረ መሪ ነውና ይከብዳል:: በቃ በጣም የሚጨንቅ ነው:: ሕዝቡ ለቀናት ዝናብ እየመታው ነው የተቀበለው:: ከምልህ በላይ ነው፤ መግለፅ ይከብደኛል::

**ግዮን፡- አንዳርጋቸው ፅጌን እንዴት ትገልጸዋለህ?**

**ሸዋቀና**፡- እሱን መግለፅ ከባድ ነው:: ትናንትና መጀመሪያ ንግግር ሲያደርግ ለሕዝቡ ባስተላለፈው መልዕክት፣ “አሁን እኔ ተፈትቻለሁ፤ ነገር ግን ብዙ ያልተፈቱ ችግሮች አሉ” ነው ያለው:: ከዚያ በኋላ እኔና አንድ የኮሚቴው አባል ይዘነው ገብተን ያዘጋጀንለትን ባህላዊ ልብስና ካባውን በምናለብሰው ወቅት ጫማውን ጎንበስ ብለን አውልቀን ባህላዊ ጫማውን ለመቀየር ስንንቀሳቀስ “በፍጹም አይሆንም፤ ይሄ ሂደት የፊውዳላዊ አስተሳሰብ ነው፤ ይህን ሁሉ ዋጋ የከፈልነው ይህ እንዲቀር ነው፤ ገና ሄጄ የበረሃ ሸበጤን-ነጠላ ጫማዬን አደርጋለሁ” ሲለን በዚህ የመንፈስ ጥንካሬ ከእስር ይመለሳል ብለን አልጠበቅንም:: ምክንያቱም አራት ዓመት ሙሉ እስር ቤት ሲታሰር በነፍስ ማጥፋት ወንጀል ተይዘው ከታሰሩ ሁለት ታሳሪዎች ጋር ነው የነበረው:: ለጥየቃ የሚያገኘው አባቱንና የአባቱን ባለቤት ብቻ ነበር:: እኛ ከሚዲያው ውጪም ስለሆነ የመደናገጥ ስሜት ነበረብን፤ እሱ ግን አንተም እንደሚዲያ ባለሙያ በቦታው ተገኝተህ እንዳየኸው በልበ ሙሉነት “አባቴን ከማግኘቴ በፊት ሕዝቡን ላግኘው፤ በቃ ተውኝ እኔ የሕዝብ ነኝ” እያለ ነበር ሕዝቡን የተገናኘው:: አንዳርጋቸው ተምሳሌት የሆነ መሪ ነው::

**ግዮን፡- በቀጣይ ከአንዳርጋቸው ጋራ ምን ለመሥራት አስባችኋል?**

**ሸዋቀና**፡- እኛ አገር ውስጥ ነው የምንኖረው፤ እርሱ መሪያችን ነው፤ እርሱ በሚሄድበትና በሚከተለው የትግል መስመር አሁንም ከጎኑ ነን፤ ምክንያቱም በእርግጠኝነት አንዳርጋቸው የፍትሕ እጦት፣ የዲሞክራሲና የሰብአዊ መብት ጥሰት እንዲወገድ ለኢትዮጵያውያን አንድነትና ታላቅነት የሚታገል የነፃነት ታጋይ እንጂ አሸባሪ አይደለም ብዬ ነው በግል የማምነው:: የአንዳርጋቸው ጥያቄዎችና ፍላጎቶች የኔ ጥያቄዎች፣ ፍላጎቶችና እምነቶች ናቸው:: የአንዳርጋቸው ሃሳብ የኔም ሃሳብ ነው::



# “እግሩ ስር ወድቄ ረጅም ሠዐት መነሳት ተስኖኝ ነበር”

**እየሩሳሌም ተስፋው**

**ግዮን፦ በግንቦት ሰባት ታስራችሁ ከረጅም ጊዜ እስር በኋላ ስትፈቱ የክሳችሁ ዋና መነሻ የነበረው አንዳርጋቸው ጽጌ በወቅቱ አለመፈታቱን ስታውቂ ምን ተሰማሽ?**

**እየሩሳሌም፦** እኔ እስሬን ጨርሼ ነው እንጂ የወጣሁት በምህረቱ አይደለም:: እኔ ከመውጣቴ አንድ ወር በፊት ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይለቀቃሉ የሚለውን ነገር ሰምቻለሁ:: በፍጹም አዕምሮዬ ውስጥ አንዳርጋቸው ይወጣል የሚል እምነት መቼም አልነበረኝም:: አሁን ስወጣ ሳየው ነው ያረጋገጥኩት እንጂ እስከመጨረሻው ሠዐት እምነቱ አልነበረኝም::

**ግዮን፦ ለምንድን ነው አይፈታም ብለሽ ያመንሽው?**

**እየሩሳሌም፦** ምክንያቱም አንደኛ ብዙ ወጪ አውጥተው የያዙት ሰው ነው:: ያንን ወጪ ሲያወጡ ደግሞ ለድርጅቱ ቁልፍ ሰው መሆኑን ያውቃሉ:: አንዳርጋቸውን ሲይዙት እንደ ግለሰብ ሳይሆን ድርጅቱን እናሽመድምደዋለን ብለው ነው አስበው የያዙት:: ግንቦት ሰባትን እንደዛ እያሰቡት አንዳርጋቸውን ይፈቱታል ብየ አላሰብኩም ነበር::

**ግዮን፦ አንዳርጋቸው እንደሚፈታ ሰምታችሁ፤ ኮሚቴ አዋቅራችሁ ለአቀባበሉ ስትዘጋጁ ነበር:: ከቅዳሜ ጀምሮ እስከ ማክሰኞ ድረስ ፍቺው ሲዘገይ ምን ስሜት ፈጠረባችሁ?**

**እየሩሳሌም፦** ተሰብስበን ስንነጋገር ሁላችንም ውስጥ የነበረው አንዳርጋቸው መጥቶ ከእኛ ጋር ይሆናል ብለን ሳይሆን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ ለአንዳርጋቸው ጥሩ አመለካከት እንዳለውና ፍርሀቱን መስበር እንደሚችል አባቱ ቤት መጥቶ አሳይቷል::

አንዳርጋቸው እንደሚፈታ ማመን ጀምሬ ቢሆንም እንደኔ ኢትዮጵያ ህዝብ መሀል ይቀላቀሉታል ብሎ ከማሰብ ይልቅ ወደ እንግሊዝ ይልኩታል ብዬ ነው ያሰብኩት:: ቢልኩትም ግን ህዝቡ አባቱ ቤት መጥቶ ቤተሠቡን “እናመሠግናለን” እንዲል እና ለአንዳርጋቸው ያለውን ክብርና ፍቅር እንዲገልጽ ነው ጫና ስናደርግ የነበረው:: በኋላ ቁጥር የማስበው መፈታቱን፤ በሆነ ቀን ይለቀቃል የሚለውን እንጂ ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር አልነበረም::

**ግዮን፦ የአንዳርጋቸው ድርጅት አመለካከትና የአቋም ጥንካሬ ደግፈሽ፤ ከመደገፍም አልፈሽ በርሃ ድረስ ትግሉን ለመቀላቀል መንገድ ጀምረሽ ነበርና፤ አይተሽው የማታውቂውን አንዳርጋቸው የተፈታ ዕለት በአካል ስታይው ምን ተሰማሽ?**

**እየሩሳሌም፦** አንዳርጋቸውን ማወቅ የጀመርኩት “ነፃነትን የማያውቅ ነፃ አውጭ” የሚለውን መጽሐፉን ካነበብኩኝ በኋላ ነው:: ከዛ ቀጥሎ የእርሱን ቃለ መጠይቆችና ንግግሮች እየተከታተልኩኝ ማየት ጀመርኩኝ:: አንዳርጋቸው ታሠረ ሲባል እኔን በሕይወቴ እንደዛ ቀን አዝኜ የማውቅበት ቀን እስካሁን ድረስ የለም:: የሁሉም ኢትዮጵያውያን ሀዘን ቢሆንም በጣም ነበር ያዘንኩት:: ቃሊቲ እያለን እኛ ፊት ለፊት ነበር የታሰረው:: ብዙ ጊዜ በቀዳዳ እያሾለኩ እርሱን ለማየት እጥር ነበር:: ሁሌ ከታሰረበት ክፍል የሚያስወጡት ቅዳሜ 8ሠዐት ስለሆነ እርሱ ሲወጣ ለማየት ሁሌም



እጥር ነበር አልተሳካልኝም:: የሁልጊዜ ህልሜ አንዳርጋቸውን ማየት ሆኖ ሳለ ባልገደሉትና ይሄን ያህል ከልጅነቱ ጀምሮ እስከ ሽምግልና መሠዋዕት የከፈለበትን ትግል ቢያይ ሁሌ እመኝ ነበር:: ያንን ፕሮግራም ስናዘጋጅ እንኳ አንዳርጋቸውን አየዋለሁ የሚል እምነት የለኝም ነበር:: ልክ አንዳርጋቸውን የያዘ መኪና ሲመጣ መጀመሪያ ያገኘነው እኛ ነበርን:: እጁን ሳምኩት፤ እስከሆነ ሠዐት ድረስ ራሴን አላውቅም ነበር:: ከመኪና አውጥተን እቤት አስገባነው:: እግሩ ስር ወድቄ ረጅም ሠዐት መነሳት ተስኖኝ ነበር:: እኔንጃ በጣም ድብልቅልቅ ያለ ስሜት ስለተሰማኝ አስር ጊዜ እጁን እስመው ነበር:: ይሆናል ብለህ የማታስበው ነገር ሆኖ ሲታየው በህይወቱ ውስጥ ትልቅ ቦታ ያለው ሰው አጠገቤ ሆኖ ሳገኘው፣ ሳየውና ስዳብሰው በጣም ከባድ ነበር::

**ግዮን፦ ከአንዳርጋቸው ጽናት ጥንካሬ ምንድነው የምትማሪው?**

**እየሩሳሌም፦** ተስፋ አለመቁረጥን ነው:: ከተፈታ ሠዐት ጀምሮ እያለ ያለው ነገር አሁንም ወደ ኋላ እንደማይመለስ ነው:: መቶ ዓመት ቢሆኝ እንኳ ጥያቄአችን እስካልተመለሰ ድረስ ወደ ኋላ አልልም ሲል ነበር:: በምንም አይነት ሂደት ወይም መስዋዕትነት ውስጥ ዋጋ እየተከፈለም ቢሆን ጥያቄው እስካልተመለሰ ድረስ ምንም ነገር ሊገድበን እንደማይችል አስተምሮናል:: አንዳርጋቸው መጀመሪያ ከእነሱ ጋር ስልጣን ውስጥ ነበር ያ ሳይሆን ሲቀር እንግሊዝ ገባ:: በተደጋጋሚ በሠላማዊ መንገድ ቢታገልም ያለመለት ዓላማ ሊሳካ ስላልቻለ ድርጅት መስርቶ በርሀ ገባ፣ ታሠረ:: ሲፈታ የሁላችንም ግምት ወደ ትግሉ ይመለስ ይሆን? የሚል ነበር:: አሁንም ግን አንዳርጋቸው ጽኑ ነው፤ የማይበገር ብረት ነው:: የዓላማና የመርህ ሰው መሆንን ነው ከአንዳርጋቸው የተማርኩት::

**ግዮን፦ ወደ ኋላ ልመልስሽና ወደ ትጥቅ ትግል ስትሄጅ የተያዝሽበት ቀን እና እንዴት እንደተያዝሽ በአጭሩ ግለጭልኝ::**

**እየሩሳሌም፦** ማይካንድራ የሚባል ኢትዮ ሱዳን ድንበር ላይ ነው የተያዝነውና፤ ስንደርስ እንደምንያዝ ባውቅም ስንያዝ በጣም ደንግጬ ነበር:: ከዚህ የሄድነውን እኔን ጨምሮ፣ ብርሃኑንና ፍቅርማርያምን ያውቁናል ያን ያህል የሠራዊት ኃይል ለኛ ምን ያደርጋል? በጣም ብዙ ከባድ መሳሪያ የታጠቁ ደህንነቶችና ወታደሮች፤ አየር ወለድ ቡድን ሁሉ ሳይቀር ነው ከበባ የተደረገብን:: በጣም ከመደንገጤ የተነሳ “እጅ ወደላይ” ሲባል እንኳ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም ነበር::

**ግዮን፦ ከዚህ ሁሉ ሂደት በኋላ አንዳርጋቸው ተፈቶ ግንቦት 22 ቀን 2010ዓ.ም ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ ጋር ተገናኝቷል:: አሸባሪ ተብሎ ተፈርጆ ለዓመታት ካሠረች ሀገር መሪ ጋር መገናኘት ምን አይነት ስሜት ፈጠረብሽ?**

**እየሩሳሌም፦** አጠብቅ ነበር:: በሆነ አጋጣሚ ጠቅላይ ሚንስትሩ ያናግሩታል ብየ አስብ ነበር:: ዶ/ር ዐብይ እስካሁን ሲያደርግ ከነበረው ነገር አንፃር ቀና ሰው፤ ውስጣዊ መልካምነት ያለው ነው ብየ አስባለሁ በራሴ:: በመገናኘታቸው ደስ ብሎኛል:: አሸባሪ ብለው፤ ብዙ ገንዘብ አባክነው፤ ከሰው ሀገር ድረስ ሄደው አፍነው አምጥተው፤ በእኔ መለስ ጊዜ ቢሆን ኖሮ የማይታሰብ እና ሊሆን የማይችል ነበር:: ያሁሉ ነገር ተቀርፎ በክብር ቤተመንግስት ገብቶ ከጠቅላይ ሚንስትሩ ጋራ ስናየው ሁሉም የተሰማውን ስሜት ተሰምቶኛል::

**ግዮን፦ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር፤ ፖለቲከኞች ከእስር መፈታትን ተከትሎ ሠፍቷል ማለት ይቻላል?**

**እየሩሳሌም፦** ምህዳሩ ሠፍቷል ማለት አይቻልም:: አንዳንድ መልካም ሂደቶች አሉ አንዳርጋቸው ተፈቷል፤ ቤተመንግስት ሄዶ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ተገናኝቷል:: ግን ዐብይ በራሱ ፍላጎት ነው ያን ያደረገው ለማለት ይከብደኛል:: ምክንያቱም ቅድሚያ ሊሠሩ የሚችሉ፤ ለምሣሌ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን አልሰረዘም:: እንደ ዐብይ ግን ይሰርዘዋል ብየ አላስብም ነበር:: እስካሁን እንዳይሰርዝ ያደረገው የሆነ ነገር አለ ማለት ነው:: ሌሎች ነገሮችም እንደዛው በመሆናቸው የፖለቲካ ምህዳሩ ሠፍቷል ብዬ አላስብም:: ግን ጥሩ ጅማሬ ነው ማለት ይቻላል::

**ግዮን፦ የእነ ፕሮፌሰር ብርሀኑ ነጋ፣ የጀዋር መሀመድ እንዲሁም የኢሳትና የኦ ኤም ኤን ክስ መቋረጥን እንዴት ታየዋለሽ?**

**እየሩሳሌም፦** ስለ ፖለቲካ ምህዳሩ ስናነሳ ጥሩ ጅማሬ ነው ከምንለው አንደኛው ይሄ ጉዳይ ነው:: ምናልባት ግንቦት ሰባትና ሌሎቹ “አሸባሪ ድርጅቶች አይደሉም” ብሎ ከሽብር ክስ ነፃ ማድረጉ የመጀመሪያ መልካም እርምጃ ሊሆን ይችላል::

**ግዮን፦ በመጨረሻ ቀረ የምትይው ወይም ማስተላለፍ የምትፈልጊው ነገር ካለ?**

**እየሩሳሌም፦** የማስተላልፈው መልዕክት እኔ ከእስር ከወጣሁ በኋላ ዘመቻ አድርገን ነበር:: ከዚያ በፊትም ብዙ ዘመቻዎች ነበሩ፤ አሉም:: ከዘመቻው ጀምሮ አንዳርጋቸው እንዲፈታ ጥረት ያደረጉ ሰዎች፤ የአቀባበል ፕሮግራሙ የደመቀና ታሪካዊ እንዲሆን ያደረጉ በሀገር ውስጥም፤ በውጭም ያሉ ሰዎችን በአጠቃላይ በአንዳርጋቸው ስም ከልብ አመሰግናለሁ::

# አንዳርጋቸው ጽጌ....
# “ለወገኑ ነጻነት፣ ነጻነቱን ተነፍጎ የኖረ ነጻ አውጪ”


ታምራ ት መርጊያ

*ተለቀቀ ሲባል ገብረ ዋህድ ነው ብዬ፣*
*ነፃ ወጣ ሲሉኝ መላኩ ነው ብዬ፣*
*ለካስ አንዲ ኖሯል፣ የነጻነት አርማው*
*የአንድነት ተምሳሌት፣ ታላቁ ሰውዬ!!!*

...ብላ ተቀኘች አሉ፤ አንዲት የአንዳርጋቸው ጽጌን ከእስር መፈታት ማመን ያቃታት አዝማሪ።

ምን ታድርግ? እውነቷን ነው። በርግጥም ከወራት በፊት ይህ ይሆናል ብሎ ያሰበ ሰው አይኖርም። ከነበረ ግን በርግጥ ያ ሰው ወይ ነብይ ወይም ደግሞ ወልይ መሆን አለበት።

የሆነው ሆነና ግን ቢያንስ በኔ እድሜ ኢትዮጵያችን እንዲህ እንደሰሞኑ ሰርግና ምላሽ ሆኖላት አይቼ አላውቅም። እሰይ!!! ያድርግላት። ደግሞም ያዝልቅላት።

ይህን እንድል ያስገደደኝ እውነታ የሰሞኑ የአንዳርጋቸው ጽጌ (አንዲ) ከእስር መፈታት ብቻ አይደለም። ከርሱ ቀድመው ነጻ የወጡ የሕሊናና የፖለቲካ እስረኞችን ታሳቢ በማድረግ ጭምር ነው።

ስመ ጥሩ ፖለቲከኛ አንዳርጋቸው ጽጌ የዛሬ 63 ዓመት ነበር ትንሿ ኢትዮጵያ በሆነችው የሸገር ምድር የተወለደው። በ1967 ዓ.ም የተካሄደውን የኢትዮጵያ አብዮት ተከትሎ፣ የደርግን አገዛዝ በመቃወም የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ፓርቲን (ኢሕአፓ) በመቀላቀልና እንደብዙዎቹ የወቅቱ ወጣቶች ሁሉ ህቡዕ (underground movement) በመግባት የፖለቲካ ሕይወትን አሐዱ ብሎ ጀመረ። በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ የነበረውና አምሐ ጽጌ፣ የተባለ ታናሽ ወንድሙ በፀጥታ ሐይሎች ተገድሎ ሕይወቱን ማጣቱን የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ግለ ታሪክ ያመለክታል።

በኋላም በኢህአፓ ውስጥ በተፈጠረው ርዕዮተ ዓለማዊ ክፍፍልና የተከተለውን የእርስ በርስ መተላለቅ ተከትሎ፣ አንዳርጋቸው ወደ ጎረቤት ሱዳን በመሰደድ፣ ዘግይቶም ወደ እንግሊዝ አገር በመኳዝ፣ የእንግሊዝ ዜግነት ለማግኘት ቻለ። ይሁን እንጂ የዶክተር ዓቢይ አህመድን አባባል ተውሰን “ኢትዮጵያዊውን ከኢትዮጵያ ማውጣት ይቻል እንደሆን እንጂ፣ ኢትዮጵያን ከኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ ማውጣት አይቻልም” ና የእንግሊዝ ዜግነትን ያገኘው አንዳርጋቸው እናት ሀገሩን ኢትዮጵያ እንኳን ከልቡ ሊያወጣት ቀርቶ፣ ይበልጥ በደሙና በሥራ አካላቱ ተሠራጭታ፣ በየደረሰበት ተሸክሟት ሲዞር ኖረ።

ይልቁንም በ1983 ዓ.ም. የደርግን ውድቀት ተከትሎ፣ የዩኒቨርስቲ ጓደኛው የነበሩት ማቹ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ይመሩት የነበረውና አዲስ የተቋቋመውን ኢህአዴግ መራሹ መንግሥት ለዴሞክራሲና እኩልነት ይሠራል ብሎ በማሰብ በውጭ በተማረው ትምህርት ወገኑን ለማገልገልና የወቅቱን አዲስ መንግሥት ለማገዝ በማሰብ በልቡ ተሸክሟት ወደሚኖረው ኢትዮጵያ ተመልሶ መንግሥታዊ ሐላፊነት ተሰጥቶት መሥራት ጀመረ።

ውሎ አድሮ ግን የኢህአዴግ አሠራር ምንም አልጥምህ ሲለውና በተለይም ሥርዓቱ የሚያቀነቅነው የዘውጌ ፖለቲካ (Ethnicity-oriented politics) ለህዝብና ለሀገር የማይጠቅም እንዳልሆነ ባሰበና ባመነ ጊዜ ሥልጣኑንን አሽቀንጥሮ ጥሎ ወደመጣበት ወደ ሀገረ እንግሊዝ መልሶ ተኳዘ። ሆኖም ግን አሁንም ኢትዮጵያን በልቡ እንደተሸከማት ጸና።

ያም ሆነ ይህ ግን አንዳርጋቸው ጽጌ ከኢህአዴግ ጋር ዓይንና ናጫ መሆን የጀመረውና፣ ጥርስ ውስጥ የገባው ከዚህ ጊዜ አንስቶ እንደሆነ መገመት ይቻላል።

በ1997 ዓ.ም. ደግሞ በወቅቱ በሀገሪቱ ውስጥ የተፈጠረውን የፓለቲካ መነቃቃትና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ሊካሔድ ይችላል ብሎ ያሰበውን ምርጫ ለመሳተፍ እና የበኩሉን አገራዊ አስተዋጽኦ ለማበርከት ተመልሶ ወደ ሀገሩ ኢትዮጵያ በመምጣት በወቅቱ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ምክትል ሊቀ መንበር በነበሩት ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ጋባዥነት ቅንጅትን ተቀላቀለ። እንዳለመታደል ሆነና በዚያ ጅምሩ አምሮ ማብቂያው ያላማረለት የ1997 ዓ.ም. ሀገራዊ ምርጫ ማግስት ጨዋታው ተጋግሎ ኢህአዴግን በእጅጉ ሲያስጨንቀው ጠቅላላ የቅንጅት መሪዎችን ሰብስቦ ለእስር ሲዳርጋቸው የአንዳርጋቸውም እጣ እንደአብዛኞቹ የቅንጅት መሪዎች እግረ ሙቅ ገብቶለት ዘብጥያ መወርወር ሆነ።

ከዚያም ከእስር ከተለቀቀ በኋላ በ2000 ዓ.ም. በሀገሪቱ ውስጥ በሰላማዊ መንገድ ለመታገል የሚቻልባቸው በሮች ሁሉ እንደተዘጉ አምኖ ግንቦት 7 የሚባል ፓርቲ ከጓደኞቹ ጋር በማቋቋም፣ አንዴ ቦግ ሌላ ግዜ ደግሞ ጭልም የሚል የትጥቅ ትግል በማካሄድ ለኢትዮጵያ መንግሥት የጎን ውጋት ሆኖ መቀጠል ቻለ።

እናም ይህ እንቅስቃሴ እንቅልፍ የነሣው የኢህአዴግ መንግሥት ግንቦት 7ን አሸባሪ ድርጅት ብሎ በምክር ቤት በማስፈረጅ፣ በዚህ ድርጅት አባልነት እየፈረጀ በርካቶችን እግረ ሙቅ እያስገባ እንደአሸን ወደ ወህኒ አጓዛቸው። የአንዳርጋቸውንም ዳና አድፍጦ ሲከተል ቆይቶ ከኢትዮጵያ የታሪክ ኩነት ጋር ሁሌም ተዛማጅነት በማያጣው የግንቦት ወር 15ኛ ቀን፣ 2006 ዓ.ም. በሀገረ የመን ሰንዓ ላይ በየመን የጸጥታ ኃይሎች አማካኝነት በቁጥጥር ሥር አዋለው።

ይኸውና አሁን ደግሞ ምስጋና ለኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል፤ ምስጋና ለአዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር እና ከሳቸው ጀርባ ለቆሙ የገዢው ፓርቲ አመራሮች ይግባና፣ ታሪክ ተለውጦ በዚሁ ታሪካዊ የግንቦት ወር ነጻነቱን አግኝቶ ከእስር ወጥቷል።

በአጠቃላይ አንዳርጋቸው ጽጌን በተመለከተ እጅግ ከፍተኛ ዋጋ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ሁሌም የራሱንና የቤተሰቡን የተደላደለና የተመቻቸ ሕይወት መምራት እየቻለ ለወገኖቹ ነጻነት በበረሃ፣ እንደሽማኔ መወርወሪያ በዱር በገደሉ ሲንገላታና ከላይ ታች ሲዋትት አመዛኙን እድሜውን ማሳለፉ ነው። ታዲያ በዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ ውስጥ ሲያልፍ ይህ ጎደለብኝ፣ ምቾቴ ተነካ ብሎ አንድም ቀን ከርዕዩ ጎድሎ አያውቅም። ምክንያቱም እርሱ በርዕዩ የቆረበውና የዓላማ ጽናት ተምሳሌቱ አንዳርጋቸው ጽጌ ነው።

አንዳርጋቸው እዩኝ እዩኝ የሚል ዓይነት ሰው አይደለም፤ ላመነበት ግን ወይ ፍንክች። በቃ እርሱ የተፈጠረው ለመስጠትና ለመሥዋእትነት ነው። ለነገሩማ “ፖለቲካና እምነት መስጠትን ይሻሉ” አይደል የሚባለው።

እናም አንዳርጋቸው ጽጌ ራሱን ለህዝብ የሰጠ የነጻነት ፋና ወጊ ነው። ለዚህም ነው የአንዳርጋቸው መፈታት የሁሉም ኢትዮጵያዊ መፈታት የሚሆነው። ወገኖቹን ነጻ ለማውጣት እርሱ ከአሳሪዎቹ ጋር እየተሳደደ ነጻነቱን አጥቶ ኖሯል። በመሆኑም ወደድንም ጠላንም ሁላችንም ኢትዮጵያውያን የአንዳርጋቸው ጽጌ ባለ እዳዎች ነን።

እዳችንን መክፈል የምንችለው ደግሞ ለከፈለው መሥዋእትነት እውቅናና ክብር መስጠት ስንችል ብቻ ነው።

በርግጥ አንዳርጋቸው በአሁኑ ሰዓት ሰውነቱ ተጎሳቁሎ ሊታይ ይችላል። ወትሮስ ሰውነት ወረተኛ አይደል። ይሁንና ዝለት የማያውቀውና በወገን ፍቅር የተዋጀው ከጠንካራ ዓለት የፀናው ብርቱ መንፈሱ ግን በማንኛውም ሁኔታ ዝንፍ እንደማይል የሚጠያይቅ አይደለም።

አንዳርጋቸው ጽጌ ሽብርተኛ ተብሎ ተፈጻሚ ባይሆንም የሞት ፍርድ ተፈርዶበታል። ለበርካታ ጊዜያት ታስሮ ሲንገላታም ቆይቷል። ይሁንና አሳሪዎቹ ያሻቸውን ታርጋ ቢለጥፉበትም፣ አንዳርጋቸው ጽጌ የሚታገልለት ሕዝብ ግን የነጻነት ታጋይ መሆኑን ስለሚገነዘብ፤ በልቡ “ነጻ አውጪ” ብሎ ለታሪክ ያኖረዋል። ልዩነቱ ፔንቲ ሊንከን የተባለው ጸሐፊ እንደገለጸው “በአሸባሪ እና በነፃነት ታጋይ መሀከል ያለው ልዩነት የአመለካከት ብቻ ነው። የሚወሰነው እንደተመልካቹ እይታና በታሪክ ፍርድ ብቻ ነው።” እናም ታሪክ የአንዳርጋቸውን ነጻ አውጪነት በወርቅ ክታብ ከትቦ በትውልዶች መፈራረቅ ውስጥ ሲመሠክርለት ይኖራል።

***እድሜና ጤና ለአንዳርጋቸው ጽጌ ይሁን!!!!***



# አንዳርጋቸው ፅጌ – የገብርኤሉ መንገድ ካህን

ግርማ ሠይፉ ማሩ

ኢትዮጵያ አገራችን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመግባት ብዙ ታሪካዊ አጋጣሚዎች፤ እንዲሁም ደግሞ ሁለት ሥር-ነቀል የሚባሉ ለውጦች በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ አስተናግዳለች:: ከእነዚህ አንዱ የሆነው የዛሬ ሃያ ሠባት ዓመት ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም የነበረው ለውጥ በብዙዎች ዘንድ ብሩህ ተስፋ አጭሮ ነበር:: ይህ ተስፋ ካጫረባቸው ሰዎች አንዱ በቅርቡ ከእስር የተፈታው ከየመን ታግቶ የመጣው የነፃነት ታጋዩ አንዳርጋቸው ፅጌ ነው:: በዚያ ክፉ ጊዜ ይህ ሰው እንደ ብዙዎቻችን ተስፋ መሰነቅ እና ለበረኻኞቹ ዕድል እንስጣቸው ብሎ አልተቀመጠም:: ይልቁንም ላግዛችሁ እችላለሁ፣ ከለውጥ ባቡሩ መሳፈር ብቻ ሳይሆን ልሾፍር ብሎ አዲስ አበባ በመግባት፣ የሽግግር መንግስቱን በአዲስ አበባ ዋና ፀኃፊነት በማገልገል ተሳትፏል:: ይህን ጉዳይ ያነሳሁት አንዳርጋቸው በአስገራሚ ሁኔታ ይህን ተሳትፎ በክብር ለመሞት እንደ ውለታ እንዲቆጠርለት፤ ለአሳሪዎቹ ጥያቄ ማቅረቡን ስለነገረን ነው:: ማሩኝ አትግደሉኝ፣ በክፉ ቀን አብሬያችሁ ነበርኩ፤ አይደለም ያላቸው:: እየሳቁ በክብር ለሞሞት የሚዘጋጅ ጀግና ፊታቸው ሲቆም፤ አሳሪዎቹ ምን እንደተሰማቸው ወደፊት በዝርዝር የማወቅ ዕድሉ ይኖረናል ብዬ አምናለሁ:: ከዚህ የምንማረው ትልቁ ነገር አምነን ለቆምንለት ዓላማ፣ በጠላት ዕጅ ውስጥ ብንሆንም ለክብር ሞት መዘጋጀት እንዳለብን ነው:: ይሰማል!!!

አንዳርጋቸው ፅጌ በመስራችነት የተሰለፈበት ግንቦት ሠባት፣ የጠመንጃ ሱስ እና ወንድም ወንድሙን ገድሎ ጀግንነት የሚመዘገብበት ዐውድ ለመፍጠር ፍላጎት እንደ ሌለው ማንም ንፁህ ሕሊና ያለው ይረዳል:: ነገር ግን በመሣሪያ ኃይል ሥልጣን የያዘ የሚመስለው በህወሓት ቁጥጥር ሥር የነበረው መንግሥት (አሁን ህወሓት በዚህ ደረጃ ያለች ስለማይመስለኝ ነው::) ፉከራው ሁሉ መንገዱን ጨርቅ ያርግላችሁ በሚል ትዕቢት ውስጥ መግባቱ፣ ብረት ለማንሳት ዋነኛው ገፊው ምክንያት እንደነበር እንረዳለን:: "የማሪያም መንገድ" ከተዘጋ፣ "የገብሬሉ" ይከፈታል ብለን ብንወተውትም የሚሰማን አላገኘንም ነበር::

የገብሬሉ መንገድ ሲከፈት ደግሞ ከካህናቱ አንዱ ሆኖ ብቅ ያለው፣ ህወሓቶች በሚያሳዩት ዕብሪት በንዴት በመጦዝ፣ እነርሱ ጫማ ስር ለማጎንበስ እና ለመጫን ፈቃደኛ ካልነበሩት አንዱ ውስጣቸው ሆኖ ገምግሟቸው "ነፃነት የማያውቅ፣ ነፃ አውጪ" ብሎ ስም ያወጣላቸው አንዳርጋቸው ፅጌ ነው:: ይህ ሰው በአንዲት ክፉ ቀን እና አጋጣሚ ምናልባትም ወደ ፊት ይፋ በሚወጣ ልዩ ድባብ ህወሓት "ደህንነቶች" እጅ ስር ወድቆ ለአራት ዓመት በቁጥጥራቸው ሥር ሆኖ ነበር:: ይህን የጨለማ ዘመን ለማሰብ ይከብዳል:: ሕገመንግሥታዊ ሥርዓት ብለው እየተመፃደቁ፤ አንድ መስመር የሕገመንግሥት ድንጋጌ ከማያከብሩ ኃይሎች ቁጥጥር ውስጥ ሲኮን ደግሞ ጨለማው ድቅድቅ ነው::

ባለፉት አራት ዓመታት የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን "የገብርኤል መንገድ ካህን" ምን አደረጉት? ምንስ ያደርጉት ይሆን? የሚለው ስጋት ወጥሮት ነበር:: አንዳርጋቸው በመረጠው የገብርኤል መንገድ ባንስማማ፣ ተገፍቶ የገባበት መሆኑን የምንረዳ ሁሉ በዚህ ጭንቅ ውስጥ እንደነበርን ለማንም ግልፅ ነው:: በግሌ አገሩን እንደሚወድ ዜጋ አንዳርጋቸው ላይ በዚህ መንግሥት ሊደርስ የሚችለውን ግፍ በማሰብ አገሬ በምን ደረጃ ልትዋረድ እንደምትችል ሳስበው ይጨንቀኝ ነበር:: መንግሥቱ ኃይለማሪያም ስልሣዎቹን የንጉሡን ሹማምንት፣ አስከትሎም አገሪቱን አሉኝ የምትላቸውን ጄነራሎች ገድሎ በግሉ የፈጠረለትን ደስታ ባላውቅም ለአገሬ ኢትዮጵያ የፃፈላትን ጥቁር ታሪክ ሳስብ ያመኛል:: የህወሓት ሰዎችም ለአገር በማሰብ ሳይሆን በግል ቂምና በቀለኝነት አንዳርጋቸው ላይ ሊያደርሱ የሚችሉት ግፍ ለአገሬ ኢትዮጵያ አንድ ተጨማሪ ጥቁር ጠባሳ ያለበት ታሪክ እንደሚፃፍ በማሰብ በስቃይ ውስጥ የከረመው ሕዝብ እንዲሁ ከአንዳርጋቸው መፈታት ጋር የሠላም አየር መተንፈስ ችሏል:: በሕይወት እና በጤና ማግኘታችን ደስ የሚያሰኝ ነው::

አንዳርጋቸውን ሳገኘው የተሰማኝ ደስታ ከሁሉም በላይ ከፍ ያደረገው በሠላም፣ በጤና መገኘቱ ብቻ አይደለም፣ እንዲህ ዓይነቱ ልዩ እስር በሚፈጥረው የመረጃ ክፍተት ያልተወናበደ መሆኑ ጭምር ነው:: አንዳርጋቸው "ስል" ከሆነ ጭንቅላቱ ጋር በጤና ስላገኘሁት ደስ ብሎኛል::



በአገሬም ተጨማሪ ጥቁር ጠባሳ የሚፈጥር ታሪክ አለመፃፉ በተጨማሪ አስደስቶኛል::

በዚህ አጋጣሚ የህወሓት /ኢህአዴግ መንግስት በዓለም ልዩ የሆነ "ቶርች ሲስተም" በመፍጠሩ በታሪክ ሊመዘገብለት የሚገባ ይመስለኛል:: በፖለቲካ ጉዳይ የሚያስራቸውን ሰዎች በተለይ ቀንደኞች ብሎ ለሚፈርጃቸው በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን መረጃ እንዳያገኙ ማድረጉ ነው:: ብርቱካን ሚደቅሳ ከደካማ እናቷ እና ሕፃን ልጇ በስተቀር ማንም እንዳይጠይቃት በማድረግ ዕለት ከዕለት ፕሮፓጋንዳ የሚነዛበት የገገርውን ሥርዓት ቴሌቪዥን ፈቅዶ በትግል ላይ ናቸው ብላ የምታስባቸው የፓርቲ አባላት ሲደባደቡ ማሳየት ዋና ተግባሩ ነበር:: በተመሣሣይ አንዳርጋቸው ፅጌ ከዘጠና ዓመት አረጋዊ አባቱ በስተቀር ማንም እንዳይጎበኘው በማድረግ የፈፀሙት ግፍ፤ የፈለጉትን ውጤት አላመጣም:: በፈለጉት መንገድ አንዳርጋቸውን ባለማስጎንበሱ ደስተኛ ነኝ:: ባለፉት ጥቂት ሣምንታት አንዳርጋቸው ቴሌቪዥን እንዲገባለት መደረጉ ደግሞ ከመውጣቱ በፊት ተስፋ እየዘሩብን ያሉትን አዲሱን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐብይ አህመድን ለመተዋወቅ እንደሚረዳው እና ተስፋም እንዲሰንቅ አግዞታል የሚል ዕምነት አለኝ:: ከተፈታ በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አንዳርጋቸውን ለማግኘት መወሰናቸው በራሱ አንድ ትልቅ እርምጃ ነው:: ያለፈውን ትተን ወደፊት ለአገራችን ሠላምና ብልፅግና፤ ለሕዝቦች ክብር የምንቆምበት ቀን የተቃረበ ይመስለኛል::









# የአንዳርጋቸው ፅጌ አቀባበል









